# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር

ወርሃዊ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የታኅሣሥ 5:1953 ኩ ዴታ

## እንቅስቃሾች ማስታወሻ


የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN


ዋጋው፡- 1.50 ብር

ሚያዝያ 1963

ርእሰ–አንቀፅ

## የታህሳስ ጀግኖች

በአንድ ህዝብ ታሪክ ውስጥ አንዳንድ አመታት መጭው ትውል ድ የማያስታውሳቸው ቀናትን እንዳዘሉ ያልፋሉ።አንዳንድ ቀናት ደግሞ "በጥሞታ" ያለፉ በሚመስሉት አመታት ውስጥ ቀስ በቀስ የተጠራቀመ ማእበል ይነሳባቸውና በታሪክ ገፆች ውስጥ ጉልህ የሆነ ቦታን ይይዛሉ።

በታህሳስ ወር 1953 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የተደረገው "የአልጋ ንቅ ንቃ" ሙከራና ያስከተለው ትግል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ "እነዚህን አ ራት ቀናት" የማይረሳ ዝክር ጥሎላቸው አልፏል።አንድን ታሪካዊ ወቅ ት ለመፍረድና በረጅም የህዝብ ታሪክ ውስጥ የሚዘውን ቦታ በትክክል ለመመዘን አስር አመት በጣም ትንሽ ጊዜ ነው።ቢሆንም፣የምናውቀው ንና የምንችለውን ያህል በዚህ የታህሳሳዊያን ሙከራ ላይ በመወያየት ላመኑባት ኢትዮጵያ ህይወታቸውን ሳይሳሱ የሰጡላትን ጀግኖች ማስታ ወስ ተገቢ ተግባር ነው ብለን እናምናለን።ይህንን "የታጠቅ" ቁጥር ለዚ ህ ለታህሳሳዊያን ሙከራ መዘከሪያ ማቅረባችን በዚሁ እውነት በመገፋ ፋት ነው።ይህንንም በምናደርግበት ወቅት የነዚህን አገር ወዳዶች ድርጊ ት መዘከሩ ብቻ በቂ አይደለም።በዚህ ብቻ ከተወሰንን ተገቢ ዋጋውን ገዘ ቅ እናደርገዋለን።

እነዚህን ቆራጦች የምናስታውሳቸው ዛሬ እኛም እንደነሱው ሀገ ራችንን በመውደድ፣እንደነሱው ለህዝባችን መልካም ኑሮ በመቆርቆር፣ የትግል ጉዳና ስለመረጥን ነው።የትናንትናው ትግላቸው የዛሬው ትግላ ችንና መጭው ትግል በኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ትግል ታሪክ ውስጥ አ ንዱ ለሚቀጥለው መነሻ በመሆን... እንደሰንሰለት የሚያያዝበት አንድ ነት አለው ብለን እናምናለን።ስለዚህ እነሱን መዘከር ዋጋ የሚኖረው የ ትናንትናውን ትግላቸውን፣የዛሬውን ትግላችንን በተሻለ ዘዴና በጠለቀ አላማ ለመቀጠል ቆርጠን የተነሳንና ከከሸፈው ሙከራቸው የሚገኘው ን ትምህርት ሁሉ ለመቅሰም የቻልን እንደሆነ ነው።

ለመሆኑ ታህሳሳዊያን እነማን ነበሩ?የትግላቸውስ አላማ ምን ነበ ረ?የትግላቸውስ ዘዴ?እኛስ፣ከዚህ ሁሉ፣ለያዝነው ትግላችን፣ለምንቀጥለ

ው ትግላቸው ምን ትምህርት እናገኛለን?እነዚህን ጥያቄዎች እያንዳን
ዱ ኢትዮጵያዊ ሊወያይባቸው ይገባል ብለን እናምናለን።በዚች ፅሁፋች
ን አንዳንድ አጠቃላይ ሀሳቦችን ለመሰንዘር መሞከራችን አብረው የሚ
ቀርቡት ፅሁፎችና ልዩ ልዩ መረጃዎች ይህን አስፈላጊ ውይይት ለመከ
ፈት ይረዳሉ ብለን ተስፋ በማድረግ እንጂ ከፍ ብለው የተደረደሩትን ጥ
ያቄዎች አሟልተን እንመልሳለን የማለት ግምት አድሮብን አይደለም።

ታህሳሳዊያን እነማን ነበሩ?

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በገዢው መደብ ውስጥ ያሉ ክፍሎች ለ
ስልጣን የሚያደርጉት ትንንቅ አዲስ ነገር አይደለም።በሃይለስላሴ ዘመነ
መንግስት እንኳን ብንወስን የምንረዳው ይህንኑ ቋሚ እውነት ነው።የጊ
ዜው "ጃንሆይ" ራሱ ከተራ አገረ ገዥነት በመነሳት ለንጉሰ ነገስትነት የ
በቃው በ1909 ዓ.ም. በመስከረም ወር ከሸዋ መሳፍንት ጋር ሆኖ በልጅ
ኢያሱ የመታው ሴራ ፍሬ በመስጠቱ ነው።ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስልጣን
ይዞ እስኪደላደል፡ተደላድሎ ፈላጭ ቆራጭ እስኪሆን፡ከፈላጭ ቆራጭነ
ት ደግሞ ዛሬ የውጭ ሃይሎች መሳሪያ እስኪሆን ድረስ ያሁኑ ንጉሰ ነገ
ስት ብዙ የትግል ውሽንፍር የመታውና አያሌ የትግል ድምፅ ያፈነ ሰ
ው ነው።

በዚህ ረጅም ዘመን የሃይለስላሴ ስልጣን ከእጅ መውጣት አፋፍ እ
የደረሰች ደጋግማ ተመልሳለች።በግልፅና በምስጢር የተደረጉትን ሙከ
ራዎችና ሴራዎች ምናልባት ከንጉሰ ነገስቱና ከቅርብ ደጋፊዎቹ በስተቀ
ር ልካቸውን ለይቶ የሚያውቅስው፡ያለ አይመስለንም።ግን ከዚህ ሁሉ
መሀል የታህሳሳዊያን ሙከራ አዲስ የሚያደርገው ምንድነው? በበኩላ
ችን እንደምናምነው ይህንን የታህሳሳዊያን ሙከራ በታሪካችን አዲስ የ
ሚያደርገው ሞካሪዎቹ ራሳቸው የቆየው የፊውዳል ስርአት መጠነኛ እ
ድገት የፈለፈላቸው ከዚህ በፊት በሃገሪቱ ያልታዩ አዳዲስ ሃይሎች መ
ሆናቸው፡በግልፅ ለእርምጃ ብለው መነሳታቸውና ለዚህም ለታቀደው እ
ርምጃ ፊታቸውን ወደንጉሰ ነገስቱ ከመመለስ ይልቅ የቆየው የአገዛዝ
ዘዴ ብቁ አለመሆኑን ተገንዝበው አዲስ ዘዴን በሃይል ሊያመጡ መነሳ
ታቸው ነው።

ታህሳሳዊያን በድንገት ከሰማይ ዱብ አላሉም።እንደማንኛውም የ



ህብረተሰብ ክፍል ሁሉ ምንጫቸው፡በታሪካችን ውስጥ ቀደም ብሎ ፈል
ቋል።ይህ ቀዋሚ ህግ ነው፤ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል በታሪክ ውስጥ
ጉልህ ድምፁን ከማሰማቱ በፊት ቃፊሮቹ እየተንጠባጠቡ በቅድሚያ
ብቅ ይላሉ።እንደዚሁም በሀገራችን ከታህሳሳዊያን በፊት ለኢትዮጵያ ህ
ዝብ እርምጃ የሚፈልጉ ሰዎች (ሀይሎች) ነበሩ።በያዝነው መቶ አመት
ግድም ብንሄድ እነነጋድራስ ግብረህይወት ባይከዳኝ፡እነፕሮፌሶር አፈወ
ርቅ የጊዜውን የአገዛዝ ስርአት በመቃወም የጃፓንን፡የቻይናን ምሳሌ እ
የጠቀሱ የተፋጠነ እርምጃ እንዲደረግ፡ነጋድራስ ገብረህይወት እንዳሉ
ት «የኢትዮጵያ ህዝብ ከተኛበት እንዲነሳ» ይወተውቱ ነበር።ለኢትዮ
ጵያ ህዝብ ወደኋላ መቅረት ምክንያት የሆነው የቆየው ስርአት መሆኑ
ን በመገንዘብ የአገዛዙን ዘዴ በየጊዜው ይቃወሙ ነበር።ነገር ግን በዚህ
ጊዜ የነበሩት ተራማጆች አላማቸውን ከስራ ላይ ለማዋል የግድ ንጉሰ ነ
ገስቱን ተጠግተው መስራት ነበረባቸው።

ጣልያን ከመምጣቱ በፊት ውጭ አገር የተማሩ የጊዜው ተራማ
ጅ ወጣቶች የፖለቲካ ተፅእኖዋቸውን ለማስፋፋትና አስተያየታቸውን
ለማዳበር፡ሀገሪቱ በይበልጥ ለመራመድ የምትችልበትን ዘዴ ለማወቅና
ለማሳወቅ "የኢትዮጵያ ወጣት" (Jeunesse d'Ethiopie) የሚባል ማ
ህበር አቋቁመው ስለመንግስቱ አሰራር መሻሻል ይወያዩ እንደነበረ ይታ
ወሳል።እነዚህ ወጣቶች ከንጉሰ ነገስቱ ስር ሆነው ማገልገል ሲጀምሩ በ
ማሀል የኢጣሊያን ወረራ መጣ።

በዚህ ጊዜ፡ሀገራችን ከታላላቆቹ ባላባቶች የጥቅም ሽሚያና ጭቅ
ጭቅ፡በተለይ ደግሞ ስርአቱ ከተረፈላት ዝቅተኛ "የስልጣኔ" ደረጃ የተ
ነሳ፡ለጠላት ወረራ በጣም የተመቸች ነበረች።አንዳንዶቹ ታላላቅ ባላባቶ
ች ከውጊያው በፊት፡በውጊያው ጊዜና ከውጊያውም በኋላ ከዱ።የቀሩ
ት ታላላቅ ባላባቶች በተንቤን፡በእንደርታና በማይጨው ለአዲሱ ዘመን
የጦር ትጥቅና አመራር ፈፅሞ ብቁ አለመሆናቸው ታየባቸው።"የሰለጠነ"
ከግር እስከራሱ የታጠቀ ጠላትና በባላባቶች አገዛዝ "የተራቆተች"፡የተ
ከፋፈለች፡ወደኋላ የቀረች፡ጦር ይዛ የተሰለፈች አገር ተጋጥመው ኢትዮ
ጵያ በጥቂት ጊዜ ውስጥ የብዙ ዘመናት "ነፃነቷ" ተደፈረ።በዚህ ጊዜ የ
ነፃነቷን ፋና አላስነካም ብሎ በየጫካው፡በየወንዙ፡በየሸንተረሩ የተሰማ

ራው ህዝብ በትናንሽ ባላባቶች፣ከህዝቡ ከራሱ በፈለቁ ቆራጥ መሪዎች፣
በተማሩ ሀገር ወዳድ ወጣ ች እየተመራ ትግሉን ያለንጉሰ ነገስቱና ያ
ለታላላቅ ባላባቶች ቀጠለ።

በትግሉ ጊዜ የብዙዎቹ አላማ ሲያነፈንፍ ቆይቶ በመጨረሻ በመ
ርዝ ጨ.ስና በቦምብ ብዛት ገፍቶ የመጣውን ጠላት እንደምንም አስወ
ጥቶ በቀድሞው ስርአት ውስጥ ተመልሶ ለመደላደል እንደነበረ ግልፅ
ነው።ነገር ግን እንደማንኛውም ሰፊ ንቅናቄ በዚህም ትግል ውስጥ የጊ
ዜውን ሁኔታ አበጥሮ በመረዳት ነገን አልፈው የተመለከቱ ነበሩ።እነዚ
ህ አዳዲስ ሃይሎች የሀገራቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ በጦር ግንባር መመ
ታት በጣም ያስቆጫቸው ሲሆኑ፣ለዚህም ለኢትዮጵያ መሸነፍ በህላፊነ
ት ከሚጠቅሷቸው ጉዳዮች አንዱ የሀገሪቱ "አለመሰልጠን" ነበር።ወደ
ኋላ የመቅረቱም ምክንያት የጊዜው አገዛዝ ዘዴ ብልሹነት መሆኑን ብ
ዙዎች አርበኞች እየተመለከቱት ሄዱ።

እርግጥ እነዚህ ሃይሎች ከፊውዳሉ አብራክ ውስጥ የተፈለፈሉ ና
ቸው።ቢሆንም የተወሰኑት(በተለይ የተማሩ ወጣቶች፣የሆለታ ተመራቂ
ዎች፣በፈረንሳይና በመስኮብ የተማሩ . . . ) የፊውዳሉን ስርአት ጉድለ
ት በቀላሉ ለማየት በመቻላቸው ጣሊያን ከወጣ በኋላ ሀገሪቱን ወደፊት
ለማራመድ አስፈላጊ የሆኑትን የፖለቲካ ማሻሻያ ዘዴዎች ያሰላስሉ ነበ
ር።ታህሳሳዊያን ከስራ ላይ ሊያውሉ የሞከሩት፣ከንጉሰ ነገስት ውጭ በእ
ርምጃ ስም የሚደረገው የአስተዳደር መሻሻል ጥንስስ ከዚህ ጊዜ ጀም
ሮ ይታያል።በዚህ ወቅት፣በተለይ በፖለቲክ፡አስተያየታቸው ይበልጥ የተ
ራመዱ ሀገር ወዳዶች እንዲያውም ከጠላት በኋላ ዘውድ የሚባለው ቀ
ንበር ተመልሶ በኢትዮጵያ ህዝብ ትከሻ ላይ እንዳይጫን በሱ ፈንታ የ
"ሪፑብሊክ" መንግስት እንዲቋቋም ይጣጣሩ ነበር።

ነገር ግን አንድን የአስተዳደርና የአገዛዝ ዘዴ ለመለወጥ የጥቂት
ሰዎች መልካም ፈቃድ ምንጊዜም አይበቃም።እንደዚህ አይነቱ አላማ
ከስራ ላይ ሊውል የሚችለው ለአዲሱ ስርአት መሰረት ሊሆኑ የሚች
ሉት አዳዲስ ሃይሎች በአሮጌው ስርአት ውስጥ ስር ሰደው በሚገባ ሊ
ያድጉና ሆነ ብለው ተደራጅተው ለለውጥ ሲታገሉ ብቻ ነው።እንግዲህ
በዚህ ዘመን ለአዲሱ የፖለቲክ አቋም መሰረት ሊሆኑ የሚችሉት አዳ



ዲስ ሃይሎች ገና መነቃነቅ በጀመረው የፊውዳል ስርአት ውስጥ ብቅ ብ
ቅ ማለታቸው ነበር።

ለዚያውም እነዚህ አዳዲስ ሃይሎች ከጠላት ጊዜው ፈተና የባሰው
ን ተደቁሰው ወጡ።የተማሩ ወጣቶች በፋሺስቶች እየታደኑ ተገደሉ።
ብዙዎቹ በሀገር ፍቅር በመመራት ጠላትን በተመቻቸው መንገድ ሲታ
ገሉ በያለበት ወድቀው ቀሩ።ስለዚህ ንጉሰ ነገስቱ ተመልሶ ለመደላደል
በሚፍጨረጨርበት ወቅት ይህ ከቀድሞውም ስር ያልሰደደ የእርምጃ ሃ
ይል፣ይህ ለአሮጌይቱ ኢትዮጵያ አዲስ ተስፋ ይሰጥ የነበረ እስትንፋስ እ
ንዳልነበረ ሆኖ ተዳከመ።ነገር ግን በፍፁም አልሞተም።

ጠላት ከወጣ በኋላ ከያለበት በየምክንያቱ የሚቀሰቀሰው አመፅ የ
ሃይለስላሴን ስልጣን አዋከበው።በዚህ ጊዜ ግን እንደጥንቱ የባላባቶች
የርስ በርስ ትንንቅ፣የጠቅላይ ግዛቶች አመፅ፣ብቻ አልነበረም።ይበልጥ የ
ተፋጠነ እርምጃ የሚፈልጉ አርበኞች፣በጣሊያን ጊዜ እንደተጀመረው
ከንጉሰ ነገስቱ አልፈውና ከንጉሰ ነገስቱ ውጭ ለሀገራቸው ደህንነት መ
ስራታቸውን አላቋረጡም ነበር።

አንዳንድ አርበኞች ንጉሰ ነገስቱ ከስልጣኑ ካላከፈለ የሀገሪቱ እር
ምጃ ይሰናከላል የሚል እምነት ስለቀሰቀሳቸው በሃይለስላሴ ላይ ሴራ መ
ምታት ጀመሩ።ከነዚህም ውስጥ በይበልጥ የተጠረጠሩት የታወቁት አር
በኛ ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሀዋርያት ወዲያውኑ መታሰራቸው ይነገራ
ል።በዚሁ ሴራ ምክንያት ብዙ አርበኞች ሲታሰሩ፣በሀይል ከሚጠረጠሩ
ት ውስጥ ብዙዎቹ እየታደኑ ተገደሉ፤በፈተናው ዘመን ከታወቁት ወጣ
ት አርበኞች አንዱ የሀንስ ሽመረጃ በሻህ "ባልታወቁ ሰዎች" በጥይት ተ
ገደለ።

በዚህ ዘመን ከያለበት የሚሰነዘረው የትግል ውሽንፍር እየተደላ
ደለ በሚሄደው በሃይለስላሴ ስልጣን ተመታ።እንግሊዞች በሚሰጡት የ
ማያቋርጥ እርዳታ፣በዘመኑ መልክ በተሰናዳ ሃይለኛ የፖሊስና የፀጥታ ድ
ርጅት፣በዘመኑ ከፍተኛ ተክኖሎጂ ሙሉ በሙሉ በሚጠቀም ፕሮፓጋን
ዳ፣ህዝቡ አይቶት ሰምቶት በማያውቀው ዘዴ በጨቋኝ አገዛዝ ስር ተያዘ።
በአከባቢውም አለም ሁለተኛው የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነት ተፈ ፅሞ፣
"በአሸናፊነት" የወጡት ኢምፔሪያሊስት ሃይሎች እንደቀድሞው ተደላ

ድለው የቀድሞ ብዝበዛቸውን የሚያፀድቁበት አለም ተመልሶ የመጣ
መሰላቸው። ሃይላስላሴና በጠቅላላው የገጋርው መደብ በዚህ በኢምፔሪ
ያሊስቶች ዘረፋ በተያዘው አለም ውስጥ ለመቀመጥና ከሚገኘው "ስል
ጣኔ" እየተካፈሉ ጦሰላም ለመኖር መደላደል ጀመሩ።ለዚህ "ስልጣኔ" ድ
ልድይ የሚሆኑ ወጣቶች ለማነፅ ወደኢምፔሪያሊስት አገሮች ብዙ ኢ
ትዮጵያዊያን ተላኩ።በ1945 አ. ም. በኢምፔሪያሊስቶች አለም መዋኘ
ት የጀመረው የኢትዮጵያ ገጋር መደብ ከጊዜው ሃያል ከአሜሪካ ኢም
ፔሪያሊዝም ጋር ጥቅሙንና ህይወቱን በማስተሳሰር "የጋራ መከላከያ"
ውል ፈርሞ በቅርቡ ከኢትዮጵያ ጋር "በተደባለቀችው" በኤርትራ "ራ
ዲዮ ማሪና" የተባለው(በኋላ ቃኘው ተብሎ የተሰየመው) የጦር ሰፈር
እንዲስፋፋ ተዋዋለ።

ይህ ዘመን የጊዜው ንጉሰ ነገስት በርግጥ በፊላጭ ቆራጭነት የገዛ
በት ዘመን ነው ሊባል ይቻላል።በዚህ ጊዜ የተነሳው ሌላ የታወቀ ሴራ
የንቢትወደድ ነጋሽ የስልጣን መያዝ ሙከራ ሲሆን ይህ ሙከራ በንጨ
ጨ እንዳለ ለመደምሰስ መቻሉ የሃይለስላሴ ስልጣን ምን ያህል የተደ
ላደለ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ነው።

በዚህ ዘመን የልማት ስራዎች በመጠኑ ተጀምረው በአንዳንድ ከ
ተማዎችና በአካባቢዎቻቸው የመንገድ፣የትምህርት፣የጤና፣ሌላም ልዩ ል
ዩ ድርጅቶች እየተስፋፉ ሄዱ።የውጭ ባለሀብቶች ገንዘባቸውን በሃገረ
ቱ አስገብተው፣ትናንሽ ፋብሪካዎችንና የንግድ ቤቶችን በማቋቋማቸው
በሃገሪቱ አዳዲስ ሃይሎች ማዳበር ጀመሩ።ተከትሎ የመጣው የኢኮኖ
ሚው መልክ መለወጥ መጀመር፣የመንግስት ስራ በያለበት ስር መስደድ፣
የኢምፔሪያሊስቶች ተፅእኖ ማደግ፣በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ለመጀመ
ሪያ ጊዜ ከባላባቱ ስርአት ቀጥተኛ ቁጥጥር ውጭ የሚያስቡና የሚያድ
ጉ ሃይሎችን አፈራ።ወጣት የጦር መኮንኖች፣ላብ አደር ሰራተኞች፣ባለ
ደመወዝ ፀሀፊዎች፣የሁለተኛ ደረጃና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣በውጭ ሃ
ገር ተምረው የተመለሱ ወጣቶች፣እነዚህ ሁሉ፣ከባላባቱ ስርአት የተላቀ
ቀ፣በአዲስ መንፈስ፣በአዲስ ዘዴ የሚንቀሳቀስ እርምጃ የሚፈልገውን የ
አዳዲስ ሃይሎች ክፍል ከመቻውም ይበልጥ አዳበሩት።

በታህሳስ ወር 1953 ዓ.ም. በአገሪቱ ወደኋላ መቅረት ተቆርቁረው



ና ስልጣን ለመያዝ በእርምጃ ስም ተነስተው በአስተዳደሩ ላይ "አመፅ"
የሰነዘሩት የዚህ ታዳጊው አዲስ ክፍል አፈቀላጤዎች ወይም ግንባር ቀ
ደሞች ናቸው።

የዚህ አዲስ ክፍል ግንባር ቀደሞች የታገሉት ከማን ጋር ነው?

ከጠላት ጊዜ ውዲህ የተደረገው መጠነኛ እርምጃ በተለይ የከተ
ማውን ህዝብ ለስልጣኔና ለእርምጃ ከፍ ያለ ጉጉት እንዲያድርበት አድ
ርጎታል።ሀገሪቱ "መሰልጠን" አለባት የሚለው አነጋገር ሁሉ የተቀበለ
ው እምነት ነበር።የዚህ የአዲሱ ስልጣኔ ሞተር ሊሆኑ የሚችሉት ይኸ
ው መጠነኛ እርምጃ የፈለፈላቸው አዳዲስ ሃይሎች(በተለይ የተማሩ ወ
ጣቶች) ናቸው የሚል አስተሳሰብ በአየሩ ላይ ያንዣብብ ነበር።ነገር ግ
ን የባላባታዊው አገዛዝ የነዚህን አዳዲስ ሃይሎች መዳበር ሲቃወም እ
ርምጃ ፈላጊዎችንም በያለበት ይኰረኩም ጀመር። ለምን?

ምክንያቱም የባላባቱ ስርአት መሪዎች ከነሱ ቁጥጥር ውጭ የሚ
ያድጉ ነጋዴዎችን፣ባለፋብሪካዎችን፣የተማሩ ወጣቶችን፣ሌላም ልዩ ልዩ
ባላባቶችንና ሃይሎችን ነፃ መልቀቅ ለስልጣናቸውና ለጥቅማቸው አስጊ
መሆኑ ይገባቸዋል።ስለዚህ ከባላባቱ መደብ መሪ፣ከንጉስ ነገስቱ ቁጥጥ
ር ውጭ፣እንዲያውም ያለሱ ልዩ ፈቃድ የሚዳብርን ማንኛውንም ሃይል
ሆነ ስልጣን በጥብቅ ይቃወማሉ።በሃገሪቱ የሚያድጉትንና ስር የሚሰዱ
ትን የተማሩ ወጣቶች፣ታታሪ ነጋዴዎች፣ባለፋብሪካዎች፣በጠቅላላው በሃ
ገሪቱ ውስጥ "ከልማድ" (ከባላባቱ ልማድ) ውጭ የሚበቅሉትን አዳዲ
ስ ሃይሎች በተቻለ ማቆርቆዝ የባላባታዊው ስርአት ቋሚ ጥቅም የሚ
ጠይቀው እርምጃ ነው።እነዚህ አዳዲስ ሃይሎች ደግሞ የእድገታቸውና
የእርምጃቸው እንቅፋት የቆየው የፊውዳል አገዛዝ ዘዴ መሆኑን እየተ
ረዱት ስለሚሄዱ እያደር ተቃውሞአቸው እየጠነከረ ይሄዳል።

በዚህ ጥረቱ የእርምጃ ፀር የሆነው የባላባታዊው አገዛዝ የሃገሪቱ
ን ታዳጊ ሃይሎች ለመግታት ሲፍጨረጨር ሌላ አዲስ ረዳት አገኘ።ይ
ኸውም ኢምፔሪያሊዝም ነው።እነዚህ ባእዳን ደግሞ በኢትዮጵያ ውስ
ጥ የራሳቸው ንግድ ቢስፋፋ፣የራሳቸው ፋብሪካ ቢዳብር፣የራሳቸው ባህል
ቢሰፍን ለጥቅማቸው ያመቻቸዋል።ይህም እስከጊዜው ድረስ ከአሮጌው
አገዛዝ ጋር የለውጥ ሃይሎችን ለመግታት የጥቅምና የአላማ አንድነት

ሰጣቸው።

እንግዲህ በታህሳስ 1953 ዓ.ም. የተፋጠጡት ሁለት ሃይሎች ናቸው።በአንድ በኩል የቀድሞዎቹ ባላባቶች አገዛዝና ኢምፔሪያሊዝም፤ድጋፋቸው የጥንቲቱ ኢትዮጵያ የአገዛዝና የጭቆና ምሰሶች፡ዘመናዊ ትጥቅ፡ዘመናዊ የማደናገሪያ መሳሪያዎች ናቸው።በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ ኢትዮጵያ "ጥንስስ ግንባር ቀደም" ሃይሎች፤ድጋፋቸው በጣም የተወሰነ ነበር።የጠላቶቻቸው ድርጅት፡የጠላቶቻቸው ሃይል፡የጠላቶቻቸው ተፅእኖ አልነበራቸውም።ሃይላቸው የአላማቸው ትክክለኛነት ብቻ ነበር። ረዳታቸው በሃገሪቱ አየር ላይ ገና ሰብሳቢና አደራጅ አጥቶ የሚያንዣብበው የለውጥ ጉጉት ነበር።

ስለኢምፔሪያሊስቶች ጣልቃ መግባት ከወራን አይቀር አንዳንድ ልንሰነዝራቸው የሚገባን ሃሳቦች አሉ። በትግሉ ውስጥ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ወደ አድሃሪዎቹ አድልቶ ተራማጆችን እንደተዋጋ ዛሬ ሁሉም የሚያውቀው ነው።በቅርቡ የኢምፔሪያሊስቶች ጋዜጦች ደጋግመው ባቀረቧቸው ትችቶች ሙከራው ከመደረጉ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ የንጉሰ ነገስቱ መንግስት ከአሜሪካ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር በምስጢር የተፈራረመውን ውል አጋልጠዋል።ይህም ከያዛቸው ነጥቦች አንዱ፡የአሜሪካን መንግስት ቃኘው ጣቢያውን ለማስፋፋት ሲፈቀድለት እሱ ደግሞ በተራው የሃይለስላሴን ዙፋን ለመጠበቅ ቃል የገባ መሆኑን ገልጧል።የሆነ ሆኖ አሜሪካኖች በዚህ ጊዜ ጥቅማቸውን በመመልከት ሰሩ እንጂ የዚህ ውል መኖር (ያውም በምስጢር የተዋዋሉት) እስከዚህም አያስራቸውም ነበር።

የኢምፔሪያሊስቶች ዋና አላማ በአገራችን ተፅእኖዋቸውን (ባህላቸውን፡የልማት አቅጣጫና ዘዴያቸውን፡ዘረፋቸውን . . . ) ለማስፋፋት ሲሆን ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ደግሞ ለዚህ ተግባራቸው የሚሆኑ ስልጡን አገልጋዮችን ከማሰናዳት አላቋረጡም።ከጥንቶቹ ባላባቶች ይልቅ በነሱ ልምድ ተነክረው የመጡና "የምክራቸውን ይዘት" በደንብ ሊረዱ የሚችሉ ወጣቶች በስልጣኑ ላይ ቢቀመጡ ደስታቸው እንደሆነ አይጠረጠርም።የባላባቱ ስርአት በምንም ነገር ሳያውከው ጠቅላላውን ህዝብ እነሱ በወሰኑለት የግዛት ቀንበር ውስጥ የሚጥልላቸው ለውጥ ከመጣ በምንም አይነት አይቃወሙትም።እንዲያውም የባላባቱ አገዛዝ ከጊዜ ጋር እየበሰበሰ ሲሄድ ለነሱ ተፅእኖ ማስፋፊያ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል፡ ለታዳጊው ዘረፋቸው አገልጋይነቱ ስለሚወስን፡እንደዚሁም ደግሞ የህዝብ ቁጣ ቀስቅሶ መውጫ የሌለው ትርምስ ውስጥ እንዳይጨምራቸው ስለሚሰጉ—ይህን ምንም ህልም ሊያስቀረው አይችልም— "የተባለውን ለውጥ" ራሳቸው ያነሳሱታል።ዛሬ በአስተዳደሩ ውስጥና ዙሪያ የተኮለኮሉት "አዲስ መኰንኖች" ለዚሁ እቅድ የታጩ ሳይሆኑ አይቀርም ብለን እንገምታለን።

ስለዚህ አሜሪካኖች የታህሳሳዊያንን ሙከራ የተቃወሙት በደፈናው "ለውጥን" በመጥላት ሳይሆን ከነሱ ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ሃይሎች በመቀስቀሱ ይመስለናል።አገር ወዳዶቹ ታህሳሳዊያን ለሃገር እንሰራለን ብለው የተነሱበትን አላማ የት ድረስ እንደሚገፉበት ስላልታወቀ በኢምፔሪያሊስቶች አስተሳሰብ ባጭር መቀጨቱ የተሻለ ሆኖ ተገኘ።ከዚህ በላይ ደግሞ በዚያን ዘመን በሃገሪቱ ውስጥ ተፅእኖዋቸው ገና ቦታ ቦታ መያዝ በጀመረበት ጊዜ ስለነበረ ለማዳበሪያ ረዘም ያለ የፀጥታና የሰላም ዘመን ያስፈልጋቸው ነበር።

## የታህሳሳዊያን አላማና የትግል ዘዴ

የትግሉ አላማ፡በአልጋወራሹ ንግግር ላይ እንደተገለጠውም ሆነ፡ በኋላ በተሰጠው ፕሮፓጋንዳ ውስጥ ተደጋግሞ እንደተሰማው፡የሃገሪቱን ጠቅላላ የልማትና የስልጣኔ እርምጃ "ማፋጠን" ከታወጀው ፕሮግራማቸው ለመረዳት እንደሚቻለው ዝርዝር አላማቸው በኢትዮጵያ አዳዲስ ፋብሪካዎችንና ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም፡ብዙ ትምህርት ቤቶችን በያለበት በመስራት፡ለገበሬዎችና ለነጋዴዎች እርዳታ በመለገስ፡"ለሃገሪቱ ከጠቀመ"(?) የውጭ ባለሃብቶችን በመጋበዝ፡የሃገሪቱን ጠቅላላ እርምጃ ለማፋጠንና ለህዝቡ የተሻለ ኑሮ ለማስገኘት ነበር።(መስመርና ጥያቄ ምልክት የኛ ነው)

ህልም እንደፈቺው ነው ይባላል።ይህም ታህሳሳዊያን የዘረዘሩት አላማ የዚሁኑ መልክ የያዘ ነው።እነዚህ ዝርዝሮች በኛም፡በታህሳሳዊያንም፡በባላባቱም መንግስት፡በኢምፔሪያሊስቶችም ተደጋግመው ይጠቀሳሉ።"እንደአላማ" በመደርደራቸው ሁላችንም እንስማማለን።ግን ሁላች

ንም ድብልቅልቃችን የሚወጣው ይህ የህዝብ ደህንነት የሚገኝበትን ዘ
ዴ አምጡ፡ከስራ ላይ አውሉ በሚባልበት ጊዜ ነው።

እኛ በበኩላችን እላይ የተጠቀሱትን አላማዎች ከስራ ላይ አውሎ
ለህዝብ ደህንነት ለማስገኘት ሰራተኛውን ህዝብ እየዘረፈና እየጨቆነ ያ
ፈነውና አላራምድ ያለው የበሰበሰ ስርአት ተጠራርጎ መውደቅ አለበት
እንላለን።በሱ መቃብር ላይ የሰርቶ አዳሪውን ህዝብ ጥቅም የሚያረጋግ
ጥ የህዝብ መንግስት ካልተቋቋመ ምንም አይነት ደህንነት የለም ብለን
እናምናለን። ስለዚህ ከሁሉ አስቀድመን ስርአቱን ለመደምሰስ ህዝቡን
አደራጅቶ ለትግል ማሰለፍ ያስፈልጋል ባይ ነን።ለኢትዮጵያ ህዝብ ደህ
ንነትና እርምጃ የሚደረገው ማንኛውም ትግል በዝባዦቹን ከነግብረአ
በሮቻቸው፡ከነመንግስታቸው ከነስርአታቸው፡ከነአጥራ ባህላቸው፡ከነብል
ሹ ሞራላቸው እንዳሉ ጠራርጎና አስወግዶ አዲስ ኢትዮጵያ ለመመስ
ረት የሚደረግ ጠቅላላ ትግል መሆን እንደሚገባው አንጠራጠርም።

የባላባቱ መንግስት መሪዎችን አጫፋሪዎቻቸው በበኩላቸው እነ
ዚህን አላማዎች "በየልማት ደብተሮቻቸው" ውስጥ እየዘረዘሩ በያለበት
ይሰብኳቸዋል።"እነዚህ አላማዎች" "ተአምር መሰስ" በሆነ ፍጥነት ከስራ
ላይ በመዋል ላይ ናቸው እያሉ "በሬ ወለደን" ሊያሰምኑን ይቃጣቸዋል
በሚሊዮን የሚቆጠረውን ሰርቶ አደር ህዝብ አራቁተው አንድ ፎቅ በ
አዲስ አበባ ውስጥ በገተሩ ቁጥር «ተመልከቱ! ኢትዮጵያ ወደፊት በመ
ገስገስ ላይ ናት» ይሉናል።የአገሪቱን ሃብት አራግፈው እየሰጡና አራግ
ፈው ለመስጠት ቃልኪዳን እየገቡ አንድ "አይሮፕላን" በዱቤ ባስመጡ
ቁጥር ኢትዮጵያ "ሰለጠነች" ይሉናል።በእንደዚህ ያለው ጥረታቸው—ጠ
ቅላላውን ህዝብ እያደኸዩ በነሱ መብለጭለጭ—ቀስ በቀስ አላማዎቹን ሁ
ሉ ከስራ ላይ እንደሚያውሉ ሊያሳምኑን ይፈልጋሉ።ስለዚህ፡ሁሉ ቀስ
ብሎ የሚመጣ ጉዳይ በመሆኑ ስርአቱ ይከበር፡ፀጥታ ይጠበቅ፡ሰላም ይ
ሁን እያሉ ህዝቡን ከትግል ለማገድና ጨርሶ ለማስተኛት ይጣጣራሉ።

በነዚህ በሁለቱ መሀከል እንግዲህ ታሀሳሳዊያን አሉ።አንደኛ፡ስር
አቱ ተጠራርጎ መውደቅ አለበት፤ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ከኢ
ትዮጵያ ገዕ ካልጠፉ ምንም አይነት ስርየት የለም በማለት ተነስተው መ
ሰረታዊ ለውጥን እንደ "ቅዳሜዊ" ግብ አይወስዱም።እንደነአጅሬ ደግሞ



ሃገሪቱ ወደፊት በመገስገስ ላይ ነችና ምንም የሚለወጥ ነገር የለም የሚ
ሉ አድሀሪዎች አይደሉም።የኢትዮጵያ እርምጃ የተሰናከለው በአንዳን
ድ ብልሹ ባለስልጣኖች ብቁ አለመሆን፡ለተማሩት ወጣቶች ሀላፊነት በ
ለመስጠቱ . . . ወዘተ. ስለሚመስላቸው የአስተዳደር ዘዴው ቢሻሻል የ
ኢትዮጵያ ችግሮች ተፍታትተው ከላይ የተጠቀሱት አላማዎች በርግጥ
ከስራ ላይ ይውላሉ የሚል እምነት ነበራቸው።ለዚህም ለተወሰነ አላማ
ህዝቡን አንቀሳቅሶ ለትግል ማሰለፍ አስፈላጊም ሆኖ አይታያቸውም።የ
ሚቻልም፡የሚያዋጣም አልመሰላቸውም።ዝም ብሎ ደግሞ በየቦታው ቅ
ን አስተዳዳሪዎች ተሹመው አስተዳደሩ እስኪሻሻል ድረስ የንጉሰ ነገስ
ቱን ሹምሽር እጅ አጣጥፎ መጠበቅ አላስቻላቸውም።ስለዚህ አስፈላጊ
ነው ብለው ላመኑበት መሻሻል በሃይልና በድንገት ስልጣኑን ከአሮጌው
አገዛዝ ለመቀማትና በየቦታው የሚያስፈልገውን ሹምሽር ለማድረግ ተ
ነሱ።

ባጭሩ፡የታሀሳሳዊያን ዋና አላማ እርምጃ ቢሆንም፡የኢትዮጵያን
ህዝብ እርምጃ አፍኖ የያዘውን ዋናውን ጠር አላዩትም።እርግጥ እነሱ የ
ሚሉት የአስዳደር ጉድለት አለ። ግን ይህ ላይ ላዩን የሚታየው የአገዛ
ዙ መልክ እንጂ የስርአቱ መሰረት አልነበረም።አይደለምም።የኢትዮጵ
ያ ህዝብ ዋና ጠላት የባላባቶቹና አዲሱ የኢምፔሪያሊስቶች የዘረፋና
የጭቆና ስርአት ነው።ይህ እስካለ ድረስ የአስተዳደር ጉድለት የግድ ይ
ቀጥላል።ስርአቱ ከመሰረቱ ከተነቀለ ግን የአስተዳደር ጉድለትም አብሮ
ይደመሰሳል።

ስለዚህ ከባላባቶቹ የፖለቲካ ስልጣን ለመቀማት አስቀድሞ ሃይል
ና ሃብት የሰጣቸውንና ለፖለቲካ ስልጣናቸው መሰረት የሆነውን የዘረ
ፋ ስርአት ከስሩ ማናጋት ያስፈልግ ነበር።ለዚህም እንኳን ስልጣንን ከባ
ላባቶቹ መደብ ቀምቶ ወደህዝቡ ለማስተላለፍ ይቅርና በዚያው በገዥ
ው መደብ ውስጥ እንኳን ከአሮጌው አገዛዝ ወደአዳዲስ ሃይሎች ለማ
ሸጋገርም ቢሆን በመጠኑ የተደራጀና ረዘም ያለ ትግል አስፈላጊ እንደ
ነበረ ግልፅ ነው።የታሀሳሳዊያን ትግል ለጊዜው አሸንፎ አዲሱ የአገዛዝ
ዘዴ መጠነኛ እርምጃን ቢወስንም እንኳን ዞሮ ዞሮ የኢትዮጵያ ጠቅላላ
የፊውዳል ስርአት ሳይለውጥ፡ኢምፔሪያሊስቶች ከአገራችን ጓዛቸውን

ጠቅልለው ሳይወጡ፣የአድሃሪ ሃይሎች ስልጣን ሳይደመሰስ፡ህዝቡ በሙሉ በፖለቲካ ንቃቱ ዳብሮ በረጋሙና በመራራው ትግል ሳይሳተፍና ሳይፈተን ምንም አይነት ቋሚ ደህንነት እንደማይመጣ መታመን ያለበት ነገር ነው።

ታህሳሳዊያን ለዚህ አስፈላጊ ለሆነው ሪቮሉሽን ለመታገል በወጡበት መደባዊ አካባቢ መታነፃቸው፡በኢምፔሪሊስቶች የስልጣኔ ተፅእኖ መገረፋቸው፡በአከባቢያቸው የነበረው ሪቮሉሽናዊ ንቃት ዝቅተኛ እንደነበረ፡የፈለቀበት ህብረተሰባዊ ክፍል ጠጋኝ እንጅ ሪቮሉሽናዊ እንዳልነበረ ሲታወስ ለመሰረታዊ ለውጥ አለመነሳታቸውን መገመት አያዳግትም።የተነሱት ለጥገናዊ ለውጥ ነበር።ለዚሁ ለጥገናዊ ለውጥ እንኳን ህዝቡን ቀርቶ በአከባቢያቸው የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል በትግል ዘዴያቸው ውስጥ አለማስገባታቸው ሲታወቅ ሙከራቸው መክሸፉ ምንም የሚያስደንቅ አይደለም።

## የታህሳሶች የትግል ዘዴ

ማንኛውም የፖለቲካ ስልጣንን ለመያዝ የሚደረግ ሙከራ ከሁሉ አስቀድሞ ወዳጅን ከጠላት መለየት አለበት።ከሰቡት ግብ ለመድረስ ለለውጥ የተነሱ ሃይሎች በዚህ ለውጥ የሚጠቀሙትን ክፍሎች ጠንቅቀው ማወቅና እነዚህንም ክፍሎች ለመጭው ትግል ማዘጋጀትና ማደርጀት አለባቸው።በዚሁ አንፃር ደግሞ በህብረተሰቡ ውስጥ ባላቸው አቋምና ጥቅም ይህን ለውጥ የግድ የሚቃወሙትን ሃይሎች ፈልጎ ማግኘትና እነሱን ደግሞ መበታተን፡ማድከምና መደምሰስ ያስፈልጋል።

የታህሳሳዊያን ሙከራ ይህ አይነት የድርጅት ስልት አይታይበትም።ከፍ ብለን ስንፅፍ የታህሳሳዊያን ሙከራ ከጠላት ጊዜ ወዲህ በሃገሪቱ የፈለቁት አዳዲስ ሃይሎች የተነሱበት አመፅ ነው የሚል አስተሳሰብ ሰንዝረናል።ይህንን ማለታችን አመፁ ድልን ሲያገኝ ዞሮ ዞሮ ከሁሉ በፊት የሚረጋገጠው ስልጣንና የሚጠበቀው ጥቅም የነዚህ አዳዲስ ሃይሎች ነው ማለታችን እንጂ እነዚህ አዳዲስ ሃይሎች ተደራጅተው በሙሉ በንቅናቄው ተሳትፈዋል ለማለት አይደለም።እንዲያውም የታህሳሳዊያን ሙከራ ደካማ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ እነዚህን ክፍሎች አደራጅቶ ለትግል ማሰለፍ አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱና አለመቻሉም



ነው።በዚህ መስመር ሃገር ወዳዱ ገርማሜ ንዋይ ወጣቶችን በየምክንያቱ ለማደራጀትና የፖለቲካ ንቃታቸውን ቋሚ መልክ ለመስጠት ደጋግሞ መሞከሩንና ደጋግሞ የከሸፈበትና ተስፋ ያስቆረጠው መሆኑን መዘንጋት አይገባም።

ይህ ሙከራ ለምን እየደጋገመ ወደቀ? ብዙዎች የሰላዩ መብዛት፣ የአንዳንድ ወጣቶች እበላባይነት፡በጥቃቅኑ ነገር መከፋፈል...ወዘተ. ለዚህ ከሽፈት ምክንያት ናቸው ብለው ያትታሉ።ነገር ግን ይህ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም።ሰላዮችና እበላባዮች ወደፊትም ይኖራሉ።ግን እነዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ለለውጥ የሚያደርገውን ድርጅትና ትግል ዘልአለማቸውን ያደናቅፉታል ብሎ ለመቀበል የአድሃሪዎችን ደደብነት ይጠይቃል።

በበኩላችን አዳዲሶቹ ሃይሎች ለመደራጀት አለመቻላቸው በጠቅላላው የህብረተሰቡን የእድገት ደረጃ በሚወስኑ ምክንያቶች ነው ብለን እናምናለን።ህብረተሰቡ በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ ይገኝ ነበር።እነዚህ ክፍሎች ገና በፊውዳሉ ስርአት ውስጥ መፈልፈል የጀመሩ እንጂ አድገው የጨረሱ አልነበሩም።ስለዚህ በዚያን ዘመን እነዚህን ክፍሎች ከወለዳቸው ስርአት የሚያጣላቸውና አይንና አፈር የሚያደርጋቸው ከፍተኛ ልዩነት የለም ነበር።ለምሳሌ የተማሩት ወጣቶች ብንወስድ፡በመንግስቱ አስተዳደር ውስጥ ገና ቦታ በታቸውን መያዝ መጀመራቸው ነበር።በዚህም ጊዜ ለይስሙላ በተሰጣቸው ስልጣን አንዳንድ "ቴክኒካዊ" አገልግሎት እያበረከቱ ከእንግዲህ እርቃኑን ለመታየት ላፈረው በከት ስርአት ዘመናዊ መልክ ይሰጡ ነበር።ለዚህም አገልግሎታቸው በቂ ጉርሻ፡መሸንገያና "አስፈላጊው" ክብር ስለማይነፍጋቸው፤ባጭሩ፡ከዘረፋው ይገባናል የሚሉትን ድርሻቸውን ለማጉረስ ስርአቱ በቂ ችሎታ ስለነበረው አልፎ አልፎ በአፍ ቢኰንኑትም ከዚህ አሮጌ ስርአት ጋር በጥቅም በመተሳሰር ተቻችለው ይኖሩ ነበር።እደዚህ ከዘረፋው ተሳታፊ የሆኑትን ሃይሎች ከስርአቱ ጋር ምንም አይነት ጠብ ሳይኖራቸው በሙሉ "በሃገር ፍቅር" ወይም ደግሞ በሌላ "ስሜት" ብቻ ተነሳስተው መንግስትን ለመገልበጥ ይደራጃሉ ማለት ፍፁም አስቸጋሪ ነገር ነው።

ቢሆንም በዚህ ክፍል ውስጥ የለውጥ ፍላጐት አልነበረም ማለት

አይቻልም።አንዳንዶቹ በሃገር ፍቅር ስሜት በመነሳሳት፡በሃገራቸው ከአ
ካባቢው አለም ወደኋላ መጐተት በመቆርቆር እርምጃዋን የሚያፋጥን
ለውጥ ይሹ ነበር።አንዳንዶቹ ደግሞ እድገታቸው በቀንዳሞቹ ባላባቶች
የተገታ መሆኑ ስለሚሰማቸው የነሱን ጥቅም በይበልጥ የሚያረጋግጥ
አዲስ የአገዛዝ ዘዴ እንዲቆም ፍላጐታቸው ነበር።የቀሩት ደግሞ በመ
በስበስ ላይ ያለው ስርአት አንዳንድ ጥቃቅን ለውጦችን ካላደረገ ተንከ
ታኩቶ ይወድቃል በሚል ፍርሃት ተገፋፍተው መሻሻልን ይደግፉ ነበር።

ነገር ግን በዚህ ጊዜ እርምጃን የሚመኙ ሃይሎች ከአሮጌው አገ
ዛዝ የከረረ ጠብ ስላልነበራቸው፡እነሱም ራሳቸው ገና ያልጠነከሩ ስለነበ
ሩ ይህ በአየሩ ላይ ያንዣብብ የነበረው የለውጥ ጉጉት በደንብ ሊቀናበ
ር አልቻለም።ስለዚህም ሀገረ-ወዳድ ግንባር ቀደሞች ከሰፊው ህዝብ ይ
ቅርና ከወጡበት የህብረተሰብ ክፍል እንኳን ሳይዋሀዱ ለብቻቸው ተወ
ርውረው የተደራጀውን አድሃሪ ስርአት ለመቋቋም ቆረጡ።

ይህንንም ለማድረግ በወሰኑበት ወቅት የታህሳሳዊያንን የፖለቲ
ካ እርምጃዎች ያደናቀፉ ብዙ "ቅን" አስተሳሰቦች ነበሩ።በከተማው፡በአ
ካባቢው የአፍሪካ አገሮች በሚነፍሰው የለውጥ ንፋስ በመመካት፡በግባ
ቸው ትክክለኛነት በመተማመን፡"እንጀምረውና ሁሉም ይከተለናል" በ
ሚል የተሳሳተ አስተያየት በመመራት፡ዞሮ ዞሮ ደግሞ በአላማቸው የባ
ላባቱን ስርአት ቋሚ ጥቅም ለመንካት ምንም ሀሳብ ስላልነበራቸው ለ
ውጡ በሰላምና በአንድ ጊዜ ይደረጋል የሚል ግምት ላይ ወደቁ።ያል
ተደራጀ ትግላቸው መጀመሪያውኑ ደካማነት ነበረው።በዚያውም ደካማ
ሃይላቸው አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ በሚገባ ባለመጠቀማቸው ታህሳሳዊ
ያን የመነመነ እድላቸውን የባሰውን አወደሙት።

አንዳንዶች ይህን በሃይል አለመጠቀም ጉዳይ የሙከራው መክሸ
ፍ ዋና ምክንያት አድርገው ይቆጥሩታል።እርግጥ አንድን ስርአት ከመ
ሰረቱ አናግቶ በሌላ በአዲስ ስርአት ለመተካት የትም ቦታ፡ምንጊዜም፡
የተደራጀና ረጋም የህዝብ አመፅና ትግል ያስፈልጋል።ግን ታህሳሳዊያ
ን ያቀዱት አላማ የ"ጥገናዊ ለውጥ" መሆኑን ስንረዳው ሙከራቸው ያ
ለ"መራራ"ትግል ሊከናወን ይችል እንደነበረ መርሳት አይገባም።ባሉበ
ት አካባቢ ሲታይ በሃይል መጠቀማቸው ብቻ ለድላቸው ምንም ዋስት



ና አልነበረም።ለጊዜው በወታደሩ ድጋፍ ቢያሸንፉም ኖሮ ያልተደራጀ
ሃይላቸውንና የተበታተነ ድጋፋቸውን ለመደምሰስ አድሀሪዎቹና ኢም
ፔሪያሊስቶች በሃገሪቱ ገና በቂ ሃይል ነበራቸው።ክላፓም የተባለ ፀሀፊ
በዚህ ጉዳይ ሲያትት እንዲህ ብሏል።«ለጊዜው በወታደሩ በኩል ያጋጠ
ማቸውን ችግር ቢወጡት እንኳን የግዳቸውን ሪቮሉሽን በማይቻልበት
የሶሻልና የፖለቲካ አከባቢ ውስጥ መግባታቸው አይቀርም ነበር»።* ይህ
አስተያየት ከሞላ ጐደል ትክክል ሲሆን «ሪቮሉሽን በማይቻልበት» ከማ
ለት ፈንታ «ሪቮሉሽን የሚያስፈልግበት የሶሻልና የፖለቲካ አካባቢ»
ቢለው ይበልጥ እውነት ይሆናል ብለን እናምናለን።

ታህሳሳዊያን በተነሱበት ጊዜ አንዳንድ የስራ ፕሮግራሞችን ማወ
ጃቸው ይታወሳል።እድል ቢያገኙ ኖሮ እነዚህን እቅዶች በተግባር ላይ ለ
ማዋል መቃጣታቸው አይቀርም ነበር ብለን እንገምታለን።በዚህን ጊዜ
መሰረቱ ያልፈለሰው፡በያለበት ተንዘራጥጦ የሚገኘው ባላባታዊ ክፍል
ዝም ብሎ ይመለከታቸው ይሆንን?አይመስለንም፤መከላከሉና ኢምፔሪ
ያሊዝምም እነሱን ከለላ አድርጐ መታገሉ አይቀርም ነበር።እንግዲህ ታ
ህሳሳዊያን በአንደበታቸው ለሰነዘሯቸው እቅዶች እስከመጨረሻው ለመ
ታገል ከቆረጡ የግድ ፊታቸውን ወደህዝቡ መመለስ ይኖርባቸው ነበር
ማለት ነው?ግን የትኛው ህዝብ?

ስለታህሳሳዊያን አወዳደቅ በተነሳ ቁጥር ተደጋግሞ የሚመጣ አን
ድ ጥያቄ አለ።ህዝቡ ለምን አልተነሳም?ታህሳሳዊያን ራሳቸው በጠላት
አውሮፕላንና ታንክ በተያዙበት ጊዜ፡ሊረዷት የተነሱት ህዝብ፡ሊደርስ
ላቸው አንዲት ድንጋይ እንኳን አለማንሳቱ አስገርሟቸው ይሆን?

ግን እኮ እንዲህ አይነቱ ሙከራ በአንድ መደብ ውስጥ ያሉትን ክ
ፍሎች የርስ በርስ መገለባበጥ የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ የህዝቡን ተ
ሳታፊነት እንብዛም አይጠቅምም።አላማው በገጋው መደብ ውስጥ ጠ
ለቅ ያለ ሹም ሽር ለማድረግ ስለሆነ፡ሙከራው በውስጡ ጠባይ በምስጢ
ር በተወሰነ የስራ አቅድና በተወሰኑ ታጋዮች መሃከል የሚያልቅ ጉዳይ

* JOURNAL OF MODERN AFRICAN STUDIES
The Ethiopian Coup D'Etat of December 1960
C. CLAPHAM p. 506

ነው።ስለዚህ ታህሳሳዊያን ህዝቡን ለማንቀሳቀስ፡ለማደራጀትና ከትግሉ ውስጥ ለማስገባት ምንም በቂ ሙከራ አላደረጉም።ታዲያስ ህዝቡ ማን ብሎ፡ምን ብሎ ይነሳ?በይትኛውስ ድርጅቱ አማካይነት ይነሳ?ህዝብ ለማስነሳት ህዝብን አስቀድሞ ማደራጀት የግድ ያስፈልጋል።

## መደምደሚያ

ከላይ እንደጠቀስነው ለማንኛውም ህብረተሰብ ክፍል ጥቅም ተብሎ የሚደረግ ለውጥ በዚያው በተጠቃሚው ክፍል የተደራጀ ትግል እንጂ በጥቂት ሰዎች ብርታት የሚገኝ ስጦታ አይደለም ብለናል።የታህሳሳዊያን ሙከራ መክሸፍ የሚሰጠን አንዱ ትምህርት ይህ ነው።ስለዚህ እኛ የህዝቡን ወገን የመረጥን፡ለህዝቡ የሚጠቅም ለውጥ የምንሻ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ጀግኖቹ ታህሳሳዊያን ከወደቁበት ወጥመድ መግባት የለብንም።ለህዝብ አዲስ ኑሮ ሊገኝ የሚችለው ህዝቡ ራሱ በፖለቲካ እውቀቱ ዳብሮና ከነጋየው መደብ ጋር በሚያደርገው ትግል በገዛ መሬዎቹ እየተመራ፡በገዛ የስራ ትልሙ ተሰልፎ ለረጅም ጊዜ ተናንቆ ጠላቶቹን እንዳሉ ሲደመስስ መሆኑን አምነን በዚህ መንፈስ መነሳት ይገባናል።

ህዝብን እንደዚህ ለማነሳሳት ደግሞ ተበድለሃል ብሎ ለማስቆጣት መሞከሩ ብቻ ዘላቂ ውጤት እንደማይሰጥ መረዳት ይገባናል።ነፃ ትወጣለህ፡መሬት ይሰጥሃል፡ስራ ታገኛለህ፡ግፍ ይቀራል፡ጭቆና ይሰረዛል፡የሚል ተስፋም እየሰነዘሩ ማንቀላለጩ ብቻውን ምንም ያህል አያዋጣም። ይህ ሁሉ የሚገኘው ከሚፃረሩ ፀረ ህዝብ ሃይሎች ጋር መራራ ትግል ከደረጉ በኋላ መሆኑን ደጋግሞ መግለፅ ያስፈልጋል።የድሉም ዋና ዋስትና የራሱ የህዝቡ ሃይል ብርታት መሆኑን ሳይሰለቹ መንገር ያስፈልጋል።ስለዚህ ግንባር ቀደም ሆነው አንድን ህዝብ ለነፃነት ትግል እናሰልፋለን የሚሉ ሃይሎች የሚያወጡትን አላማ ከስራ ላይ ለማዋል፡የቀሰቀሱትን የህዝብ ቁጣ የትግል ሞተር ለማድረግ፡ያስነሱትን የነፃነት ተስፋ ከግቡ ለማድረስ ከተጠቃሚው ህዝብ መማር፡ተጠቃሚውን ህዝብ ማስተማርና ማደራጀት አለባቸው።በእውነት ለህዝብ አለኝታ የሆነ አላማ የጊዜውን የተደራጁ ወንበዴዎችና ዘራፊዎች ጥቅም ስለሚነካ ከያለበት



ታላቅ ተቃውሞ ያጋጥመዋል።እነዚህ ፀረህዝብ ሃይሎች ጥቅማቸውን ለመጠበቅ ለምንም አይመለሱም።ይህን ጊዜ ለተራማጁ ወገን የሚቀረው የማይበገር ተገን ተጋዳዩ ተበዝባዥ ብቻ ነው።ነገር ግን ለዚህ፡ለትግል ህዝቡ ሆን ብሎ ካልተደራጀና ወድቆ እየተነሳ ካልተፈተነ ምንም የድል ዋስትና የለውም።

ታህሳሳዊያንን አስቆጥተው ያስነሷቸው ህዝቡን ያሰቃዩትና ያጐሰቆሉት የነበሩት የኑሮው ነቀርሳዎች ዛሬም አሉ።እንዲያውም ከመቻውም ብሰዋል።ይህ አቋም ተደምስሶ የኢትዮጵያ ህዝብ አዲስ የነፃነት ኑሮውን እስኪጀምር ድረስ ታህሳሳዊያን፡ከነሱም በፊት ሆነ ከነሱም በኋላ ሃገራችን ደጋግማ ያፈራቻቸውን ጀግኖች የጫሩት የትግል ፋና እንደበራ ይቆያል።ሌሎች ብዙ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ከጉድለታቸው በመማር፡ከድፍረታቸው አርአያነት በመቀበል፡ከመስዋእትነታቸው ባለአደራነትን በመውረስ፡ትግላቸውን በአዲስ መንፈስ፡በአዲስ እምነት፡በአዲስ ዘዴ እስከመጨረሻው ይቀጥሉታል።ህልማቸው አልተፈፀመም እንጂ አልሞተም።ለጊዜው መሸነፋቸው የህዝብ ጠላቶች የዘልአለም ድል አይደለም።ሊሆንም አይችልም።

## የ5 ታህሳስ 1953 የመንግስት ግልበጣ

### ሙከራ ዝርዝርዜና(1)

በታህሳስ ወር መጀመርያው ሳምንት፣ሃይለስላሴ፣ምእራብ አፍሪቃንና ብ
ራዚልን ለመጎብኘት፣ከአዲስ አበባ ወጥቶ ሄዶ ነበር።የግልበጣው ሙከራ
የተከናወነው ያኔ ነው።«ሃይለስላሴ ብራዚል እንደደረሰ»፣አለ "ታይም"
የተባለው የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ልሳን፣በ26 ታህሳስ 1960 ባወጣ
ው ቁጥሩ፣«የወርቅ እንክብልና የ200 ዶላር(የ500 የኢትጵያ ብር) ጉር
ሻ ሲነሰንስ የመንግስቱ መገልበጥ ተነገረው።»

13 ታህሳስ 1960፤ ማታ፣የክብር ዘበኛ ከፍተኛና መከከለኛ መኮንኖች
እየተላኩና በስልክም ጭምር፣«እቴጌይቱ ታማለችና በነፍስ ድረ
ሱ» እየተባሉ፣መሳፍንቱና መኳንንቱ ወደላይ ግቢ እንዲሄዱ ተ
ደረገ።"ቀንደኞቹ" በንደዚህ ከተያዙ በኋላ፣በአዲስ አበባ ጊዜ አቆ
ጣጠር፣ከምሽቱ 4 ሰአት ጀምሮ፣የዘመኑ "የኢትዮጵያ መንግስት ባ
ንክ"፣የስልክ ዋና ማዞሪያና ጠቅላላው የቴሌኮሙኒኬሽን አውታ
ር፣ራዲዮ ጣቢያው፣አይሮፕላን ማረፊያው፣ሰስቱም ግቢዎችና የከ
ተማይቱ አውራ መዳረሻዎች በክብር ዘበኞች ተያዙ።የድሮው አ
ርበኛ የጊዚው አድህሪ፣የአበበ አረጋይ ሚስት፣ቆንጅት አብነት፣የበ
ኋ ወጥቶ መቅረት ስላሳሰባት፣ወደስጋ ዘመዷ፣ወደመርእድ መንገ
ሻ ደውላ፣እንዲያጠያይቅላት ለመነችው።መርእድ፣"ነገሩ ስላላማረ
ው" —ጊዜው ሌሊት ነበርና—ወደጊዜው የምድር ጦር አዛዥ፣ወ
ታከበደ ገብሬ ሄዶ ቀስቀሰና ወደአንደኛ ክፍለ–ጦር(መሻሎኪያ)
ወሰደው።እዚህም መሽጉ።የመሻሎኪያ ጠቃሚነት የቱን ያህል እ
ንደሆነ ለማንም አይሳትም።ለገሀሩና አየር ጣቢያው በቅርቡ ይገኛ
ሉ።መድፈኛውና ታንከኛው ጦር በዙርያ ጥምጥም መንገድ ሊገ
ናኝ ይችላል።የአዲስ አበባን የስንቅና የሸቀጥ መግቢያ በር ለመቆ
ጣጠር ወይም በመዝጋት ለያገርው እጅግ ምቹ ነው።ከዚህም በቀ
ር፣አየር ሃይሉን ቢያስፈልግ አስከብቦ ለማስገደድ፣ከሀረሩ የምስራ

(1) ቁጥር ለተደረገባቸው ሁሉ በፅሁፉ መጨረሻ ማብራሪያ ይሰጣል።



ቅ ጦር የሚመጣ ተደራቢ ሰራዊት ቢኖር ደግሞ ከላንዳች አከል
ወደአዲስ አበባ ለማስገባት ቦታው የተመቸ ነው።በጭሩ እንዳጋ
ጣሚ ሆኖ ስሙ እንደሚያመለክተው፣"መሻሎኪያ" ከአዲስ አበባ
ስትራቴጂያዊ ቦታዎች አንዱ ነው።ያም ሆነ ይህ፣የራስ አበበ ሚስ
ት መርእድን ከስጠነቀቀች በኋላ፣ሳይቆረጡ ቀርተው የነበሩት የአ
ዲስ አበባ የስልክ መስመሮች ሁሉ በድን ሆኑ።አጨናጋፊዎች የ
አበበ አረጋይን ስልክ ሆነ ብለው ትተውት ይሆን? ጉዳዩ አሁንም
ስንግ ነገር ነው።ራስ አበበን በፀረፋሺስት ትግል ጊዜ በጠላትነት፣
በኋላ ደግሞ በወዳጅነት አውቀው ነበር የሚለው ኢጣሊያዊ ጋዜ
ጠኛ፣ኢንድሮ ሞንታኔሊ፣በ"ኮሬራ ዴላ ሴራ" (የረቡእ 21 ታህሳስ
1960) ይኸን ነጥብ ደህና አድርጐ ነው ያብራራው።"ጆርናል ኦፍ
ከረንት ሂስትሪ" የሚባለው የአሜሪካን የምሁራን መፅሄት ደ፡ግሞ
ጠቅላላ ምስጢሩ እ.አ.አ. በ1980 ዓ.ም. በዋሽንግተኑ የውጭ ጉ
ዳይ ሚኒስቴር ታትሞ እንዲገለፅ፣ፀፎ ነበር።(2)

—በዚሁ እለት ማታ፣ከምሽቱ ሰስት ሰአት:አንድ የክብር ዘበኛ መ
ኮንን:የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ማደርያ ቤት ድረስ ሄዶ፣ለውጥ መደ
ረጉን ከገለፀላቸው በኋላ:ተማሪዎቹ መሬ-ቃልና ሰሌዳ ሲያዘጋ
ጁ አደ፦።

14 ታህሳስ፤ በረፋድ

በዋዜማው ያልተያዙት ሚኒስትሮችና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣኖ
ች "ወደስራቸው" ሲሄዱ:ሀንፃዎችን የያዙት ክብርዘበኞች: አናስገ
ባም እያሉ የመለሱዋቸው አሉ፤በገዛ መኪኖቻቸው ወደክብር ዘበ
ኛ ጠቅላይ መምርያ የተወሰዱም አሉ ። የከተማው ህዝብ፣በየቦታ
ው መትረየስ ተደግኖ በማየቱ ግር ቢለውም፣በመጠያየቅ ከመዋ
ዠቅ በቀር ነገሩን በደንብ አላጤነውም።በዛን ሰአት ሰስት ግምቶ
ች ነበሩ የተሰነዘሩት።እነሱም፣1ኛ) እቴጌይቱ ወትሮም በሽተኛ ስ
ለሆነች ሞታለች፤2ኛ) ጦርሰራዊት መንግስት ለመገልበጥ ተነስቷ
ል ስለተባለ ክብርዘበኛ አጨናገፈበት፤3ኛ) ራስ አበበ ሊነግስ ሰራ
ዊቱን አሳመፀ የሚሉ ነበሩ።

—ከጠዋቱ ሰስት ሰአት ተኩል ጀምሮ፣አንዲት የፕሮፓጋንዳ ባለ

ድምፅ ማጉሊያ መኪና፣ሰፈር ለሰፈር፣መንገድ ለመንገድ እየዞ
ረች፣ህዝብ ራድዮውን ከፍቶ እንዲያዳምጥ ጋበዘች።ልክ አራት
ሰአት ከ5 ደቂቃ ሲሆን፣አልጋ ወራሹ፣አዋጁን አነበበ።

—የዚያኑ ሰአት የሲ.ቢ.ል አቢያሲዮን አስተዳዳሪ፣አበተ አግዴ፣ድ
ርጅቱ በነበረው ራድዮ፣የደረሰውን ድንገት ለሃይለስላሴ ለማር
ዳት ሞክሮ ነበር።መልክቱ ይድረስለት አይድረስለት ግን አልታ
ወቀም።የጥሪ ምልክቱ ኢ.ቲ.3 ኤክስ ዋይ የሆነ የግል መቀበ
ያና መላኪያ ራድዮ የነበረው ማንነቱ ያልታወቀ ሰው፣በ15 ሜ
ትርባንድ፣ከአዲስ አበባ ስድስት ጊዜ በእንግሊዝኛ መልክት አ
ስተላለፈ።መልክቱም፣«ለንጉሱ መልክቴን ያደረሰ ሰው፣አገሪቱ
ን ከመአት ያድናታል» የሚል ነበር።በጭማሪም ላዳማጮቹ(መ
ልክቱ የተሰጠው ኬንት፣ለንደን ነው ይበላል።) «ጉዳዩን ለእስ
ራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ንገሩልኝና እሱ ለንጉሱ ያስታ
ውቅልኝ» ሲል አሳሰባቸው።እንደዚህ አይነቱ መቀበያና መላ
ኪያ ራዲዮ የነበረው፣የንጉሱ ልጅ ሳህለስላሴ ብቻ ስለነበረ፣እሱ
ሳይሆን አይቀርም መልክቱን ያስተላለፈው የሚሉ አሉ።ነገር
ግን ከሳህለ ስላሴ ውጭ፣እስራኤላዊም ሌላም በእድ ሊሆን ይ
ችላል።ይኸ የሚያሳየን፣አገራችን የአድፋጮች፣የአጨናጋፊዎ
ችና የሰላዮች ዋሻ መሆኗን ነው።መልክት አስተላላፊው እንዲ
ያ የተጣደፈበት ምክንያት፣እንደዚያ ያለ መሳርያ ያላቸው ሰዎ
ች ሁሉ እንዲያስረክቡ ተደጋግሞ በራድዮ ታዝዞ ስለነበረ ነው።
ከዚህ በኋላ አሳባቂው ራድዮውን ዘጋ።

—እኩለ-ቀን ላይ ሃይለስላሴ ብራዚል ገባ።

—በነዚያ ቀኖች፣የራድዮ ጣብያው አዛዥ ሻቄ ጀግና፣ሻለቃ ዮሀን
ስ ምስክር ነበር።ለህዝቡ የተሰሙት ሀተታዎች ሁለት መልክ ነ
በራቸው፤አንደኛው ጦር ሃይሎችን ማነቃቃት፤ሌላው ደግሞ ለ
ሰላማዊው ህዝብ አዲሱን ሁኔታ ማብራራት።እኩለ ቀን ላይ፣የ
አዲሱ "መንግስት" መግለጫ ተነበበ።ቀጥሎም፣የወታደር ደመ
ወዝ ወደአርባ ብር ማደጉ ተነገረ።ስምንት ሰአት ላይ፣ለውጭ
አገሮች አምባሳደሮች፣ሚኒስትሮችና ቆንሲሎች "በሰላም የመ



ንግስት ለውጥ" መደረጉን የሚያበስራቸው መግለጫ ተደጋግ
ሞ ተሰማ።ከዚያ ቀደም ብሎ፣የዚያኑ ጊዜ ምክትል የውጭ ጉ
ዳይ ሚኒስትር፣ዶክቶር ጕይተአም ጴጥሮስ፣የውጭ አገር መልክ
ተኞቹን እየተቀበለ፣ለውጡን አበስሯቸው ነበር።መንግስታዊ
ውን መግለጫ የፈረመው ግን ዳዊት ዑቅባግዚ ነበር።ዳዊት ዑ
ቅባግዚ በዚያኑ ሰሞን ተገድሏል።እንዴት እንደሞተ ግን በትክ
ክል አይታወቅም።ብዙው ሰው የሚያወራው ከመሳፍቱና ከመ
ኳንንቱ ጋር አብሮ መረሸኑን ነው።

—በዚያን ሰአት፣በስዊድን ሚኒስትር የነበሩት አቶ ተፈሪ ሻረው፣
በኢምባሲው ህንፃ ውስጥ ግብዣ አድርገው፣"ነፃነት፣ዴሞክራሲ
ና አርነት ለዘላለም ይኑሩ!" ሲሉ ከዲሱ መንግስት ጋር መሰለ
ፋቸውን ለአለም ጋዜጠኞች አስታቁ።በያገሩ ከነበሩት አምባሳ
ደሮች ውስጥ እሳቸው ብቻ ናቸው በግልፅና በማያዳግም አኳ
ኋን አዲሱን መንግስት የደገፉት።

15 ታህሳስ፤ ተደርጎ የማይታወቀውን፣ራድዮ ጣቢያው፣ረቡእ እለት፣
15 ሰአት ከ20 ደቂቃ አስተላለፈ።እኩለ ቀን ላይ አዲሱ መንግስ
ት ሹምሽር አድርጎ፣ራስ እምሩ ሃይለስላሴ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ሜ
ጀር ጀነራል ሙሉጌታ ቡሊ፣የጦር ሃይሎች ጠቅላይ መምርያ ሹ
ም ተባሉ።

—ሃይለስላሴ ብራዚልን መልቀቁ ተሰማ።ስለዚህ ማናቸውም ለማ
ረፍ የሚሞክር በራሪ የሚተኰስበት መሆኑን የሚገልፅ ማስጠ
ንቀቅያ ተደጋግሞ ተላለፈ።የጕሬው አየር ጣቢያ በኢትዮጵያ
አየር መንገድ ሰራተኞች ብርታት በበርሜል፣ድንጋይና በሌላም
አይነት ቀራቅንበ ተዘጋ።

—አቶ ተፍሪ ሸረው ደጋፊነታቸውን በአፊሴል ለዳዊት ኡቅባግ
ዚ አስታወቁ።

—የኰሌጅ ተማሪዎች፣"ባዲሱ መንግስት እንርጋ፣ኢትዮጵያ የጠ
በቀችው ቀን መጣላት"፣ወዘተረፈ የሚሉ መሪ ቃሎች የተፃፉ
ባቸውን ሰሌዳዎች ተሸክመው፣በሰልፍ እነመርአድ መንገሻና
ከበደ ገብሬ ወደመሸጉበት ወደአንደኛ ክፍለጦር አመሩ።

—"የኢትዮጵያ ጠቅላይ ገዥ" የሚል ቅፅል ስም ተሰጥቶት የነበ
ረው የያንኪው አምባሳደር፣አርሰር ኤል. ሪቻርድስ በ"አስታራቂ
ነት" ወደክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያና ወደአንደኛ ክፍለጦር
ውር ውር ይል ነበር።ተግባሩ፣ለንመርእድ ጊዜ መስጠትና የክብ
ር ዘበኞቹ የከተማ አያያዝና ታክቲክ ምንአይነት እንደነበረ መ
ሰለል ነበር።እውነትም ተግባሩ ተሳክለት . . . ።

—ከቀትር በኋላ የሃይሉ ሚዛን ወደአድሀሪው ወገን አዘነበለ።

—በጄኔራል ፅጌ ዲቡ፣የፖሊስ ኰሚሽነር ቁጥጥር ስር የነበረው የ
ፈጥኖ ደራሽ ሻለቃ አዛጋር፣ኰሎኔል የበኋላው ጄኔራል ታደሰ
ብሩ፣አየር ጣቢያውን ይጠብቁ ለነበሩት ክብርዘበኞች ተደራቢ
ጦር ያመጣ መስሎ፣ማረካቸውና ለንመርእድ ገባ።

—በኤርትራ የሃይለስላሴ እንደራሴ የነበረው፣ያሁኑ የህግ መወሰኛ
ምክርቤት ፕሬዚዴንት ጄኔራል አቢይ አበበ፣በክብር ዘበኞች ባ
ልደረቦች ዘንድ ሽብርና ጥርጣሬን ለማሳደር ከአስመራው የአ
የር ሃይል ሰፈር ሁለት "ጄት" አይሮፕላኖችን ልኰ፣በዝቅታ በአ
ዲስ አበባ ላይ ከማስበረሩም ሌላ፣"ጃንሆይ መጡ" የሚል ማደ
ናገርያ ወሬ የያዙ ተባራሪ ቅጠሎች አስበተነ።በዚህ ረገድ የመ
ገናኛ ጣቢያ ሆኖ የተጠቀመው አየር ጣቢያ ላይ ተገትሮ የነበ
ረው ዲ–ሲ–6 አይሮፕላን ነው።

—ሰላማዊ ህዝብ ከመንገድ እንዲርቅ "አዲሱ መንግስት" በራዲ
ዮ አማካይነት አዘዘ።ክብር ዘበኛ ወደአዲስ አበባ ደቡብ ገፋ።መ
ርእድ መንገሻና ከበደ ገብሬ ከሹመትና ማእርጋቸው ተሻሩ።ይ
ኸንኑም ለኢትዮጵያ ህዝብ ያበሰረው፣ከመስፍን ስለሺ ልጅ፣ከ
ጃራ ጋር በኢትዮጵያ ሆቴል ተታኩሶ የሞተው፣ጠበቃው አሰፋ
ዱላ ነበር።ቀጥሎም፣"መኪኖቻቸውን እንደ ገላቸው ሽሚዝ የ
ሚቀያይሩ ከሀድያን" የሚል መግለጫ በራዲዮ አሰማ።

—በዘጠኝ ተኩል፣በመከላከያ ሚኒስቴርና በገብረማርያም ትምህር
ት ቤት መከከል፣ከቡር ዘበኞችና ጦር ሰራዊት ተታኩሱ።ክብር
ዘበኞቹ፣እየገፉ የመጡባቸውን የጦር ሰራዊት ባልደርቦች በተ
ራቸው ገፍተው፣መከላከያ ሚኒስቴር አደረሷቸው።ብዙ ተኩስ



ና ብዙ እልቂት የደረሰው በዚያው ግድም ነው።ይኸ ሁሉ ሲሆ
ን ግን ቸርችል ጐዳና አፋፍ ላይ፣ፈረንሳይ ባንክ ቅጥር ግቢ ው
ስጥ፣መሽገው የነበሩትና ልክ አንደኛው የትራፊክ መብራት ስ
ር አፈሙዛቸውን ወደለገሀር አቅጣጫ ደግነው የነበሩት ሁለት
ታንኮች አንዴም እንኳን አልተኰሱም።በጦር አይን ሲታይ፣እ
ነዚህ ታንኮች ለእግረኛው መከታ ሆነው ቢሳተፉ ኖሮ፣በመከላ
ከያ ሚኒስቴር መሽጐ የነበረው ጥቂት ጦር ሰራዊት እጁን በሰ
ጠ ነበር።ደግሞም፣በ"አበ ሰጡኝ" የሁለቱም ተፃራሪ ሃይሎች የ
ይዞታ ክልል ሆኖ የነበረው የአድዋ አደባባይ መታለፍ፣በአድ
ሀሪው ጦር ላይ የሞራል ድልን ባስገኘ ነበር።በዚህን ጊዜ ሁሉ
"ታማኞቹ" ከሀረር ተደራቢ ጦር ገና አልመጣላቸውም ነበር።የ
ድሉ ሚዛን ወደማን እንደሚያደላ ገና አልታወቀም ነበር።እስ
ከዚህች ሰአት ድረስ የሃይል ሚዛን ያልነው የመንፈስ ጉዳይ ብ
ቻ ነበር።ተጨባጩ ሁኔታማ ለነመንግስቱ ነበር ምቹነቱ።

—የሆለታ የጦር ትምህርት ቤትና የሀረር አካደሚ እጩ መኰን
ኖች፣አለቆቻቸውና አሰልጣኞቻቸውን አስረው፣ከአዲሱ መንግ
ስት ጋር መደባለቃቸው በራዲዮ ተነገረ።

—ህዝቡን ለማረጋጋትና የጦር ሰራዊቱን ለማደናገር፣"ሁለቱም ጥ
ለኛ ወገኖች ጠባቸውን አቁመው በአዲሱ መንግስት መርሃ መ
ሰረት ተባብረው ለመስራት ወስነዋል።ተኩሱም በቅርቡ አንዲ
ቆም ተስፋ ይደረጋል" የሚል መልክት በራዲዮ ተሰማ።

—በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ጦርነቱ ተባባሰ።በሀረር ከሰፈረው የ
ምስራቅ ጦር፣ብዙ ወታደር በንጉሱ አማች፣በመቶ አለቃ ደረጀ
ሃይለማርያም መሪነት ደርሶ፣አንደኛውን ክፍለጦር፣መድፈኛው
ንና ታንከኛውን ሻለቃ አጠነከረ።የክብር ዘበኛ ዋና ገድጋጅ ጠ
ር እንዲሆን ተመድቦ፣በእስጢፋኖስ ቤተስኪያን በኩል ታቹን
አልፎ፣በአንደኛ ክፍለጦር አካባቢ በጀግንነት ከተዋጋ በኋላ፣ተ
ደራቢም ደጀንም ስላጣ በሃይል ተጠቅቶ ተበታተነ።በግንባር ቀ
ደምነት ዋናውን መተላለፊያ ገድግዶ እንዲዝ የተመደበው ይ
ህ ጦር ስለነበር፣ይህ ጦር እንደተፈታ፣ጦር ሰራዊት እየገፋ ወ

ደሰሜን(አራዳ) እና ምእራብ(አዲስ ከተማ) በኩል መጣ።ሰአ
ቱ፡ከምሽቱ 11 እና 12 መካከል ነበር።(3) በዚህን ጊዜ ሁሉ
የፖሊስ ሰራዊት በምንም ለማንም አልተሳተፈም።በግርግሩ ሰ
ቢያ ወደየቤቱ የሄደው የክብር ዘበኛና የፖሊስ ሰራዊት ባልደ
ረባ ብዙ ነበር።ይኸን ጊዜ ነው እንግዲህ፡ተጨባጩ ሁኔታ ለአ
ድሃሪው ወገን የተመቸው።ወድያውኑ፡ከተከላካይነት ወደአጥቂ
ነት ተሸጋገረ።በዚሁ መጠን ደግሞ፡የክብር ዘበኛው ጦር ቅስም
እየተሰበረ ሄደ።

—የጦር ሁናቴውን ከቁጥጥሩ ስር የከተተው አድሀሪው ሃይል፡በ
ጨርቆስ ቀበሌ ያለውን የኤሌክትሪክ ሃይል ቆረጠ።ራዲዮው ቆ
መ።ነገር ግን የራዲዮ ጣቢያው ሰራተኞች፡ባጠገባቸው የነበረው
ን ረዳት ዲዜል ኤሌክትሪክ አንቀሳቃሽ ሞተር አስነስተው ፕሮ
ግራሙን ቀጠሉ።የኤሌክትሪክ ራዲዮ የነበረው ህዝብ ለመስማ
ት አልቻለም ኩሬንቲ ስላልነበረ በከተማው።ጦር ሰራዊቱ፡በዚ
ህ አኳኋን፡ሳይኮሎጂያዊ ዘመቻውን ጀመረ።

—ከዚህ በፊት ግን፡ፓትሪያርኩ ባሲልዮስ፡የሃይለስላሴን ጦር የወ
ጋ "ውጉዝ ከመአርዮስ ይሁን" ብሎ ስለገዘተ የክብር ዘበኛው
ጦር በዚህና በሃይል ሚዛኑ መከንበል ምክንያት እየተንጠባጠ
በ ይበታተን ጀመር።ማለት፡ልክ ክህናቱ እንዳስተማሩት ከስጋ
ው ነፍሱን መረጠ! ሆኖም፡እዚህ ላይ መዘለል የማይገባው ነጥ
ብ አለ።በኢትዮጵያ ታሪክ—የዱሮውም ያሁኑም— ለመጀመ
ርያ ጊዜ የቤተክህነቱ ግዙፋን በራዲዮ በይፋ ተዘለፉ።ተቺው፡
የቤተክሊያኒቱን ልኡላን ከመርአድና ከከበደ ጋር እያመሳሰለ፡
"ሀብት እያከማቹ፡ቤት እያከራዩ ህዝቡን ያሞኙታል" እያለ አ
ጋለጣቸው።

—11 ሰአት ላይ የነፋስ ስልኩ(የጅማ በር) ማስተላለፊያ ጣቢያ ስ
ለተመታ ራዲዮው ቀጥ አለ።ክብር ዘበኞቹም ራዲዮ ጣቢያው
ን እየለቀቁ ሄዱ።በዚህን ጊዜ ሁሉ አየር ሃይል አዲስ አበባን
ይቀጠቅጥ ነበር።

—ሲመሽ፡በአዲ አበባ እልልታው አስተጋባ።እነመርእድ ይልቁን



ም ጳጳሳቱ፡"ንጉስህ መጣልህ" እያሉ አደናግረውት ስለነበረ ህ
ዝቡ፡እንቅስቃሴው መቅሰፍት መስሎት ነበርና ገላጋይ እንደመ
ጣለት ቆጠረው።ይኸም ሌላ የሳይኮሎጂያዊ ጦርነት ዘዴ ነበር።

—ማታውኑ "የአዲሱ መንግስት" ሰራዊት ተበታተነ፤ላይ ግቢ ከነ
በሩት ወታደሮች በስተቀር፤ስንቅና ጥይት፡መገናኛና አዛጋር አል
ነበረውምና።ስለዚህ እነጄኔራል መንግስቱ ንዋይ፡የተረፉቸውን
ወታደሮች ይዘው፡በተያጋርነት ያስቀመጧቸውን የባላባታዊው
ን መንግስት አውራዎች ከክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምርያ ወስደ
ው በገነተ ልኡል ቤተመንግስት መሸጉ።ከመከላከያ ሚኒስቴር
ሰፈር ቀጥሎ ይኸኛው ዋና የጦር ሜዳ ሆነ።

—ወደኩንጉ የተላከው "የጠቅል ብርጌድ" የማስታወቅያ ሀላፊ የ
ነበረው፡አሀዱ ሳቡሬ፡ሁኔታው ወደአድሀሪያኑ መንጋደዱን በቅ
ጡ አልሰማም መሰል፡ባጠገቡ የነበሩት 2,500 ወታደሮች አዲ
ሱን መንግስት እንደሚደግፉ የሚገልፅ ሀተታ ፅፎ ለጋዜጠኞ
ች አደለ።

16 ታህሳስ፤ ከጧቱ 5 ሰአት ራዲዮ ጣቢያው በጦር ሰራዊ ተያዘ። )

—የእንግሊዝ አየር ሃይል አይሮፕላኖች፡በዜጎቻቸው አሳበው ጣ
ልቃ ለመግባት፡በቆጵሮስ፡በኬንያና በአደን አደፈጡ።

—ጦር ሰራዊት እየገፋ ላይ ግቢ ደረሰ።

—ሃይለስላሴ ከርቱም ደረሰ።ፋሽስቱ ጄኔራል ኢብራሂም አቡድ፥
በደንብ ከተቀበለው በኋላ፡3000 ወታደር ሊሰጠው ቃል ገባለ
ት።ከንጉሱ ጋር አገር ላገር ሲዞር የነበረው ኮሎኔል ሰለሞን ከድ
ር አይሮፕላን ውስጥ አደጋ ለመጣል ሃሳብ አለው የሚል መል
ክት ስለተነገረ፡ካለበት ተይዞ አስመራ ገባ።

—ሰአቱ አይታወቅም፡የተያዙት መሳፍንትና መኳንንት፡በገርማ
ሜ፡በሻምበል ክፍሌ ወልደማርያምና በክብር ዘበኛው ሲቪል ባ
ልደረባ በነጋሽ ድንበሩ ተረሸኑ።በዚሁ ቀንና ሰአት፡የተረሸኑት
የባላባታዊው መንግስት ደንደሶች የሚከተሉት ናቸው።ራስ ስ
ዩም መንገሻ፡አበበ አረጋይ፡አባ ሃና ጅማ፡ብላታ አየለ ገብሬ የህ
ግ መወሰኛ ፕሬዚዴንት፡ደጃዝማች ለጥ ይበሉ ገብሬ የህግ መ

ወሰኛ ምክር ቤት አባል፣ብላታ እሸቴ ገዳ ምክትል ያገር ግዛት
ሚኒስትር፣ዳዊት ኡቀባዝጊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴታ፣ሊቀ
መኳስ ታደሰ ነጋሽ የፍርድ ሚኒስትር ዴታ፣አምደ ሚካኤል ደ
ሳለኝ የማስታወቂያ ምክትል ሚኒስትር፣መኰንን ሃብተ ወልድ
ገብረወልድ እንግዳ ወርቅ ምክትል ፀሀፌ ትእዛዝ፣ለማ ወልደ
ገብርኤል የማእድን ምክትል ሚኒስትር፣ክብረት አስታጥቄ ያገ
ር ግዛት ምክትል ሚኒስትር።(4) ሐጂ ፋራና መኰንን ደነቀ እ
ግራቸውንና ጉልበታቸውን ቆስለው ዳኑ።ቀማኛው አንዳርጋቸ
ው መሳይ ግን–የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ ያለው የሚታመን ሲ
ሆን –መጋረጃ ውስጥ ተደብቆ ዳነ።ከዳኑት መካከል፣አግደው
ተሰማ፣በመከላከያ ሚኒስቴር ረዳት ሚኒስትር፣ይገኙባቸዋል።(5)

—ጦርሰራዊቱ በታንክና በሌላ ከባድ መሳሪያ ታግዞ ግቢ ጥሶ ገባ።
ገርማሜ ንዋይ–አንዳንዶቹ መንግስቱ ይላሉ–የንጉሱን አማች
ደረጃ ሀይለማርያምን ደረጃ ላይ በመትረየስ ገደለው።

—የአሜሪካኑ አምባሳደር ርቻርድስ በመስኮት ዘሎ ከግቢው አመ
ለጠ።ጀኔራል ፅጌ ዲቡ በደንብ ሲዋጋ ቆይቶ፣ሞተ።ጦርሰራዊት
ድሉን ካረጋገጠ በኋላ፣የፅጌን ሬሳ በመንገድ እየጐተተ እስከ
አራዳ ጊዮርጊስ ወሰደው።የገርማሜ ወንዳፍራሽ ሬሳ ግቢው
ውስጥ ተገኘ።ራሱን ይግደል ሲተኩስ ይሙት እስካሁን የሚያ
ውቅ የለም።

17 ታህሳስ፤ ሃይለስላሴ አዲስ አበባ ገባ።አልጋ ወራሽና ራስ እምሩ" እ
ጅ ነስተው" ተቀበሉት።

—ኰሎኔል ወርቅነህ፣ቀጨኔ አጥቢያ የተደበቀበት ቤት በጠቋሚ
ተገኝቶ፣ከጦር ሰራዊት ጋር በጥብቅ ሲዋጋ አምስት ወታደር ጋ
ዜጦች እንደሚሉት፣ሰባት ወታደር ሰው እንደሚለው፣ካራገፈ
በኋላ፣ራሱን ገደለ።ባጠገቡ፣በቡጫቂ ወረቀት በርሳስ የተፃፈ የ
መጨረሻ ቃል ተገኝቷል።ፅሁፉም፣የዳግማዊ ቴዎድሮስን አርአ
ያ መከተሉን የሚገልፅ ነበር።

—ኰሎኔል ማክሊን የ ተባለ አድሃሪ የእንግሊዚ ፓርላማ አባል፣
"ናስር ለነገሩ እንግዳ አይደለም" የሚል የሀሰት ወሬ "በደይሊ



ቴሌግራፍ" ነዛ።

—በዚች ቅዳሜ እለት የወርቅነህ ገበየሁ ሬሳ በአራዳ ጊዮርጊስ ተ
ሰቀለ።

—ሃይለስላሴ ቅልጥ ያለ ጋዜጣዊ ጉባኤ አደርጉ፣አርበኞቹን "ከሃ
ዲዎች" እያለ ትዝታቸውን ለማጉደፍ ከሞከረ በኋላ፡«የኔን ፕ
ሮግራም ከመውሰድ በስተቀር ያመጡት አዲስ ሀሳብ የለም፤ው
ድ ልጄም ተገድዶ ነው እንጂ፣ወዶ አልገባላቸውም» ሲል ፕሮ
ፖጋንዳ ነዛ።

18 ታህሳስ፤ የሃይለስላሴ የልጅ ልጅ፣ሳምሶን በየነ፣በስቶኰልም፣«ተፈሪሽ
ረውን ሽራዋለሁ» ሲል ለጋዜጠኞች ተናገረ።

—የዚያኑ ሰአት የአሸንጉሊት ምክርቤት ሊቀመምበር የነበረው ሃ
ይለማርያም ከበደ፣«ህዝብ ሊያሸፍት ሲሄድ ተገኘ» ተብሎ የፊ
ጢኝ ታስሮ ከደሴ አዲስ አበባ መጣ።

—የማስታወቂያ ሚኒስትር፡እንቅስቃሴው መጨፍለቁንና በውጊያ
325 ሰዎች መሞታቸውን አወራ።"ደይሊ ቴሌግራፍ" የሚባለ
ው የእንግሊዝ ጋዜጣ ግን፡ሟቾቹ ወደ 475 እንደሚደርሱ ገ
ምቷል።ሮይተር የወሬ ምንጭ በበኩሉ የሟቹን ሰው ቁጥር ወ
ደብዙ ሺ አድርሶታል።መተናፈሻ፡መላወሻና መፈናፈኛ በሌለ
በት አገር ውስጥ፣ፍሬውን ከገለባ መለየት አይቻልምና በዚያን
ሰሞን የወደቁትን ጀግና ተማሪዎችና ሰላማዊ ህዝብ ቁጥር አፍ
ሞልቶ መናገር ቀላል አይደለም።የተዋጉት ክብር ዘበኞች ጠቅ
ላላ ቁጥር፣4,500 ነበር።ውጊያውም 36 ሰአታት ሙሉ ነበር የቆ
የው።

—በዚህን ጊዜ ሁሉ—በትክክል ለመናገር፣ከቅዳሜ 17 ታህሳስ ጀ
ምሮ—ፈላጭ ቆራጩ መርእድ መንገሻ ነበር።ፓርላማው እስ
ከተሰበሰበበት እስከ 26 ታህሳስ ድረስ፣ከእጅ መስጠት ትእዛዝ
ጀምሮ እስከ "ህግና ስርአት ማስከበር" ድረስ ያሉት እርምጃዎ
ች ሁሉ፣ለህዝብ ሲታወጁ በመርእድ ስም ነበር።እንዲያውም፣
በጦርነቱ ሁኔታ ምክኒያት የተፈጠረው ወታደራዊ መንግስት የ
ገዛ አጫፋሪዎቹን በየቁልፉ ስፍራ ማስቀመጥ አስችሎት ነበር።

ነገር ግን በበዝባዥ ገገር መደብ ውስጥ የጥቅም ግጭትና ቅራ
ኔ ስላለ፡"ይቺ ጥሬ ካደረች አትቆረጠምም" በሚለው ፈሊጥ መ
ሰረት፡መርእድ መንገሻን ከጦር ሃይሎች ጠቅላይ መምሪያ ሹም
ነት ወደመከላከያ ሚኒስትርነት አዛወሩት።

—ሃይለስላሴ በራዲዮ ህዝቡን የሚደልል ንግግር አሰማ።"የተታለ
ሉት ሁሉ" እጃቸውን እንዲያስረክቡ አዘዘ።

19 ታህሳስ፤ ሰው ወደየስራው(ስራ ካለው ማለት ነው) ተመለሰ።

—የወርቅነህ ሬሳ ከተሰቀለበት ተነስቶ ባልታወቀ ስፍራ ተቀበረ።

—በዩኒቨርሲቲ ኰሌጅ ይማር የነበረው የወርቅነህ ታናሽ ወንድም
መብራቴ ገበየሁ፡ታሰረ።

—በኰንጎ "የጠቅል ብርጌድ" ጠቅላይ አዛዥና በኰንጎ "የተባበ
ሩት መንግስታት የሰላም ሰራዊት" የጦር ሃይሎች ጠቅላይ መ
ምርያ ምክትል ሹም የነበረው ጄኔራል ኢያሱ መንገሻ፡ወደፓ
ሪስ ኤምባሲ ባስተላለፈው ቴሌግራም፡የወታደሮቹን የነመንግ
ስቱን እንቅስቃሴ ደጋፊነት አስተባበለ።

21 ታህሳስ፤ ጌታቸው በቀለ፡የዚያኑ ጊዜ የባህር ረዳት ሚኒስትር፡ዘጠኝ
ጊዜ መደበቂያውን እየተቃከሰ ከለወጠ በኋላ፡ተያዘ።

24 ታህሳስ፤ መንግስቱና ገርማሜ ንዋይ ከክብር ዘበኛ የስፖርት ክፍል
ሀላፊ፡ከሻምበል ባየ ጥላሁን ጋር በዱከም በኩል ታቹን ወደዞቋላ
አቅጣጫ ሲያቋርጡ፡አንድ ቤት ውስጥ ገቡ።በዚያን ሰአት የንዋይ
ወንድማማቾች ስእል በገፍ ታትሞ በገፍ ተበትኖ ስለነበረ፡ተቀባያቸ
ው የሆነችው ሴትዮ፡መኖራቸውን በጐረቤት በኩል ለዱከም ፖሊ
ስ አስታወቀች።ፖሊሶች ደርሰው ተታኰሷቸው።የነመንግስቱ ሃሳ
ብ ወይም ፍላጐት ምን እንደነበረ ምንጊዜም ምስጢር ሆኖ የሚ
ቀር ነው።እንዲሁም፡በዚያች በባላገር ደሳሳ ጐጆ ውስጥ የነበረው
ሁኔታና የደረሰውም፡ፈትፋች የሚናገረውን ትተን፡ገርማሜና ባየ በ
ጥይት ሞቱ።ሲታከሱ ይሙቱ ወይም ራሳቸውን ይግደሉ ለማወቅ
አስቸጋሪ ነው።የሁለቱ ሬሳና የቆሰለው መንግስቱ ንዋይ በዱከም
ፓሊሶች ወደአዲስ አበባ ተወሰዱ።አይነስቡ ላይ በፅኑ የቆሰለው ጄ
ኔራል መንግስቱ፡እየደማ ሃይለስላሴ እግር ስር ተጣለ።የሁለቱ የጦር



ጓዶቹ ሬሳ ግን በማግስቱ አራዳ ጊዮርጊስ ላይ ተሰቀለ።የዚያለቱ ማ
ታ የያዛቸው የዱከም ፖሊስ አስር አለቃ፡አዲስ አበባ ሞቶ ተገኘ
እየተባለ ይወራል።ወሬውን ለማረጋገጥ አልተቻለም፤ገዳዩም አል
ታወቀም።

25 ታህሳስ፤ የገርማሜና የባየ ጥላሁን ስቅል ሬሳ በህዝብ ሲታይ ዋለ።
በዚያን ሰአት የተነሱ ስእሎች የህዝቡ ስሜት እንዴት እንደነበረ
አሳምረው ያሳያሉ።ከአይን ምስክር እንዳገኘነው፡አንዲት መነኩሲ
ት፡«ደግ አረጉት! ይኸን ወንበዴ!» እያለች ስትለፈልፍ ተመልካቹ
ህዝብ ደበደባት።በዚሁ ሌሊት ሬሳው ከተሰቀለበት ተወስዶ ባል
ታወቀ ስፍራ ተቀበረ።

31 ታህሳስ፤ የአቶ ተፈሪ ሻረው የሚንቀሳቀሰውና የማይንቀሳቀሰው ን
ብረት ተወረሰ።«አሁን»—አሉ አቶ ተፈሪ ሻረው—«በቆሳቁስ በ
ኩል ድሀ ነኝ።በመንፈስ ግን ጌትነትና ፀጋ ይሰማኛል።በስዊድን እ
ንኳን ባይሆን፡በሌላ አውሮፓዊት አገር፡ስራ ፈልጌ መቀጠር አለ
ብኝ።ባለቤቴ ግን የት እንዳለች አላውቅም።»

4 ጥር፤ የሀሰት ወሬ ነዛ በሚል ወንጀል የተከሰሱ አምስት ሰዎች፡አር
ባ ጅራፍ ተገረፉ።ከተገረፉት መካከል "መርከቶ" እህል ተራ፡ህዝ
ብ በተሰበሰበበት የንጉሰ ነገስቱን መንግስት የሚኰንን ንግግር አ
ድርገሀል ተብሎ የተወነጀለው ከህሳይ ተድላ የተባለው ወጣት መ
ምህር ይገኝበትዋል።

7 ጥር፤ ለጦር ሰራዊት ወታደሮች፡እንደየማእርጋቸው 20 እና 30፡ለአ
የር ሃይል 50 ብር፡በግ መግዣ ድርጎ ተሰጠ።የገናን በአል ምክን
ያት በማድረግ።

ጥር አጋማሽ፤ አንድ ቀን ማታ የጥይት ሮምታ ተሰማ።በብዙዎች የሚወራ
ው እውነት ከሆነ ገና ያልተያዙ ክብር ዘበኞች፡መድፈኛ ጦር ቅፅ
ር ግቢ ውስጥ ታስሮ የነበረውን ጄኔራል መንግስቱን ለማስለቀቅ ሲ
ሉ ከተኮሷቸው አዳፍኔና መትረየስ የመጣ ድምድም ነው።በዚያው
ሰሞን፡የማስታወቂያ ሚኒስቴር ህንፃ በቀን ብርሃን በመትረየስና በ
አዳፍኔ ተመታ።

ጥር ወር መጨረሻ ገደማ፤ በብላታ ሃይሌ ወልደኪዳን ሰብሳቢነት፡በሻ
ቼ ኰሎኔል ተፈራ ገብረማርያም ህግ አስከባሪነት፡በመንግስቱ ንዋ

ይ ላይ የሚፈርድ ልዩ ችሎት ቆመ።ተከሳሹ ከውጭ ጠበቃ መጥ
ቶ እንዲቆምለት ቢጠይቅ፡ተከልክሎ፡ጌታሁን ሁነኛው የተባለ ኢ
ትዮጵያዊ ጠበቃ"እንዲከራከርለት" በግድ ታዘዘ።የፍርድ ችሎት ለ
ህዝቡ ክፍት ይሆናል ብሎ ሃይለስለሴ በጋዜጣዊ ሸንጐ ለአለም አ
ውርቶ ሳለ፡የተገደሉት ሹማምንት ሚስቶችና ቤተሰቦች ብቻ በተ
ገኙበት በዝግ ተፈፀመ።በችሎቱ እንድትገኝ የተፈቀደላት ዣን
ኰንቲኒ የምትባል አሜሪካዊት ጋዜጠኛ ብቻ ነበረች።ከርሷ ሌላ፡
በጄኔቭ የሆነው፡የአለም ህጋጊያን(ህግ አውጪ) ደርግ(ኰሚቴ)
ታዛቢ ልኮ ነበር።ደርጉ ባወጣው የጃንዋሪ 1961 እትሙ፡ፍርዱ በ
ትክክል አለመካሄዱን ገልፀዋል።ለሙግት ወደ ኢትዮጵያ ሊሄድ
ፈልጎ የነበረው አንድ እንግሊዛዊ ጠበቃ፡ከለንደኑ የሃይለስላሴ ኤ
ምባሲ መግቢያ ቪዛ ባለማግኘቱ፡ቀረ።መንግስቱ ንዋይ የተከሰሰበ
ቸውና የተፈረደባቸው "የወንጀለኛ መቅጫ" አናቅፅ የሚከተሉት
ናቸው።250፡252፡522።ከመንግስቱ ጋር በሁለተኛ ተከሳሽነት የቀ
ረበው፡ሻምበል ክፍሌ ወልደማርያም ነበር።

17 የካቲት፤ የስዊድን መንግስት፡ከአድሃሪው መንግስት የቀረበለትን የ
እጅ ሰንሰለት አልቀበልም ብሎ፡ለአቶ ተፈሪ ሻረው፡አንደኛ ፀሃፊ
ለነበረው አባቱ ጌታቸውና ለአቶ ተፈሪ ቤተሰብ የፓለቲካ ጥገኝ
ነትን ሰጠ።

መጋቢት አጋማሽ፤ ሃይለስላሴ፡35 ውጭ የተማሩ ወጣቶችን፡ረዳት ሚኒ
ስትርና ዋና ድሬክተር እያለ በየቦታው ሸነሸናቸው።

መጋቢት መጨረሻ ገደማ፤ ጦር ሰራዊት ቃል የተገባለትን 40 ብር ደ
ሞዝ ባለማግኘቱ፡ከግጉረምረሙም በላይ፡መንግስቱን ለመገልበጥ
የልብ ልብ ተሰማው።ተዳፍኖ የነበረው ቅሬኔ ሁሉ እንደሚፈታ
ም አስታወቀ።ሃይለስላሴ ደመወዝ ጨመረለት።ነገር ግን፡ለ ጠቅላላ
ው ሰራዊት የተዳረገውን ገንዘብ ድምር ብቻ ስለሆነ የተናገረው፡
ወታደሩ በነፍስ ወከፍ ቢያከፍለው፡ሶስት ብር እንኳን እንደማይደ
ርሰው ገባው።ስለዚህ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ፡ተሰፋ የተገ
ባለትን የ40 ብር ደመወዝ እድገት አገኘ።ከዚያን ጊዜ ወዲህ፡ዛቻ
ን ለኑሮ ማሻሻያ መሳሪያ አድርጐ ይጠቀምበታል።



29 መጋቢት፤ ታይቶ በማይታወቅ ቅልጥፍና የተኰጠነው የነመንግስቱ
ፍርድ ፍፃሜ ደርሶ መንግስቱ ንዋይና ክፍሌ ወልደማርያም የሞ
ት ፍርድ ተፈረደባቸው።መንግስቱ ይግባኝ አልልም አለ።ከብዙዎ
ች እንደተሰማው «የኔ ከጓደኞቼ ተለይቶ በህይወት መቆየት»–አ
ለ ጀኔራል መንግስቱ ንዋይ፡የመጨረሻ ቃሉን ሲሰጥ – «የዘመኑ
ን ፍትህ ለመጪው ትውልድ ለመመስከር ረድቷል፤ከእንግዲህ ወ
ዲህ መቆሜን አልፈልገውም፤ከኔ በፊት የሞቱትን አግኝቼ የዘራሁ
ው ዘር ስር የያዘ መሆኑን እንድነግራቸው መሞት ይገባኛል።»

መጋቢት 30፤ በትናንትናና በዛሬው አጥቢያ መንግስቱ ንዋይ፡ከወታደር
ደንብ ውጭ በሆነ አኳኋን፡የጀኔራል መለዮውን ለብሶ፡ተክለሃይማ
ኖት አጠገብ ተሰቀለ።ሲሰቀልም፡ሃይለስላሴ በቦታው ተገኝቶ ነበር
ይባላል።ያም ሆነ ይህ፡የአለም በቃኙ ሰቃይ የጭነት መኪና ላይ አ
ውጥቶ ማነቆውን ካጠለቀበት በኋላ፡ጀኔራል መንግስቱ ንዋይ፡መ
ኪናው ተነስቶ እስኪያንጠለጥለው ድረስ ሳይጠብቅ፡ዘሎ ህይወቱ
ን አሳለፈ፤ሬሳው ተሰቅሎ ውሎ ማታ ተነሳ፤የተቀበረበት ቦታ ግን አ
ይታወቅም።እህቱ ሬሳው እንዲሰጣት ጠይቃ አሉታ መልስ አገ
ኘታለች።ጀኔራል መንግስቱ በተሰቀለ ማግስት፡ንብረቱ ሁሉ ተወ
ረሰ።ያሳድጋቸው የነበሩት ልጆች ተባረሩ።የታህሳሱ እንቅስቃሴ የ
መጀመሪያው ደረጃ እዚህ ላይ ተደመደመ።

23 ሀምሌ፤ (16 ሀምሌ) "የሙሉ ነፃነት መንግስት ማህበር" የተሰኘ ስብ
ሰብ፡"የጥፋት ልደት" የሚል ፅሁፍ በከተማው አስበተነ፤አበባ ታበረ
ክት ዘንድ በእቴጌ ተማሪዎች ስም በቀረበችው ትንሽ ልጅ እቅፍ
ውስጥ ከቶ ሃይለስላሴ እጅ እንዲደርስ አድርጓልም እየተባለ ይወ
ራል።ወዲያውኑ በግቢም በውጭም የሰው አደን ተጀመረ።ከዚያ
በኋላ፡በዚህ ማህበር ስም እያሌ ተባራሪ ቅጠሎች በአዲስ አበባ ከ
ተማ ውስጥ ተነዝተዋል።

19 መስከረም፤ አምልጠ ደብረ ሲና አጠገብ፡ከካህናት ጋር ይኖር የነበ
ረው፡መኳንንቱን ከረሸኑት አንዱ፡የክብር ዘበኛው ነጋሽ ድንበሩ፡
ተሰቀለ።ከዚያ ቀደም ብሎ፡ከፍተኛው ፍርድ ቤት 15 አመት ፈር
ዶበት ነበር።ይግባኝ ቢል ጊዜ ግን፡ሃይለስላሴ «ይሙት በቃ» ብሎ

ፈረደበት።በጠቅላላው ከተፈረደባቸው ጥቂቶቹን መጥቀስ አይከፋ
ም።ሻለቃ ተፈራ ወልደ ተንሳይ 15 አመት፣የክብር ዘበኛ ማስታወ
ቂያ ክፍል ሹም የነበረው ሻምበል አስራት አደፍርስ አምስት አ
መት፣የክብር ዘበኛ አርኬስትራ መሪ የነበረው ሻምበል አፈወርቅ
ዮሀንስ ሶስት አመት፣በራዲዮ "የህዝብ መንግስት" የጦር ሃይሎች
ፕሮፓጋንደኛ የነበረው ዳምጤ አሰማኸኝ ሶስት አመት የተፈረደ
ባቸው በዚሁ አመት ውስጥ ነው።ዛሬ ከሞላ ጐደል ሁሉም ተፈት
ተዋል።

የታሰሩት እጅግ ብዙ ናቸው።ሁሉንም መዘርዘር እጅግ ያስቸግራ
ል።በዚሁ ምክንያት የተሰደዱት ኢትዮጵያውያን ቁጥር 15 ይደር
ሳል።ከነዚህ ሌላ ስንት ሰዎች እንደተሰደዱ ማወቅ አዳጋች ነው።ይ
ኸ ሁሉ ሁኔታ፣የኢትዮጵያን ሰርቶ አደር ህዝብ እንቅስቃሴ በበለ
ጠ እንቃቃው።ከዚያ ወዲያ ያለው አዲስ የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪ
ክ መሆኑ ጥርጥር የለውም።ስለዚሁ ጉዳይ የተጠቃቀነ ሃሳብ ለማግ
ኘት፣በዚሁ ቁጥራችን ውስጥ የቀረቡትን ልዩ ልዩ ጥናቶች መመ
ልከት ይጠቅማል።

---

ከዚህ በላይ በኩ ዴታው ጊዜና በኩ ዴታው ሰሞን የተወሰዱትን
ና የተፈፀሙትን እርምጃዎች ዝርዝር፣ለአንባቢዎቻችን ለማቅረብ ሞክ
ረናል።ሙከራችን የተሟላ አይደለም።ስለኩ ዴታው የተሟላ ዜና ለመስ
ጠት የሚችሉ በኩ ዴታው ውስጥ የተሳተፉ ወይንም ኩ ዴታውን በቅ
ርብ ሆነው የተከታተሉ ብቻ ናቸው።ለጊዜው ከነዚህ ሰዎች ጋር ግንኙ
ነት ማድረግ ወይንም ከነሱ ዜና ማግኘት "ትንሽ" አስቸጋሪ መሆኑ ለማ
ንም ግልፅ ነው።ዘመኑ በሚያመችበት ጊዜ፣እነዚህ ሶዎች ስለኩ ዴታው
"የተጨበጡ"ና ሰፊ ዜናዎችን እንደሚሰጡን ተስፋ እናደርጋለን።የጐደ
ለው በዚያን ጊዜ ይሟላል።

ከፍ ብለው የሰፈሩት ዜናዎች ከአንባቢዎቻችን የደረሱን ናቸው።
ለትክክለኛነታቸው ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች አይደለንም።ነገር ግን ከ
ብዙ አቅራቢዎች ተደጋግመው በመነገራቸው ከእውነት ብዙ አይርቁ
ም ብሎ በመገመት ለአንባቢዎቻችን ለማቅረብ ደፍረናል።አንባቢዎቻ



ችን የማይስማሙባቸው ነገሮች ቢኖሩ አስተያየታቸውን ቢያስታውቁን
በደስታ እንደምንቀበለው ልንገልፃቸው እንወዳለን።

---

(1) በነዚያ ታሪካዊ ቀናት የታዩትንና የደረሱትን ድርጊቶች ስን
ዘረዝር፣አመተ ምህረቱን የጠቀስነው እንደአውሮፓ አቆጣጠ
ር ነው።የወራቱ ስም ግን፣ያው የኢትዮጵያ ነው።"ሴፕቴምበር"
ን መስከረም ብሎ ለቆጠረ፣አከሄዳችን አያሳስተውም።
(2) ሬይፎርድ ሎጋን፤ጆርናል ኦፍ ከረንት ሂስትሪ፤፬ሊዩም 44 ቁ
ጥር 257 ጃንዋሪ 1963 ተመልከት።
(3) ሰአቱን የምንጠቅሰው እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር ነው።
(4) ያንዳንዶቹ ስልጣን ለማንም ግልፅ በመሆኑ አልጠቀስነውም
(5) ሙሉጌታ ቡሌም በዚሁ ቀን ተገድሏል።ብዙ የቅርብ ተመል
ካቾች በይፋ እንደሚያወሩት ከሆነ የገደሉት የአዲሱ መንግ
ስት ወገኖች አይደሉም፤አድሃሪው ወገን አስገድሎታል እያ
ሉ ይጠረጥራሉ።

## የታህሳስ ጀግኖች

### መግቢያ

ስለታህሳሱ እንቅስቃሴ ሲወራ "ስለአንቀሳቃሾቹ" ማውጋት የግድ
ያስፈልጋል።የእንቅስቃሴው መሪዎች እነማን ነበሩ? ሀሳባቸው ምን ነበ
ር? ምን አይነት መንግስታዊ ድርጅቶች ለማቋቋም አቅደው ነበር? . . . .

እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ጥያቄዎች በሰፊው መመለስ ነበረ
ባቸው።እያንዳንዱን "መሪ" እየወሰዱ ለነዚህ ጥያቄዎች የነበረውን መል
ስ ለአንባቢዎች ማቅረብ ሰውየውን በበለጠ "ከማስተዋወቱም" በላይ ከ
ድርጊቶቹም የሚቀሰሙትን ትምህርቶች የተሻለ አቅጣጫ(የተጣራ መ
ልክ) ይሰጣቸው ነበር።

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ በቅድሚያ ይኸንኑ በመረዳት ስለአንዳንዱ
"መሪ" የፖለቲካ አስተሳሰብ፡የህይወት ታሪክ . . . . ለመሰብሰብ ወጥኖ ነ
በር።ነገር ግን፡ትክክለኛ ምንጭ ማግኘቱ በማስቸገሩና አልፎ አልፎ ያጋ
ጠሙንም "ዜና አዋቂዎች" ዜናቸውን ለማካፈል ያላቸው ፈቃድ በመ
መንመኑ ውጥኑ በሚገባ ሳይሳካ ቀርቷል።

ዜና ማግኘት የቻልነው ስለአንዳንድ ሰዎች ብቻ ሲሆን ይኸውም
ራሱ የተሟላ አይደለም።አልፎ አልፎም "ግድፈት" ሊኖረው ይችላል።በ
ዝርዝርና በሰፊው የማቅረቡ ፈንታ "እውቀቱ" ያላቸው ሰዎች ነው።እነ
ዚህ ሰዎች "በተመቻቸውና አጋጣሚ" ባገኙ ጊዜ ያላቸውን ዜና እንደ
ሚያካፍሉን ተስፋ እናደርጋለን።"ሰው ያለውን ከምዘገዘገ ፈሪ አይባል
ም" የሚባለውን የአባቶች ታሪክ በመመርኮዝ ያችንው ያለችንን ምጥን
ዜና ቀጥለን ለአንባቢዎቻችን አቅርበናል።አንባቢዎች የጐደለውን እያ
ሟሉ፡የተገደፈውን እያቀኑ እንዲያነቡ ስንጠይቅ የሚያቀርቡልንም እር
ማት ወይም ተጨማሪ ዜና ካለ በደስታ የምንቀበል መሆናችንን እያስ
ታወስን ነው።

### ገርማሜ ንዋይ

እ.አ.አ. በ1924 ዓ.ም. በአዲስ አበባ፡በጊዮርጊስ ቀበሌ ተወለደ።
የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን በተፈሪ መኰንን፡የሁለተኛ ደረጃ ትምህር



ቱን በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አከናወነ።ከዚያ
ም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አሜሪካን አገር ሄዶ በዊስኰንሲንና በኰሎ
ምቢያ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርቱን በመከታተል የማስትሬት ዲግሪውን
አገኘ።

በ1954 ዓ.ም. ገርማሜ ለዶክትሬት ዲግሪው ትምህርቱን ለመቀ
ጠል በመዘጋጀት ላይ ሳለ በኃይለስላሴ መንግስት ተጠርቶ ወደ ኢትዮ
ጵያ ተመለሰ።እንደተመለሰም ተራበተራ በአገር ግዛት ሚኒስቴር የወላ
ሞ አገረ ገዥና የጅጅጋ አገረ ገዥ ሆኖ ሰረቶአል።

በተማሪነቱ ወቅት ገርማሜ ንዋይ በተማሪ እንቅስቃሴዎች ከፍ ያ
ለ ንቃትና ተሳታፊነት እንዳሳየ የታወቀ ነው።በተፈሪ መኰንን ትምህር
ት ቤት በተደረጉት ፀረጀስዊት እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ እስከመታሰ
ር መድረሱ ይነገራል።አሜሪካ በነበረበት ጊዜ በዕሁፎችም ሆነ በክርክ
ሮች ከፍ ያለ ተሳታፊነት ከማሳየቱም በላይ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበ
ር ፕሬዚዳንት ሆኖ ሰርቶአል።

ማንኛውም የህዝብ ጉዳይ የህብረት እንጂ የግለሰብ ስራ ውጤት
ሊሆን እንደማይችል ገርማሜ ተረድቶት እንደነበረ አገሩ ከተመለሰ በ
ኋላ የተማሩትን ወጣቶች ለማደራጀትና በፖለቲካ መስመር ለማሰለፍ
ያደረገው ጥረት በጉልህ ያሳያል።በመጀመሪያ በራስ እምሩ መኖሪያ ይሰ
በሰቡ የነበሩትን የተማሩ ወጣቶች ከልተጨበጠ ወሬና ከዊስኪ እንካሰ
ላንቲያ ወደ አገሪቱ እውነተኛ ፕሮብሌሞች ፊታቸውን ለማዞርና ከመ
ጠጥ ማህበርነት ወደ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ለመምራት ሞከረ።የአብዛ
ኞቹ አድርባይነትና የመንግስቱ ሰላዮች ጥረት ይኸንን ሙከራውን አከ
ሸፈው።ከዚያም የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ትምህርት ቤት የቀድሞ ተማሪዎ
ች ማህበርን በማቋቋም የለውጥ ፖለቲካ መሳሪያ ሊያደርገው ሞከረ።ያ
ብዛኛዎቹን ማህበርተኞች የመሳፍንት መብት ተቆርቋሪነትና የተረፉትን
አድርባይነት ቀስ በቀስ ገርማሜ ተረዳው።የጊዜው የተማሩ ወጣቶች አ
ንድነትና ለአገሪቱ እድገት ቆርጦ ለመታገል ያላቸው ጉጉት የተ ወሰነ
መሆኑ ግልፅ ሆነለት።ስለዚህም ለአገሩ የሚመኝላትን ለወጥ ለማምጣት
ሌላ ድጋፍ መፈለግ ጀመረ።በወንድሙ በመንግስቱ ንዋይ አማካይነት ወ
ደ ጦር ኃይሎች፡በተለይ ወደ ክብር ዘበኛ፡ፊቱን አዞረ።

ከታህሳሱ ኩ ዴታ መሪዎች ውስጥ በፖለቲካ ንቃትና ተራማጅነት ገርማሜ ንዋይ ግንባር ቀደም እንደነበር ጥርጥር የለውም።የገርማሜ ርእዮተአለም ምን ነበር? ሊደረስበት የሚፈልጋቸው ግቦች ምን ምን ነበሩ? እነኚህን ጥያቄዎች በተሟላ መልክ ለመመለስ ገርማሜን በቅርብ የሚያውቁት፣አብረውት ለብዙ ጊዜ የሰሩና ሃሳቡን የተካፈሉት፣በተለይ የሬቮሉሽነሪው ካውንስል ስብሰባዎችና ድርጊቶች ላይ የነበሩ ሰዎች መፃፍ፣መናገርና ያሉዋቸውን መረጃዎች ማውጣት እስኪችሉ ድረስ መጠበቅ ያስፈልጋል።እስከሁን በሚታወቀው ይህ ወጣት ከፍ ባለ ያገር ፍቅር የሚገፋፋ፣ለኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮ መሻሻል በተቀዳሚነት የሚቆረቆር እንደነበር አይጠረጠርም።ስለኢትዮጵያ ስርአት በሚመለከትበት ጊዜ በመጀመሪያ ላይ(አሜሪካን አገር ተማሪ ሆኖ ሳለ) አፄ ሃይለስላሴን በመርዳት ያገሪቱን ሁኔታ ማሻሻል ያስፈልጋል ብሎ ቢያስብና ቢፅፍም አገሩ ከገባ በኋላ የሃይለስላሴ ተራማጅነት በወሬ ብቻ መሆኑን በቅርብ ሆኖ ሊገነዘብ ቻለ።በተለይም በፊውዳል ስርአቱ ውስጥ መሻሻል ማድረግ ይቻላል ማለት ከንቱ ሃሳብ መሆኑን እንደተረዳው አያጠራጥርም።

በፊውዳሊዝም ስርአት ውስጥ ያለው የባለርስትና የጢሰኛ ገበሬ መሰረታዊ የማይታረቅ ጠብ ለወጣቱ ገርማሜ ገና በተማሪነት ዘመኑ ሳለ ታይቶት ነበር።በአሜሪካን አገር ባቀረበው ቴሲስ ውስጥ ስለፊውዳሊዝም መሰረታዊ ቅራኔ ሲያትት እንዲህ ይላል፤«ፊውዳል ባላባቶች ሃብታቸውን የሚያዳብሩት ገበሬው ከሚያመርተው አብልጠው በመዝረፍ እንጅ ምረቱን በማሳደግ አይደለም።በዚህም ሰፊውን ህዝብ እያደር በሚከፋ ድህነት ውስጥ ይጨምሩታል ማለት ነው።»

ከሃይለስላሴና ከአስተዳደሩ ጋር አብሮ መስራት አለመቻሉን ሲረዳ ከአስተዳደሩ ውጭ በሆኑ ሃይሎች በመረዳት(የተማሩ ወጣቶች ማህበር፣የድሮ ተማሪዎች ማህበር) ለማሻሻል እንደሞከረ ግልፅ ነው።ይህም ሙከራ እንደማያዛልቅ አየው፤ስለዚህም አስተዳደሩን በሃይል ለመለወጥ ቆረጠ።ይህም በጊዜው ከነበሩት ግንባር ቀደም ተማሪዎችና ምሁራን አቋም በድርጊት አልፎ የሄደ በመሆኑ ገርማሜን የግንባር ቀደም ግንባር ቀደም ሊያደርገው ችሏል።

ገርማሜ በአለምና በተለይም በአፍሪቃ ስለነበረው ሁኔታ አጥርቶ



የሚያውቅ ነበር።ቅኝ አገዛዝን በጥብቅና በማያወላውል አኳኋን ሲያወግዝ ስለ ኢምፔሪያሊዝምም ብዙ ቅራኔዎችን ይገልፅ ነበር።ገርማሜ ከተማሪነቱ ወቅት ጀምሮ ኢምፔሪያሊስቶች በአፍሪቃ የሚያደረጉትን ጥፋት ተመልክቶ፣በጠቅላላው የቅኝ ገዢዎች በአፍሪቃ የሚያደርጉትን ጭቆናና ዘረፋ ይኰንናል፤የአፍሪቃ ህዝቦች የሚያደርጉትን ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል በአድናቆት ይመለከታል።ይህም ፀረኢምፔሪያሊስት ትግል ያለውን የወደፊት እድል ሲገልፅ፣«አፍሪቃውያን መብታቸውን እስኪያረጋግጡ ድረስ የራሳቸውንና የሃገራቸውን እድል በገዛ እጃቸው እስከስገቡ ድረስ ሪቮሉሽኑ እንደሚቀጥል ምንም ጥርጥር የለውም» ይላል።በተለይ ስለ ኢትዮጵያ የአሜሪካን ኢፔሪያሊዝምን ጠንቅ ልብ ብሎ ባያየውም ብዙዎች እንደፃፉት የአገሪቷን ከኢምፔሪሊያዝም ጋር መግጠም በጥሩ አይን የሚመለከተው አልነበረም።

በአስተሳሰቡ ከፍ ያለ ሶሽያሊስት ዝንባሌ እንደነበረው ግልፅ ነው፤ ብዙ መፃህፍቶችን አንብቧል። በወላሞ የሚገኙትን ሚስዮኖች ከስደነበሩዋቸው ነገሮች አንዱ ገርማሜ ቤት ይገኙ የነበሩት የማርክሲስት መፅሀፎች እንደነበሩ ይገልፃል።

ባጭሩ ገርማሜ አገር ወዳድና ቆራጥ ኢትዮጵያዊ ከመሆኑም በላይ በፖለቲካ አስተሳሰቡ ከታህሳሶቹ የበሰለና ተራማጅ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ለሚያምንበት ኢትዮጵያ እስከመጨረሻ ድረስ የታገለና ህይወቱን የሰዋ ጀግና ነው።ግንባር ቀደም የሆነ ኢትዮጵያዊ፣ምሁራንና ተማሪ አርአያነቱን ሁሌም የሚመክበትና ከመንፈሱ የማያወጣው ነው።

## መንግስቱ ንዋይ

እ.አ.አ. በ1916 ተወለደ።ከኢጣሊያን ወረራ በፊት በሆለታ ካዴት ትምህርት ቤት ከቆየ በኋላ፣ጣልያን ኢትዮጵያን በያዘበት ጊዜ በስደት ጅቡቲና ካርቱም ቆይቷል።ከዚያም በክብር ዘበኛ ውስጥ በመኰንንነት ሲሰራ ቆይቶ በኰሎኔልነት ምክትል አዛዥ ከነበረ በኋላ እ.አ.አ. በ3-10-56 ብሪጋዴር ጄኔራል ሆኖ የክብር ዘበኛ ጠቅላይ አዛዥ ሆነ።

መንግስቱ በፖለቲካ አስተሳሰቡ የነበረውን ትክክለኛ አቋም ለመናገር ያስቸግራል።እንደገና በቅርብ የሚያውቁት ለመግለፅ እስኪችሉ

መጠበቅ ያሻል።በጠቅላላው ግን ስለመንግስቱ በምንናገርበት ጊዜ ሁለት ነገሮችን ማስታወስ ያስፈልጋል።አንደኛ፡ወንድሙ ገርማሜ በሃሳብና በአስተያየት የማያጠራጥር ተፅእኖ እንደነበረው ለመገመት አያስቸግርም፤ሁለተኛ ደግሞ መንግስቱ በገጋርው መደብ ውስጥ ሙሉ አባል በመሆን ሀይልና ሀብት ሳያንሰው ሁሉ በጁ ሁሉ በደጁ የነበረ ሰው ሆኖ ሳለ በአገር ወዳድነት ስሜት ተገፋፍቶ ያንን ድሎት በመናቅ ለለውጥ ቆርጦ ተነስቷል።ይህ ብቻውን ከፍ ያለ ምሳሌነትን ያዘለ ነው ለማለት ይቻላል።

## ወርቅነህ ገበየሁ

ወርቅነህ ትውልዱ ጎንደር ሲሆን ከድሀ ቤተሰብ የመነጨ ነው።በራሱ ተጣጣሪነት አዲስ አበባ መጥቶ በስዊድኖች በመረዳት ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ገባ።ቀጥሎም በክብር ዘበኛ የካዴቶች ትምህርት ቤት የጦር ትምህርት መከታተል ጀምረ።በዚያን ጊዜ መንግስቱ ሊያውቀው ከመቻሉም በላይ ንቃቱንና አስተዋይነቱን አይቶ ድጋፉን ይሰጠው ጀመር።መንግስቱ የብርጋዴር ጄኔራል ማእርግ ባገኘበት ጊዜ ወርቅነህ ፀጥታ ክፍል ውስጥ እንዲሰራ አደረገው።እ.አ.አ. ግንበት 1959 በረዳት ሚኒስትር ደረጃ የፀጥታ ክፍል ሹም ሆነ።ነሀሴ 1959 በሌተና ኰሎኔልነት ማእርግ ልዩ ክቢኔ ውስጥ የኢታ ማጆር ምክትል ሹም ሆነ።

ስለወርቅነህ የፖለቲካ አስተያየት ያሉት መረጃዎች በጣም ትንሽ ናቸው።ይሁን እንጂ በጠቅላላ አነጋገር ከአንዳንድ ወጣቶች ጋር ስለለውጥ በሚነጋገርበት ጊዜ ወደፊት ተራማጅ አስተያየት እንደነበረው ይነገራል።በተለይም ጥቅም ወዳድ የሆኑትን ሁሉ ይንቅፍ ነበር።በግል ኑሮውም የተቆጠበና ስራ ወዳድ መሆኑ ይታወቃል።

በራሱ ተጣጣሪነት፣ጥሮ ግሮ ያደገ ሰው ሲሆን በእጁ ይዞት የነበረው ሃይልና ስልጣን ሳይማርከው (ከሃይለስላሴ ጋር የነበረውን ቅርብ ተደማጭነት ማስታወስ ይበቃል) የኩ ዴታውን ዝግጅት እያወቀ በጭር ሊቀጨው ሲችል እንዲያውም ተመልሶ ከገርማሜ በሰማው ጊዜ ሙሉ ተባባሪ መሆኑን በቆራጥነትና በጀግንነት ስራው አስመስክሯል።



## ፅጌ ዲቡ

በግምት፡እ.አ.አ. በ1910 ዓ.ም. ሀረር አውራጃ ጉርሱም ተወለደ። ፅጌ ዲቡ የልጅነቱን ጊዜ ጉርሱም፡ሀረርጌና ጅጅጋ አሳለፈ።የፋሺስት ጦር ኢትዮጵያን ሲወር ፅጌ ዲቡ ከኢትዮጵያውያን አርበኞች ጦር ጋር ተቀላቅሎ ሲዋጋ ቆየ።ከዚያም ወደ "እንግሊዝ ሱማሌ" ተሰደደ።ኢትዮጵያ ነፃነቷን ስታገኝ ፅጌ ዲቡ በጦር ትምህርት ቤት የመኰንን ትምህርትን አጠናቆ፡በኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት በልዩ ልዩ የመኰንን ደረጃ አገልግሏል። በመጨረሻም በብሪጋዴር ጄኔራል ማእርግ የፖሊስ ሰራዊት ጠቅላይ አዛጋ ሆኖ ሰርቷል።

ስለፅጌ ዲቡ ፖለቲካዊ አቋም አስተያየት መስጠት በጣም አስቸጋሪ ነው።ከየአቅጣጫው ብዙ ተቃራኒ ዜናዎች ይሰማሉ።በቅርብ የሚያውቁት ትክክለኛውን ዜና እስኪሰጡን መጠበቁ ይሻላል።ግን እዚህ ላይ ያለአንዳች ጥርጥር ለመጥቀስ የምንችለው አለ።ይኸውም ፅጌ ዲቡ በታህሳሱ "አብዮት" ተካፋይ ከመሆኑም በላይ ከመሪዎቹ አንዱ ነበር።በቆራጥነት ሲዋጋ በትግሉ ሜዳ ላይ ህይወቱን ሰውቷል።

ስለነሻለቃ የሀንስ ምስክር፡ሻለቃ ተፈራ ወልደተንሳይ፡ሻምበል ባየ ጥላሁን፡ነጋሽ ድንበሩ፡ገርማሜ ወንዳፍራሽ.... (ዝርዝሩ ብዙ ነው) አጭር ዜና እንኳን ለመስጠት ባለመቻላችን እናዝናለን።ምክኒያቱን በመግቢያው ላይ መግለፃችን ይታወሳል።ስለነሱ ምንም ወሬ ማግኘት አልቻልንም።

ከነዚህ ወጣቶች አንዳንዶቹ በጦር ሜዳ ላይ ህይወታቸውን ሰውተዋል።አንዳንዱ ከተያዙ በኋላ ተፈርዶባቸው(!) ተረሽነዋል፤ተሰቅለዋል፤ ብዙዎቹ በርከት ላሉ አመታት በእስር ቤት ከፍ ያለ ስቃይ ተቀብለዋል፤ አሁንም ገና በእስር ቤት በመማቀቅ ላይ ያሉ አይጠፉም።

ወጣም ወረደ፡ሁሉም በአገር ፍቅር በመገፋፋት በታያቸው መንገድና በተገለፀላቸው መንገድ ጨቋኙን መንግስት ለመገልበጥ ሞክረዋል። ለጊዜው የተሳካለት ቢመስልም ቆራጦቹ የጀመሩት ውጥን ግቡን ማግኘቱ ስለማይቀር በዚያን ጊዜ "ለታህሳሱ ጀግኖች" የኢትዮጵያ ህዝብ እውነተኛ በታቸውን ይሰጣቸዋል።

# የታሀሳሱ እንቅስቃሴ "አናቶሚ"

ከዙዋይ ረዚን

## መቅድም

የታህሳሱ ቀራጦች የተሳሳቱባቸው አያሌ ፍሬነገሮች ነበሩ።ቢሆንም እኛ በመንበረ ፃድቃን ላይ ተቀምጠን፡እነሱን እንደመካነ ህፀአን ወስደን የነቀፌታ እሳት ካወረድንባቸው እውነቱን ለማወቅ አንችልም። ድርጊቶቻቸውንም በአንፃር በአንፃር ለይቶ በመመልከት ሊቀሰም የሚቻለው ትምህርት ሊያመልጠን ይችላል።እነሱ ራሳቸውን ባቀኑበት ወቅት—ከዚያም በፊት—የነበረውን የኢትዮጵያ ሁኔታ አፍታትተን ለማየት፡የነሱንም ህብረተሰባዊና መደባዊ ምንጭ ለይተን ለማወቅ ብንጣጣር ከፊታችን ለሚጠብቀን እንደ ሞገድ የጠነከረ ትግል ጠቃሚ ትምህርቶችን ለማትረፍ እንችላለን።ከለዚያ በመርፌ ጫፍ ላይ ምን ያህል መላእክት ተንጠላጥለዋል እያልን ስናሰላ ቀኑ ይመሽብናል....።

## መግቢያ

ቡርጋርዋ ሊቃውንትና ጋዜጠኞች፡በደፈናውም አድሀራዊያን ሁሉ ሊያሳምኑን እንደሚፈልጉት ሰዎች አንድ ታሪካዊ እርምጃ ሲወስዱ፡«ድንገት "ስለሚታያቸው"» ወይም «ወፈፍ አድርጓቸው» አይደለም።ድርጊታቸውን የሚያነሳሳውና ታሪካዊ የሚያደርገው በአንድ የተወሰነ ጊዜ ህብረተሰባቸው የሚገኝበት ተጨባጭ ሁኔታ ነው።በሌላ አነጋገር፡ድርጊታቸው የአንድ ተጨባጭ ሁኔታ ነፀብራቅ ነው።ሆኖም፡ድርጊታቸውን የሚመሩትና የድርጊታቸውንም ግቦች የሚተልሙት፡የመደብ ጥቅሞቻቸውና ርእዮተአለማቸው ናቸው።በተለይ በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸው የመደብ ቦታ፡ስለህዝብ የሚኖራቸውን አስተያየት ይገራባቸዋል።በህዝብ ላይ የሚኖራቸውም እምነት ወይም እምነተቢስነት በዚሁ ላይ የተመሰረተ ነው።ስለሆነም፡ድርጊታቸው፡ሪቮሉሺናዊያንን ባያጠግብም፡ሪቮሉሺናዊያን በስሜት ተመርተው፡ሣጢአታቸውን በማብዛት፡እነሱ ያንቀሳቀሱትን እርምጃ ጠቃሚነት መሳት የለባቸውም።ስለዚህ፡በዚህ ፅሁፍ ውስጥ፡የታህሳሱን እንቅስቃሴ "ዴሞክራሲያዊ አብዮት" ብለን ብንጠራው፡እነ



ዚያ የማይረሱ ሰአታት ዴሞክራሲያዊ ነበሩ ወይም ዴሞክራሲን አመጡልን ለማለት ሳይሆን፡የፈጠሩት ሁኔታ ሰርቶ አደር ህዝባችንን ወደዴሞክራሲያዊ ትግል ሳቡት ማለታችን ነው።

እዚህ ላይ፡ምሁራዊ ንትርክ አያሻም።ማድረግ ያለብን፡የኢትዮጵያን ህብረተሰባዊ አቋምና በውስጡም የሚከናወኑትን ድርጊቶች በሳይንሳዊ አቅድ ሰነጣጥረን ለመመርመር መሞከር ነው።ታሪካዊና ህብረተሰባዊ እድገትን ከግለሰብ አድራጐቶች አንፃር መመልከት ትተን፡የሰፊው ህዝብ(the mass) ጠቅላላና ዝርዝር ድርጊቶች ውጤት መሆኑን በቅድሚያ ማመን አለብን።ታሪክን የሚፈጥረው ጀግናው ወይም ስመጥሩው አይደለም።ስምና አድራሻው፡መልኩና አኳኋኑ የማይታወቀው ሰፊው ህዝብ እንጂ።ስለዚህ፡ታሪክን ስንመረምር መጠየቅ ያለብን «እገሌ ምን አደረገ?» ሳይሆን፡«የሆነው ሲደረግ፡ሁኔታው ምን አይነት ነበር?» ነው። ብጭሩ፡ታሪክ በመሰረቱ ከኤኮኖሚ አቋምና የኤኮኖሚውን አቋም ተመርኩዞ ከሚፈልቀው ስርአተማህበር ተነጥሎ ሊታይ አይገባውም!ሊታይ አይችልም።

«እስከ ዛሬ ድረስ (1) ያለው የማናቸውም ህብረተሰብ ታሪክ» –አሉ ገናናዎቹ የፕሮሌታሪያት መምህራን፡ማርክስና ኤንግልስ–«የመደቦች ትግል ታሪክ ነው።»

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ከዚህ የእድገት ህግ ውጭ አይደለም።የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ፡በጨቋኞችና ተጨቋኞች፡በበዝባዦችና ተበዝባዦች መካከል ሲደረግ የቆየውና አሁንም የሚደረገው የመደብ ትግል ታሪክ ነው።

ከስመጥፉው ዘመነ–መሳፍንት (1750–1855) (2) ጀምሮ፡ከዚያም በፊት(ራቅ ብለን ሳንሄድ)፡የጥቅም አበላላቸው በተለያየው ልዩ ልዩ ገዢ መደቦች መካከል፡እንዲሁም በማእከላዩ መንግስት ና በነዚህ የቀበሌ አውራዎች መካከል ይፈፀም የነበረው ደም መቃባት ህዝቡን አሰለቸው።የዘውድ አወራረሱ ህግ፡ መላና ቅጥ አጣ።በዚሁ ሁከትና ደም መፋሰስ በበዛበት ሁኔታ ውስጥ፡ድሀው አራሽ የጌቶቹን መሬት እየነጠቀ፡(በእውነት የገዛ ራሱ መሆኑን ገና አልተረዳውም ነበር።) እንዳይወሰድበትም እየተናነቀ ሲታገል ኖረ።መኳንንቱ በፊናቸው፡የገበሬው ትንንቅ

ዳብሮና ተዛምዶ የመደብ ጥቅማቸውን እንዳያጠፉባቸው በመስጋት ጊዜያዊ እርቅ እያደረጉ በአንድነት ሆነው ህዝቡን ቀጠቀጡት።የኢትዮጵያ ህዝብ ቀልቡ ጠፋ።ድንጋይ የመጥረብ፥ግንብ የማነፅ ልማድ የነበረው ህዝርችን፥ወፍ ይመስል ጐጆ እየቀለሰ፥ገና ከሩቅ ሰው ሲያይ እየበረገገ ኖረ።የንጉስ ወታደር ወይም የአንድ ባለማአርግ ጭፍሮች፥እየመጡ በእጁ ያለውን ሁሉ እየሻጠጡ ስለበሉበት፥ከእጅ ወደአፍ የሚሆነውን ብቻ ማምረትን የመከላከያ ዘዴ አደረገው።ለማይመለከተው የመኳንንት የርስ በርስ ብጥብጥ የጥይት ራት መሆን የሰለቸው ገበሬ ምኑንም ሳያውቀው በገፍ እየተከነ የቤተክርስቲያን ጭፍራ ሆነ።በአሁኑ ወቅት በወሎ፥በትግሬና በበጌምድር ከያምስቱ ወንድ አንዱ ካህን ነው።የባለበት ደግሞ፥"ለጌታ እያደረ" ብጤዎቹን ይዘርፍና ይበድል ገባ።

በደፈናው፥እነዚህ ናቸው ወደኋላ የመቅረታችን ምክንያቶች።ምልክታቸው አሁንም አልጠፋም።አገራችን፥ሶሺያሊዝምን ስትገነባም እንኳን፥የነዚህ ደዌዎች ሰንበር በቶሎ እንደማይጠፋላት ግልፅ ነው።

— I —

## የቅድመ–1960 ኢትዮጵያ
## ህብረተሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዝጓዝ

አገራችን የምትገዛው መሰረቱ የፊውዳል ስርአት በሆነ አድሃሪ የንጉሰ ነገስት መንግስት ነው።ማለት፥መንግስቱ የተተከለው ታሪክ ሞት በፈረደበት፥ፈፅሞ ወደኋላ በቀረ ኢኮኖሚያዊ መሰረት ላይ ነው። ይህ ኤኮኖሚያዊ አቋም የወለደው ህብረተሰባዊ ስርአት የተወሳሰቡ ቅራኔችዎ በዝተውበት፥የህዝባችንን ግስጋሴ ገትቷል።ከነዚህ ቅራኔዎች የተነሱ፥የምርትና የሀብት እድገት ተዘግቶ ተይዟል።የአምራቹና የሸማቹ ህዝብ ቆሳቁሳዊና አእምሯዊ ፍላጎቶች ፍፁም ሊረኩ አልቻሉም።የኤኮኖሚው ልእላነ–አቋም የሆኑት ኑባሬዎች(3) ለህዝቡ ቁራኛ ሆነውበታል

ባምራቹና በሸማቹ መካከል፥በአምራቹም በሸማቹም ህዝብ ውስጥ፥በህዝቡና በገዢዎቹ፥ከዚያም አልፎ በገዢዎቹ መካከል የጥቅም ልዩነቶች የፈጠሯቸው መሰረታዊ ቅራኔዎች አሉ።የድሮዎቹ የገጠር መኳንንት፥ስራቸውን ሳይነቅሉ በአኗኗራቸው የቡርዣዋነት ጠባይ ወስደዋል።



ስለዚህ፥የኢትዮጵያ ልብ፥እንደጥንቱ ከገጠር ሳይሆን፥በከተማ ነው የሚመታው።በገጠርና በከተማ መካከል ቁልጭ ያለ የኑሮም የአስተሳሰብም ልዩነት አለ።ሚስት የፈተለችው ኩታ፥ቁጥራቸው ከዘበት ቀን ለሚበልጠው "የህዝብ በአላት" እንጂ፥ለአሁኑ የአሮጌና የዘመናዊ መጢቃ(ዲቃላ)ኑሮ አገልግሎቱ እየተቀነሰ ሄዷል።በጭስ የታፈነው ጐጆ እንኳን፥ጭራሮ ወይም ላት ማብራቱን ትቶ፥የሚጠቀመው እንደያቅሙ በጋዝ ወይም በፋኖስ ነው።ጊዜውም ቢሆን ፍቹን ለውጧል፤"ለክርሞ" የሚል ጠሙን ያድራል ለዛሬ የሚሆነው እንኳን የለውምና።

አዲስ አበባና ሌሎቹ "እድለኞች" ከተሞች፥በከፊል ኤሌክትሪክ አላቸው።

ገዥ መደቦች ባንድ በኩል አጥንቱን ቆጣሪ መሳፍንት በሌላው በኩል ጊዜው ያፈራው "የዘመኑ" መኳንንት ሆነው አይን ያወጣ የስልጣን ሽሚያ ጀምሯል።

ንጉሱ አንዱን አጋብቶ ሌላውን ማፋታት፥አንዱን ሽር ሌላውን መሸም ዋና ስራው ሆኖአል።

መኳንንቱ(የመሬቱም የገንዘቡም) አይን ባይን ሚስት ይነጣጠቃል፤እቁባት ያስቀምጣል፤ዲቃላ ያንጠባጥባል፤የህዝቡን ሴት ልጆች ያገለምታል፤ውርስ ላይ ውላጆቹን ያጋድላል።

የህዝቧ ልጅ፥መድረሻ አጥታ ሽርሙጥና ገብታለች።

በጠቅላላው፥አይን የማያሸው ጭቆናና ብዝበዛ ከፍ ያለ የኤኮኖሚና የግብረገብነት ውድቀት አስከትሏል።

የኮሪያው ኢምፔሪያሊስት ጦርነት የቡናን ዋጋ አስወደደ።ማገዶው "የኢትዮጵያ" ወታደር ያመጣውን የደሙን ዋጋ ናኘው።የውስጡ ገበያ ነፍስ የዘራበት መስሎ ታየ።እንዲሁም አክሉ የጉደለበት ምስኪን በዛ።ግን ወዲያውኑ ግብፅ በእንግሊዝ፥ፈረንሳይና እስራኤል ተወረ ስትከላከል፥የስዊዝ በር በመዘጋቱ በአንድ ሸቀጥ ላይ የተንጠለጠለው የአገራችን ኤኮኖሚ ወደቀ።«በእንቅርት ላይ ጆሮ–ደግፍ» እንደሚባለው፥የተፈጥሮ ቁጣዎች(መአቶች) ተከታትለው መጡ።ብዙውን የኢትዮጵያ ክፍል፥ተምችና አንበጣ መታው።ወረርሽኝ ተከትላ መጣች።"ፈላጭ ቆራጩ" የንጉሰ ነገስት መንግስት አውራ ወደቤጌምድርና ጐጃም ሄዶ፥«የ

ግብር ምህረት አደረግሁ» አለ።በመሀሉ፣መኰንን ሃይለስላሴ የሰው ሚ
ስት ሲያጐለምት ባልየው በጥይት አቃጠለው።ባላገሩ፣ያለቅስና ያላቅስ
ዘንድ በጭቃ ሹምና በምስለኔ እየተገደደ ከነኮተቱ ወደአዲስ አበባ ጐ
ረፈ።ይህ "ብሄራዊ ሀዘን" ከያሙና ከባአላቱ ጋር ተደምሮ፣መሬት እየጫ
ረ፣ከተመኛውን የሚመግበውን አራሽ ስራ አስፈታው።

ብዙ ገበሬ በየገጠሩ ከፍጥረትና ከፊውዳል ስርአት ጋር የሚያደ
ርገው ትንንቅ ታክቶት፣በትውልድ አገሩ ከገባበትም እዳ ለማምለጥ፣ከና
ከቴው እንደወጣ ቀረ።በተለይ አዲስ አበባ ትልቅ የተስፋ—ቢስ ህዝብ
መታጐሪያ ሰፈር ሆነች።ይኸ ሳያንስ፣"የመስፍኑ ሀረር መታሰቢያ ሆስፒ
ታል መዋጮ" ህዝቡን በደረቁ ላጨው።በከተማ ማጅራት መምታት፣በገ
ጠር ውንብድና፣በመስሪያና ፍርድ ቤቶች ጉቦ መብላት ታይቶ ከማይታ
ወቅ ደረጃ ደረሱ።

ትግሬና ወሎ በ1951 በረሀብ ተመትተው፣100,000 (4) ሰው አ
ለቀ።ትስበ፣በትግሬ ብቻ 400,000 (5) ሰው ፈጀ።በሽታው እንዳይዛመ
ት አስፕኢይ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ተብሎ፣ሰብል በእሸትነቱ እ
ሳት ተለቀቀበት።ከብትም አለቀ።ከተመኛውም ባላገሩም ትርቦ፣የእህል
ዋጋ ሰማይ ወጣ።«የመካከለኛው ምስራቅ ጐተራ ለመሆን ትችላለች» ተ
ብላ የምትገመተው አገራችን፣የያንኪ የነቀዘ ስንዴ ማፍሰሻ ሆነች።"ስን
ዴ አዳዮቹ" በለስልጣኖች፣ከዱቄቱ ጋር ኖራ እየቀየጡ ረሀብተኛውን በ
ተቅማጥ ስቃይ ጨረሱት።እነዚህ አሜሪካኖች ሲከብሩ፣ድሀው በየሚዳው
ወድቆ ስለቀረ ጅብ እንኳን ፊላ በብዛቱ ሸቶበት ሻቹን ትቶ እስከማለፍ ደረ
ሰ።ስለዚህ ነገር ያየው ቢናገር ይሻላል።

ይኸ መቅሰፍት የገጠሩን ህዝብ ቁጥር ከፉኛ አቃወሰ።ባላገሩ ሙ
ልጭ ብሎ ከተማ መግባት በመጀመሩ፣ኋላ የቀሩት ሴቶች፣ህፃናትና አዛ
ውንት የተተወውን እርሻ ብቻቸውን ሊያካሂዱት አልቻሉም።አባወራ
ቸው ለግብር ከፍያ በአራጣ የተበደረውን ገንዘብ ለመክፈል አልቻሉም፤
እርቦ ለማፍሰስ የተበደረውን የሀል ዘር መመለስ ተሳናቸው።በግርድና
ለመኖር ወደከተማ የሄደችው ሴት ስራ አጥታ ሸርሙጥና ገባች።

በሚያዝያ ወር 1952 የደራሳ ህዝብ በንጉሱ ልጅ በተናኘ ወርቅና
በልጅዋ መሬቱን ቢነጠቅ አምፆ፣የአድሀሪው መንግስት ወታደሮች አን



ድ ሺ የሚሆን ገደሉበት።በዚያው ሰሞን፣በወሎ፣ጨፋ ወረዳ፣ገበሬ ስለሸ
ፈተ ወታደር ተልኮ፣ህዝቡም ተፈጀ፤መንደሮቹም ተቃጠሉበት።

የስራ—ፈቱ በአዲስ አበባ ከተማ መከማቸት፣ለጥቂት ጊዜ፣ለካፒታ
ሊስቶቹ ተመቻቸው፤የተቀጣሪዎቻቸውን ደመወዝ በዝቅተኛነቱ ለማዝ
ለቅ።በኋላ ግን፣ይኸ ምቹ ሁኔታ በሰራተኛው ህዝብ ዘንድ የፈጠረው ቅ
ራኔ ከርሮ እንዳይፈነዳ ስለተፈራ፣ሙያተኛውም ስራ—ፈቱም እየተለቀ
መ ወደአዶላ ተጋዘ።

"ፈላጭ" የንጉሰ ነገስቱ መንግስት ራሱ ከፈጠረው አዙሪት ሁኔታ
ለመውጣትና በመንፈስ ሊሸፍትበት የተቃረበውን ህዝብ ለመደለል፣"የ
አምስት አመት(1957–61) የልማት እቅድ" አወጣ።ነገር ግን፣እቅዱ እ
ንኳን ሙሉ በሙሉ በከፊልም እንደማይሳካ ከመጀመሪያው ግልፅ ነበር።

በፊውዳል የመረሬ ጭቃ ውስጥ በሚዳክር ስርአተ መንግስት ው
ስጥ "የኤኮኖሚ ፕላን" መገመት ጉምን ለመጨበጥ የመቃጣት ያህል
ነው።የዘውድ ኢዮቤልዩ(1948) ሲከበር የወጣው ገንዘብ፣ከዚያም በኋ
ላ የደረሱት የዘረዘርናቸው ሁኔታዎች፣የገዢዎቹም ዘረፋ ጭምር ግምጃ
ቤቱን አራቁተውታል።ሆኖም፣አድሀሪው መንግስት ይዞታውን ለማጥበ
ቅ ይመቸው ዘንድ፣በእቅዱ አሳቦ አገሪቱን ለኢምፔሪያሊስቶች—በተለ
ይም ለያንኪ ኢምፔሪያሊዝም—ብርግድ አድርጐ ከመክፈቱም በላይ፣ከ
ነሱ ገንዘብ እየተበደረ የጦርና የፀጥታ ሃይሎችን አጠነከረ፤ቢሮክራሲው
ንም አስፋፋው።የከከ ከላ ባህል ድንኳኑን ጣለብን።ላልቶ የነበረው የገ
ጠር ይዞታው ከተጠናከረለት በኋላ፣«የትምህርትና የጤና ታክስ» እያለ
ሰርቶ—አደሩን ህዝብ ሞለጨው።

አዲሷ ጠቅላይ ግዛት—ኤርትራ—ተደረበች።በኤርትራ ጦር ሰራ
ዊት መላክ ብቻ ሳይሆን፣የባህርና የአየር ሃይል ማቋቋምና ማስፋር አስ
ፈለገ።

በዚህ ሁሉ ጉድ ላይ፣ንጉሱ ከቁጥጥሩ ውጭ ከሆነበት ሁኔታ ለማ
ምለጥ፣ሃፍረተ—ቢስና እረፍተ—ቢስ ቱሪስት ሆነ።(በነገራችን ላይ ብዙው
ን ጊዜ ጋብዙኝ እያለ ነው ለጉብኝት የሚጋበዘው።) ነገር ግን፣"ሲሮጡ
የታጠቁት፣ሲሮጡ ይፈታል" እንደሚባለው፣ካፋጠጠው ገሀድ ለመሹለክ የመ
ረጠው ዘዴ፣ብሄራዊውን ገቢ ስላሟጠጠው ሁኔታውን አባባሰው።እንዲ

ሁም፡የ"ወዳጅ አገር እንግዶቻችንን" ለመቀበል የሚደረገው ወጪ።

ከዚህም በቀር፡የአፍሪቃ ህዝቦች ነፃነታቸውን ማግኘትና ነፃ የእድገት ጎዳና ለመከተል መታገል፡ይልቁንም የሱማሊያ፡ሱዳንና ግብፅ ሬፑፕሊካዊ አስተዳደር መትከል፡ውስጡ የበሰበሰውን ፊውዳሊስት መንግስት ክፉኛ አስበረገገው።ስጋቱ ግን፡ከነዚህ አንዳቸው ያጠፉኛል ብሎ ሳይሆን፡የነዚህ አገሮች ሽውታ ወደኢትዮጵያ ነፍሶ ህዝቡን እንዳያነቃብት ነበር።የኤርትራው ውስጣዊ አስተዳደር ህገመንግስትና የሚፈቅዳቸው የቡርዣዋው ዴሞክራቲካዊ መብቶች ራሳቸው ራስ ምታት ሆነውበት ነበር።

ቢሆንም የህዝቡ የማወቅ ጉጉት እንዳይቀሰቅስበት በመፍራት ስሜቱን በምስጢር እንደያዘ፡የሰሎሞንና የሳባ ተረቱን ሳይለቅ፡ፊቱን ወደአፍሪቃ አዞሮ፡በአህጉሩ ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ ይንበጫረቅ ጀመር።ይህን ሲያደርግ ግን፡«ኢትዮጵያዊያን ከአፍሪቃዊያን በዘርም፡በስልጣኔም በባህልም ይበልጣሉ» ብሎ ለማሳመን ስብከቱን አላቆመም።ለዚህ ነበር ለአንድ በጣት ለሚቆጠሩ ወጣት አፍሪቃዊያን ድርጎ እየሰጠ ባሉት ኮሌጆች ውስጥ ለአይነት ያስቀመጣቸው።

የታህሳሱ ቆራጦች፡አድሀሪውን ፊውዳሊስት መንግስት ለመገልበጥ በተነሱበት ወቅት፡ኢትዮጵያን አይነተኛ የሚያደርጉት ሁኔታዎች እነዚህ ነበሩ።የእንቅስቃሴውም አነሳስና አወዳደቅ ሳቢያዎች መታየት ያለባቸው ከዚህ አንፃር ነው።

— II —

## የታህሳሱ እንቅስቃሴ ጉድለቶች (weaknesses)

የተዘረዘረው ሁኔታ ሰርቶ–አደሩን ህዝብ ተከላካይ፡ገዢዎቹን አጥቂ አድርጓቸው ነበር።በሌላ አነጋገር፡ሰርቶ–አደሩ የፖለቲካና የመደብ ንቃት አልነበረውም፤የገዢዎቹ መንግስትና ሌላውም መጨቆኛ መሳሪያቸው እጅግ ጠንካራ ነበር።ባጭሩ፡ህሊናዊውና አንፃራዊው ሁኔታዎች ለህዝባዊ ሬቮሉሽን የተመቹ አልነበሩም።ከዚህም በቀር፡ይህ ሁኔታ የወለደው የፖለቲካ ወይም ሌላ አይነት ህዝባዊ ድርጅት አልነበረም።በዚህ ረገድ ሲታይ፡ህብረተሰባዊ ቦታቸው የተዘጋጀ ድርጅታዊ አቋም የሰ



ጣቸው የጦር መኰንኖችና ሲቪል ባልንጀሮቻቸው፡ሁኔታውን ለማረም —አዎን ለማረም— መነሳታቸው የሚያስገርም የሁኔታው ውጤት ነው። የመደብ አስተያየታቸው ግን በሰፊው ህዝብ ላይ እምነት ከማሳደር አገዳቸው።ከለዚያማ ኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የፀጥታ ሹም፡ጀኔራል ፅጌ ዲቡ የፖሊስ አዛዥ ሆነው በሴራው ከገቡ ዘንድ በቅድሚያ ሌላው እንኳ ቢቀር አንድ ስውር የመኰንኖች ድርጅት በቋቋሙ ነበር።(ይህን ለማድረግ ለነሱ ቀላል ነበርና ነው እነሱን የጠቀስናቸው።) አብሯቸው ጠንስሶ በኋላ የከዳቸው የዚያን ጊዜው ኰሎኔል የበኋላው ጀኔራል ታደሰ ብሩ በነሱ ስህተት ተምሮ፡ለሙከራው ምርኩዝ ይሆነው ዘንድ፡ድርጅት አቁሞ እንደነበር ይታወሳል።ደግሞም መርእድ መንገሻና ከበደ ገብሬ፡ከሀረርና ደብረ ብርሃን ጦር አንቀሳቅሰው፡ደም ለመቃባትና ለማቃባት መዘጋጀታቸው በታወቀ ጊዜ፡ታህሳሳውያኑ ለህዝቡ መሳሪያ ማደል ነበረባቸው።ብቻ "በነበረ ቤት አይሰራም" . . . .

የታህሳሱ እንቅስቃሴ ዋናው ጉድለቱ—ቀደም ብለን እንደገለፅነው—ላብ አደሩንና ገበሬውን፡ንኡስ ብርዧዋውን አንቀሳቅሶ የሚያሳትፍ ድርጅት አለመፈጠሩ ነው።ንኡስ ቡርዧዋ፡በየመሸታ ቤቱ ይራቀቅበት የነበረውን "የለውጥ" ወግ ረስቶ፡ገለልተኛ ተመልካች ሆነ።በመጠኑም የተሳተፉት ተማሪዎች ብቻ ናቸው።ከምሁራኑ ውስጥ እጅግ ወረተኞች የሆኑት፡ደም ደም ሸቷቸው ወደብሾፍቱና አምቦ ሸመጠጡ።ነገር ግን ደግሞ፡እያንዳንዱ ጭቁን መደብ እንዴትና በየትኛው አካል አማካይነት ድጋፉን ያበርክት?

ከህዝቡ ጋር ረድፋቸውን ከገጠሙት አንዳንድ ምሁራን በስተቀር ሌላው ቀለም–ጠቀስ እኮ፡በታሪካዊ ጊዜያት ህዝቡ ሲነሳ ጭራ ይሆናል እንጂ ለግንባር–ቀደምነት ወግ አይበቃም።ስለዚህ፡ሰርቶ–አደሩ ሳይመራው ቀርቶ፡ማን እደሚያሸንፍ ለማየት ያደባውን ምሁር እንደዚህ ስናኳስሰው ሀጢአት አይሆንብንም?! ይኸን መሰረታዊ ጠባዩን ለይተን ካላወቅንበት፡በወሳኙ የህዝባችን ትግል ጊዜ በስተጀርባ ነው የሚወጋን።

የአልጋ ወራሹ ንግግር ራሱ ማንንም የማያረካ ነበር።«አንተን መስዬ በደመወዝ አድራለሁ» ሲል፡ደመወዝ ይቅር የእለት ጉርስ የሌለው ህዝብ እንዴት ይመነው? ደመወዙ፡ባለው ጥሬ ገንዘብና የመሬት ሃብት

ላይ ተጨማሪ ነው ወይስ ሁሉን እርግፍ አድርጎ በደሞዝ ብቻ መኖርን ነው የመረጠው? የአልጋ ወራሹ ንግግር ለነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ አልነበረም።አልጋ ወራሹ፣በህገመንግስቱ መሰረት ተዘጋጅሁ እንጂ፣አዲስ ህገመንግስት እፅፋለሁ ወይም የነበረውን ህገመንግስት ሽሬያለሁ አላለም።በዚያም ሰአት ሆነ ከዚያ በፊት፣ከዚያም በኋላ፣ለሃይለስላሴ ህገመንግስት ቁብ የነበረውና ያለው ማነው? ስንቱስ ነው? ይኸ ሀረግ፣እንቅስቃሴው የሃይለስላሴን አስተዳደር መንቅሮ ለመጣል የፈለገ አላስመሰለውም።አልጋ ወራሹ ዱሮውንም ጥሩ ገዢ አልነበረውም፤ለዚህ የወሎ ህዝብ ይመስክር! ህዝቡ፣እንደምሁራን ፀጉር መሰበጣጠርን አያውቅም፤ረቂቅ ቃላት ለሱ ነፋስ ናቸው።የሚያምነው በሚጨበጥ ሀቅ፣በሚታይ ድርጊት ብቻ ነው።ይኸን ምንጊዜም መርሳት የለብንም።

ባለአስራ—አንዱ—ነጥብ መግለጫም እንደዚሁ አሻሚ ነበር።ወገግ ብሎ የሚታይበት ነገር ቢኖር፣በጎ አሳቢነቱ ብቻ ነው።በተግባር ላይ የመዋሉ ጉዳይ ግን በጣም አጠራጣሪ ነበር።ስራ ለፈታው ስራ ይላል።ስራው ከየት ነው የሚመጣው? የሚታረሰው መሬት ሁሉ በታላላቅ ባላባቶች እጅ ሆኖ? ፋብሪካ ሳይኖር? ስራ እንዴት ነው የሚፈጠረው? ስራው ዛሬውኑ ካልተገኘ ምን ያደርጋል? ለዚህ ለዚህማ፣ሃይለስላሴም ከሞትክ በኋላ መቃብርህ ላይ ፋብሪካ ሰርቼ ከሰማይ ቤት አስጠራሀለሁ ብሎም አልነበረ? የሆነውስ ይሁን? ስራ ሰጪዎቹ እነኛ ሰውን ከመንገድ እያፈሱ አዶላ ሲያግዙ የነበሩት ፖሊሶች ናቸው ወይስ ባላገር ግብር በዛብኝ ብሎ ሲያምፅ፣በዘመናዊ መሳሪያ ይጨፈልቁት የነበሩት ክብር ዘበኞች?

ከትምህርት ገበታ የተባረሩት ሁሉ ወደተማሪ ቤት ይመለሳሉ ይላል።ተማሪ ቤቱ መቼ ተሰርቶ? ተማሪ "ሲያብጥ" ከበው የሚቀጠቅጡት ክብር ዘበኞችና ፖሊሶች ናቸው ለተጨናገፈው እድሉ የሚቆረቆሩለት?

በትምህርት ቤትና ሆስፒታል መስሪያ እየተሳበበ የከተማ ቦታ የተወሰደባቸው ካሳ ይከፈላቸዋል ይላል።ከሚገብሩበት የጢሰኛ ወይም የግል ኩርማን መሬት በሃይለኞች ተነቅለው፣ቤት ታዳራቸውን ጥለው፣የሚጉላሉት በዝተው ሳለ ለርስተኞች ካሳ ለመክፈል ቃል የሚገባ "አዲስ" መንግስት ለነሱ ምናቸው ነው?



የፍርድ ቤቶቹ ፍትህ ገምዳልነት፣የዳኞቹ ጉቦ በላተኝነት፣የነገርተኞች መጉላላት መቼ ተጠቀሰ? የፋብሪካው ሰራተኛና የሻያተኛው ኑሮ እንዴም አልተወሳም።የውጭ ከበርቴዎችን አብሮ ፋብሪካ እየከፈተ ወይም እንደልቡ እየነገደ "ያገሩን" ድንግል ገበያ ለመብላት የሚመኘው ነጋዴ ከቁጥር ውስጥ አልገባም።ሴትኛ አዳሪዋ ከገባችበት አዘቅት የምትወጣበት መፍትሄ አልተሰነዘረላትም።ምሁሩ፣እንደየትምህርት መስኩ የስራ ድልድል እንደሚደረግለት አልተነገረውም።

በሌላ ትእዛዝ እስኪሻር ድረስ የተደነገገው የሰአት እላፊ ደንብና የምክር ቤቱ መበተን ህዝቡን በፍፁም የሚመለከቱ አልነበሩም።ሰአት እላፊ ድሮም አለ፤ፓርላማው ደግሞ "የእሺ ጌታዬ" ባዮች ማጉሪያ ነው።

እንደሚታየው፣አዋጁም ሆነ መግለጫው የንቅናቄውን ወዳጆችና ጠላቶች አይለይም።በግልፅ የሰርቶ አደሩን ህዝብ መደብ ድጋፍ ለማግኘት አለመቃጣቱ፣አላማው የህብረተሰቡን ቅራኔዎች በማዳፈን፣ታዳጊውን ቡርጋዦዊ ለስልጣን ለማብቃት ብቻ መሆኑን ያሳያል።

የታህሳሱ እንቅስቃሴ መሪዎች ራሳቸውን አለማስወቃቸው፣ከሰፊው ድርጊታቸው የተነሳ በህዝቡ ዘንድ አለመወደዳቸውን ያውቁ እንደነበረና በህዝቡ እምነት እንዳልነበራቸው፣እንዲሁም በራሳቸው እንዳልተማመኑ ያመለክታል።ለዚህ ብለው፣"የግድ ቃን ጮሌ" ያበቀሉትን ራስ እምሩንና ሙሉጌታ ቡሊን አምጥተው ሾሟቸው።በአድሃሪው ሰራዊት ቅራኔ ለማምጣት ደግሞ፣የወታደሩን ደመወዝ መጨመራቸውን አወጁ።ይኸ ሃሳባቸው በአንድ በኩል ለጊዜው ታሪካዊ ጥቅም ቢኖረውም፣በሰላማዊው ህዝብና በሰራዊቱ መካከል የነበረውን ልዩነት እንዳሰፋው አልተገነዘቡትም።እዚያው በዚያው፣የሰራተኛው ህዝብ ደመወዝ መጨመሩን ቢያስነግሩ ኖሮ ግን . . . .

በዚህ ሁሉ ላይ፣ተገለበጠ የተባለውን የሃይለስላሴን አገዛዝ ግፍ በዝርዝር አላጋለጡም።

## -III-

## የታህሳሱ እንቅስቃሴ ስህተቶች

የኢትዮጵያ ቡርጋዦዊ—ይልቁንም ወታደራዊው ክንፉ—በንኡ

ስ ቡርጋርዋው ምሁር ተደግፎ ፊውዳሊዝምን ለመጣል ያልቻለባቸው
ምክንያቶች ተዘርዝረዋል።ነገር ግን፡ቡርጋርዋዚው ገና ታዳጊ ስለነበረ፡አ
ስተሳሰቡን ፊውዳላዊ አስተያየት እንደተጫነበት ለማንም ግልፅ ነው።በ
መጀመሪያ እቅዱን እንመልከት .....

1ኛ) በፊውዳላዊ ህብረተሰብ ውስጥ፡ምርት ግታ በተፈጥሮ ሃይሎ
ችና በድንገት የሚከናወን በመሆኑ፡በአስተሳሰባችንና በምግ
ባራችን ላይ ምልክቱን ትቶልናል።በእንደዚህ አይነቱ ህብረ
ተሰብ ውስጥ ያደገ ሰው፡እንኳን መንግስት መገልበጥን ያሀ
ል ትልቅ ድርጊት ከላንዳች እክል ማከናወን፡ለወዳጅ ቀጠር
ም በሰአት መድረስ ያዳግተዋል።ጠቅላላው ህብረተሰብ፡በካ
ፒታሊዝም፡ከዚያም ይልቅ በሶሺያሊዝም ስርአት ስር በዲሲ
ፕሊን ተደራጅቶ ሲሰራና ሲኖር ብቻ ነው በአጊጊሩም በአስ
ተሳሰቡም ከዝርክርክነት የሚገላገለው።እነ ጄኔራል መንግስ
ቱ ንዋይ፡አድሀሪውን አስተዳደር ለመገልበጥ ውጥናቸው የ
ቆና ሆኖ ሳለ፡የፖለቲካ ፕሮግራማቸው፡ስትራቴጂያቸውና ታ
ክቲካቸው፡እንዲሁም ድርጅታዊ አቋማቸው በዚህ ምክንያ
ት በቅጡ ሊሰናዳላቸው አልቻለም።ከነሱ በፊት፡ከነሱም በኋ
ላ የተዶለቱት ፀረመንግስት ሴራዎች፡እደዚሁ መክነው መቅ
ረታቸው፡ከፍ ብለን የዘረዘርናቸውን አስተያየቶች ሊያረጋግ
ጥልን ይችላል።የገበሬ ህብረተሰብ ባንዴ ለመክበር እንደሚ
ቸኩል ሁሉ፡እነ መንግስቱ ንዋይም፡ሀሳባቸው ገና ስር ሳይሰ
ድ በተሎ እንዲሳካላቸው ተቻኩሉ።የአካባቢያቸው ውልዶ
ች ናቸውና፡አካባቢያቸው ያስተላለፈላቸውን ውርስ በሙሉ
መንጥቀው ለመጣል አልቻሉም።

2ኛ) የፖለቲካ ፕሮግራማቸው፡በዚያን ሰአት ሰፍኖ የነበረውን ጠ
ቅላላ ሁኔታ አላስተዋለም።(6)

3ኛ) እንቅስቃሴው ሳይሳካ ቢቀር፡አላማውን ለማዝለቅ የሚያስች
ል ስትራቴጂ አልተዘጋጀም።ቢያስፈልግ ገጠር ገብቶ በወያ
ኔ(በህዝባዊ) ጦርነት ውጊያ ለመቀጠል የሚያስችል እቅድ
አልተሰናዳም።



4ኛ) የታህሳሱ ሙከራ አነሳሾች፡ህዝብ ግር ብሎ ይነሳል ብለው ገ
ምተው ነበር።ግፍ መኖሩን ማወቅ አንድ ነገር ነው፤የግፉ ም
ክንያቶች የትኞቹ እንደሆኑ ማወቅ ግን ሌላ ነገር ነው።ጄኔራ
ል መንግስቱ ንዋይ፡ቲአትርና የጦር ልምምድ በማሳየት፡እን
ዲሁም በሙዚቃና በአለባበስ ክብር ዘበኞችን ለማስወደድ
ሞክረው ነበር።እንደዚህ አይነቱ ዋዛ ትምህርት፡መንግስት መ
ገልበጥን ለሚያህል ሙከራ ፋይዳ የለውም።ያለፉ ታሪኮች ደ
ህና አድርገው እንዳረጋገጡት፡አስተሳሰብ አይደለም የአንድ
ን ሰው ማንነት የሚገራው፤ማንነቱ ነው አስተሳሰቡን የሚገ
ራው።በሌላ አነጋገር፡ክብር ዘበኞች ራሳቸውን በህዝቡ ዘንድ
ያስወደዱ ቢመስላቸውም፡የጭቆና መሳሪያ መሆናቸው ይኸ
ንኑ የጭቆና መሳሪያ ለመደምሰስ የሚያስችላቸውን አስተሳ
ሰብ አልሰጣቸውም።

5ኛ) ከእንቅስቃሴው መሪዎች ውስጥ፡የህዝብ ልጅ አይገኝባቸው
ም ነበር።

6ኛ) ህሙስ እለት፡ታህሳስ 1953፡በአዲስ አበባ ከተማ ውጊያ ከመ
ጀመሩ በፊት፡አንደኛ ክፍለ ጦር፡መድፈኛውና ታንከኛው ክ
ፍል እንዲሁም አየር ሃይል አልተከበበም።ውጊያው ሲጀመ
ር ደግሞ፡በአለቃና በጭፍራ እንዲሁም በተለያዩት የክብር ዘ
በኛ ክፍሎች መካከል ሊኖር የሚገባው የተቀናበረ የጦር ሜ
ዳ ግንኙነት ተቋረጠ።ይኸ አደጋ ይደርስ ይሆናል ብለው መ
ሪዎቹ አልገመቱም ነበር።

የከሸፈቱን ቴክኒካዊ ምክንያቶች ልንዘረዝር ብንሞክር፡ቁጥራቸው
ና አይነታቸው ስለሚበዛብን እዚህ ላይ እናቆማለን።ሆኖም፡ይኸን ምእ
ራፍ ከመዝጋታችን በፊት ልንል የምንችለው አንድ ነገር አለ፤«አብዮ
ታውያኑ ጠፉ፡አብዮቱ ግን ቀጥሏል!» «ከኔ በፊት የሞቱትን አግኝቼ የ
ዘራነው ዘር ስር የያዘ መሆኑን እንድነግራቸው መሞት አለብኝ» የሚለ
ው የጄኔራል መንግስቱ ንዋይ የመጨረሻ ቃል፡ከትንቢትነት ወደገሀድ
ነት መለወጡን ባለፉት አስር አመታት—ይልቁንም ባለፉት አምስት አ
መታት—የደረሱት የከተማውም ሆኑ የገጠሩ እንቅስቃሴዎች ይመሰክ

ራሉ።ንዋይ ወንድማማቾችና የጦር ጓዶቻቸው የጫሩት እሳት፡ዴሞክራሲያዊውን ትግል አንቀሳቅሶና አፋጥኖ አድሀሪያውያኑን ማቃጠል ጀምሯል።ህዝባዊት ኢትዮጵያ እስከምትቋቋምበት ድረስ ትግሉ ይቀጥላል። በፊታችን ተደቅኖ ለሚጠብቀን ታላቅ ትግል ይረዳ ዘንድ ከታህሳሱ ድርጊቶች የሚገኙትን ትምህርቶች ሁሉ በሚገባ ከመቅሰም አንቦዝን።

–IV–

## ታህሳስ ሊደገም ይችላልን?

ያለፈውን ምእራፍ ስንዘጋ፡«አብዮታውያኑ ጠፉ፤አብዮቱ ግን ቀጥሏል» ብለን ነበር።እዚህ ላይ፡አባባላችን አሻሚ መሆን የለበትም።የታህሳሱን ሙከራ ያንቀሳቀሰው ሰበብና ሙከራው ያንኰራኰረው እንቅስቃሴ ነው ቀጥሏል የተባለው።በአሁኑ ሰአት፡ፊውዳሉ ስርአት የጨቆናቸው መደቦች ሁሉ እንደየመደባቸው ጥቅም ጨቋኛቸውን ስርአት ይቋቋማሉ።የአሁኑ የትግል ደረጃችን ከፊውዳሊስቶቹና ከጥገኞቹ ባለከፒታሎች በስተቀር፡ህዝቡን በሙሉ አቅፏል።የመደብ ትግሉ የህብረተሰባችን አንቀሳቃሽ ሆኖ ሳለ፡መሰረታዊ ጥቅማቸው የተነካባቸው መደቦች ሁሉ፡ጥላቻቸውን የደገኑት በፊውዳሊስቱና ከውስጡ በበቀሉት ኢትዮጵያዊያንና በሱ ጡት አባትነት በደነደኑት ባእዳን ላይ ነው።ይኸ ዋና ጠላት ባይኖር ኖሮ፣እነዚህ የተለያዩ መደቦች ምንጊዜም ተመሳሳይ ምኞት፣ተመሳሳይ አላማ ሊኖራቸው ባልቻለም ነበር።ከፍ ብለን የታህሳሱን እንቅስቃሴ «ዴሞክራሲያዊ አብዮት» ብለን የሰየምንበት ምክንያት ለዚህ ነው።ይኸ የጥቁ መደቦች ወዳጅነት ግን ዘለቄታ የለውም።

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ቅራኔዎች ከላይ ወደታች ሊወነዱ—ይቅርታ ሊድበሰበሱ—የሚችሉበት ተጨባጭ ሁኔታና ጊዜ አለፈ።ከእንግዲህ ወዲያ ከላይ ወደታች የሚመጣ "ለውጥ"፡ከሁኑ ፊውዳላዊ ጭቆና የማይሻል፡አድሀሪና ፋሺስታዊ የወታደር ጭቆና እንደሚሆን ለማንም ግልፅ ነው።የያንኪ ኢምፔሪያሊዝም ተቺዎች እንኳን፡አገራችን «ሌላዋ ቪየትናም» እንደምትሆን ተነበየውብናል።ይኸ ከሆነ እንኰራለን እንጂ አንርበደበድም።እነሱማ እኛን ማስበርገጋቸው ነው!በኛ አስተያየት፣ከእንግዲህ ወዲያ በኢትዮጵያ የሚመጣ ለውጥ በህዝቡ የሚከናወን መ



ሆኑን ስለተገነዘበ ነው፡ቪየትናምን ማስፈራሪያ ጭራቅ ሊያደርጉብን የፈለጉት ከእንግዲህ ወዲህ፡ወታደራዊ ግልበጣ አይነ ጥላ የጣለባቸው ቢኖሩ፣በበቅሎ በመረገጥ ፈንታ በታንክ መደፍጠጥን የመረጡ መሆን አለባቸው።

የታህሳሳዊያኑ እንቅስቃሴ ከሚመስገንባቸው ውጤቶች አንዱ፣ዘራፊዎቹን ሚኒስትሮች መፍጀቱ ሳይሆን፡—መቼም ሚኒስትሮች ቢረግፉ ሌሎች ሚኒስትሮች ይበቅላሉና—ዙፋኑን አጐናፅፎትና አሽሞንሙኖት የነበረውን "የነገስታቱ መለኰታዊ መብት" ተረት መሆኑን ማጋለጡና ማርከሱ ነው።ይኸ በእውነት ታሪካዊ እርምጃ ነው።ትንፋሽ እስኪያጥረን ሶስት ሺ አመት ወደኋላ ሳንሄድ፡ባለፉት አርባ አመታት እንኳ አፍዝ አደንግዝ ሆኖብን የነበረው የስብከት አስማት መርከሱ ራሱ፡ርእዮተአለማዊ ትግላችንን አቃልሎልናል።አሁን፡ሳንገላመጥ፡"ይሉኝታን" ሳንፈራ፣«ህዝባዊት ኢትዮጵያን እናቁም!» እያልን ልንጮህ እንችላለን።

የኢትዮጵያ ሰርቶ አደር ህዝብ—በከተማ ሆነ በገጠር—ጨቋኙን የንጉሰ ነገስት መንግስት መቋቋም ጀምሯል፤በክበቢው የሚደርሱበትንና ጉልተው የሚታዩትን ጥቃቶች በልዩ ዘዴና መሳሪያ በመከላከል ላይ ይገኛል።ነገር ግን አንድ መረሳት የሌለበት ቁምነገር አለ።ያለንበትን ሁኔታ ሊለውጥ የሚችለው ሪቮሉሽናዊ ርእዮተአለም ስጋ ለብሶ ወደ መሳሪያነት ሲለወጥ ብቻ ነው።በሌላ አነጋገር፣ሪቮሉሽናዊ ርእዮተአለም የምሁራን መራቀቂያ ከመሆን ወጥቶ ህዝቡ ህሊና ውስጥ ሲገባና ህዝቡም በሱው በመመራት በመሳሪያ ከጨቋኞቹ ጋር በሚያደርገው ቁርጥ ትግል ነው አሮጌውን ህብረተሰብ ደምስሶ፡በፍራሹ ላይ አዲስ ህብረተሰብን ሊገነባ የሚችለው።

በአሁኑ ወቅት ህዝቡ ወደአጥቂነት አድሀሪው መንግስት ወደተከላካይነት በሚሸጋገሩበት ድልዲይ ላይ ተሰልፈው ይታያሉ።ይኸውም፡ከአስር አመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ።በዚህ አኳኋን፣የአገራችን ህሊናዊና አንፃራዊ ሁኔታዎች ሊገጣጠሙ ምንም አልቀራቸው ለማለት ይቻላል።

ታህሳስ፡ሪቮሉሽናዊያንም ፀረ ሪቮሉሽናዊያንም ትልቅ ትምህርት ያገኙበት ታሪካዊ ድርጊት ሊሰኝ የሚገባው እንግዲህ ለዚህ ነው።

-V-

## አሻሻዮች ቢመጡ . . .

ያለንበት ዘመን፡የአለም ኢምፔሪያሊዝም የሚያጣጥርበት ወቅት ስለሆነ ይህ የበዝባዦች ስርአት ተፈንቅሎ እስከወደቀ ድረስ፡አንድም ህዝብ በሰላም ሊኖር አይችልም።እድሜ ለካፒታሊዝም ደግሞ፡ብቻውን መኖር አይቻለውም።እንግሊዛዊው ማተሪያሊስት ፈላስፋ፡ፍራንሲስ ቤከን፡«ባሩድ ሰውን ሁላ አስተካከለው» እንዳለው፡ካፒታሊዝምም እንኳን በአይን በስምም የማይተዋወቁ ህዝቦችን፡በፈተለው ኢኮኖሚያዊ ማግና ድር አያይዟቸው፡እድላቸውንና ተስፋቸውን አመሳስሎታል።ኢምፔሪያሊዝም የዘረፈው የህዝቦች ጥቅም በህዝብ እንዳይመነጩቅበትና በለው ላይ ለመጨመር ሲል የማይፈፅመው በደልና ግፍ የለም።አንድ ህዝብ የኑሮው እስትንፋስ የሆነው ኢኮኖሚው በኢምፔሪያሊዝም እስከተያዘበት ጊዜ ድረስ፡በባርነት እንጂ በአርነት ሊኖር አይችልም።ችግሩ የከፋውን ያህል ትግሉም ፅኑ ይሆናል።ለድል እስኪደርስ ግን፡ብዙ የትግል ደረጃዎች ማለፍ አለበት።የአገራችንም ሁኔታ ከዚሁ እድገት ህግ ነፃ አይደለም።

ብሄራዊ አድሀሪያንና የአለም ኢምፔሪያሊዝ—በተለይም የያንኪ ኢምፔሪያሊዝም—በኢትዮጵያ የፈጠሩት ሁኔታ ምን አይነት እንደሆነ ተመልክተናል።ይኸ ሁኔታ ግን፡ለኛ ብቻ የተመደበ ስላልሆነ፡ከመሰሎቻችን ከተበዝባዥ አለም ህዝቦች ጋር አዛምዶናል።«እኔን ያየህ ተቀጣ» እንዳለ ሁሉ፡በመከከላችንም «እኔን ያየህ ከኔ ተማር፡ካንተም እማራለሁ» አለ።

ህዝባዊ ትግል እስከልተጀመረ ድረስ፡የጊዜው የኢትዮጵያ ሁኔታ ለኩ ዴታ—ማለት፡ለመንግስት ፍንገላ—ምቹ ነው።ለማነውሳ የሚመቸው? ጠቃሚያቸው የሆነው ስርአት በህዝባዊ ማእበል ድምጥማጡ እንዳይጠፋባቸው ለሰጉ የገዢው መደብ አባላት ወይም አንዳንድ መጠገኛ እርምጃዎችን በመውሰድ በህብረተሰባቸው ውስጥ የተፈጠሩትን ቅራኔዎች ለማዳፈን ለተነሱ፡ከገዢው መደብ ለፈለቁ "በጐ አሳቢዎች" ነው።

የመጀመሪያዎቹ፡ያለው አስተዳደር ጥቅማቸውን ከአደጋ ላይ የሚ



ጥልበት ጊዜ መድረሱን አውቀው ይህንኑ ጥቅማቸውን ሲጠብቅላቸው የኖረውን መንግስት ገልብጠው ጭቆናቸውንና ይዞታቸውን በተሻለ የሚጠብቅላቸው መንግስት ያቋቁማሉ።(ግሪክ፡ብራዚል፡አያሌ የአፍሪቃ አገሮች።)

የኋለኞቹ፡ከተለያዩ የንኡስ ቡርዣዋ ርእዮተአለሞች የተዳቀለ የአስተዳደር ፍልስፍና አዘጋጅተው መንግስቱን ይገለብጡና ራሳቸውንና ድርጊታቸውን "ሪቮሉሽናዊ" ብለው ይጠሩታል።ዋናው አላማቸው ሊፈነዳ የተቃረበውን ቅራኔ ማስታገስ ስለሆነ፡ሪቮሉሽን ጠጋኝ እርምጃዎችን እየወሰዱ፡እውነተኛውን ህዝባዊ አብዮት ያዘገያሉ።(ግብፅ፡ሊቢያ፡ሲሪያ፡ኢራክ፡ወዘተረፈ።) እነዚህ ከገዢው መደብ ፊታቸውን ያዞሩት "በጐ አሳቢ" ሰዎች፡አላማቸውን አውቀውባቸው በሃሳብም ሆነ በአስተያየት ወይም በድርጊት የሚጋተሩዋቸውን እንደ ሰራተኞች ማህበራት መሪዎች ያሉትን የህዝብ ልጆች ከመስቀልና ከመረሸን አይመለሱም።(እነናስር ስልጣን ሲይዙ፡ግንባር ቀደም የነበሩትን የሰራተኛው ህዝብ መሪዎች፡በሚሰሩበት ፋብሪካ ደጃፍ ላይ ሰቅሏል።)

ጥቅማቸውን በበለጠ ለማደላደል የሚነሱት መቼም አድራጐታቸው የታሪክን ግስጋሴ ለመቀልበስ ስለሆነ፡በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን ቅራኔዎች ያገዝፋሉ እንጂ፡አያጠፏቸውም።አላማቸውም ይኸ አይደለም። ስለዚህ ሲገዙም በሃይልና በግፍ ነው።

"በጐ አሳቢዎቹ" ግን፡የፊተኛው መንግስት ለጨቆናቸው መደቦች ይልቁንም ለላብ አደሩ ህዝብ፡አንዳንድ መሻሻልን በማምጣት አስታግሰው፡ለብሄራዊ ቡርዣዋዚ መፈንጫ ሜዳ ይከፍቱለታል።ሚኒስትሩም ጠበብቱም የሚሾመው ከመሀሉ ነው።ሆኖም፡የአድሀሪያን ጥቅም ከኢምፔሪያሊዝም ጥቅም ጋር የተዋሀደ በመሆኑ፡አዲሶች መሪዎች ይህን ጥቅም ሲነኩ ጥላቸው በቀጥታ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይሆናል።ስለዚህ፡የኒዎ ኮሎኒያሊስት ግንኙነት በይኖር ኖር የቀረው አለም ቡርዣዋዚ የርእዮተአለምና የመደብ ዘመዶች ሊሆኑ ይችሉ የነበሩት አዲሶቹ መሪዎች ሳይወዱ፡ከፀረኢምፔሪያሊስቱ ሰፈር ይገባሉ።ድርጊታቸው ታሪካዊ የሚሆነው እንግዲህ ለዚህ ነው።(በዚህ በኩል ግብፅ ጥሩ ምሳሌ ናት።)

እንደዚህ አይነቱ "በጐ አሳቢ" የመንግስት ፍንገላ፡በአላማውም፡በ

ርእዮተአለሙም፣በሚወስዳቸው እርምጃዎች እጅግ ይወሰናል።በተለ ይ፣ለአዲሱ አስተዳደር እንቅፋት የሚሆኑት፣የአገሪቱ ኢኰኖሚ የኢም ፔሪያሊዝም ጥገኝነትና የመሪዎቹና የጭፍሮቹ ንኡስ ቡርዣዋ ጠባይ ና ቸው።በአንድ በኩል፣የድሮዎቹ ባለጥቅሞች፣ከኢምፔሪያሊስቶችና ከው ስጣዊ አድሀሪ ሀይሎች ጋር ተጋግዘው እንዳያጠፉት ወይም መንግስቱ ን ከገለበጡት ውስጥ አንዳንድ አካባቢዎች በነዚህ ፀረህዝቦች ተደግፈ ው ወይም ከቀደምቶቹ የተወረሱትን ሀብቶች ተከፋፍለው ለመብላት ከ ጅለው እንዳይገለብጡት ይሰጋል።በሌላው በኩል፣የወሰዳቸው እርምጃ ዎች ያላረኩት የላብ አደር ህዝብ እንዳይነሳበትና፣በራሱ አምሳል ሊፈጥ ረው ያሰበው አለም እንደእንቧይ ካብ እንዳይፈርስበት ይፈራል።ስለዚ ህ ወዳጅና ጠላት ሳይለይ ግራና ቀኝ ይመታል።እውነትም ስጋቱ ስጋት ነው።

ንኡስ ቡርጋዣ በተፈጥሮው፣እንጣጥ ባይና ሸውሻዋ በመሆኑ፣በህ ዝብ ስም ከተነሱት መሪዎች ውስጥ—ሁሉም እንኳ ባይሆኑ—በዙዎቹ በአዲሱ ሁኔታ ከብረው፣እሱም አልበቃ ብሏቸው፣ጥቅማቸውን ከወደቁ ት ከቀድሞዎቹ ገዢዎች –(ግልበጣው መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት አ ይደለም ብለን ነበር።)–ጥቅም ጋር አጋብተው፣በጋብቻም ተሳስረው፣አድ ሀሪ ኩ ዴታ ያደርጋሉ።ከዚያ በኋላ፣ለማደስ ተነሳንላት ያሉዋትን አገር "የሙዝ ሪፑብሊክ" አድርገው፣ራሳቸውም የአለም ኢምፔሪያሊዝም አ ጋሰስ ሆነው፣ለጌታቸው ለኢምፔሪያሊዝም በጫኑት የህዝብ ሀብት ልክ በሚወረወርላቸው ፍርፋሪ ግለሰባዊ ፍላጐታቸውን እያረኩ፣ሰርቶ አደ ሩን ህዝብ በአካልም በመንፈስም ያቆረቁዙታል።

ያ ግንባር ቀደም ድርጅትና ሪቮሉሽናዊ ርእዮተአለም በማጣት ህ ዝባዊ ትግሉን ለመጀመር የታጉለው ላብ አደር ህዝብ፣እንግዲህ ሌላ ምቹ ሁኔታ እስኪፈጠርለት ጊዜ ድረስ መጠበቅ ይኖርበታል፤ሪቮሉሽን ቀጠሮ የለውምና።

ለማጠቃለል ያህል፣በአሁኑ የአገራችን ሁኔታ፣የፍፁም አድሀሪያን ኩ ዴታ አደጋ አለ።ብሄራዊ ቡርጋዣዊ ግን፣በተጠቀሱት ምክኒያቶች ከ እንግዲህ ወዲያ እድል የለውም።ስለዚህ፣አድሀሪያኑ በኢምፔሪያሊዝም ታግዘው፣ላብ አደሩ ህዝብ በመላው አለም አራማጅ ህዝብ ተድገፎ ተ



ፋጧል።የመጀመሪያዎቹ ተከላካዮች፣የኋለኛው አጥቂ ሆኗል።ይህን ቁል ጭ ያለ ቅራኔ ሊያስውግድ የሚችለው ህዝቡ፣ከቅምጥ አጥቂነት ወደ ገ ቢር አጥቂነት ሲሸጋገር ብቻ ነው።ሌላ አማካይ መፍትሄ የለም።ሆኖም ህዝቡ ግንባር ቀደም ድርጅትና ሪቮሉሽናዊ ርእዮተአለም ያስፈልጉታ ል።ሁለቱ ነገሮች ግን ተደጋጋፊዎች ናቸው።ሁለቱም ነገሮች ከተሳኩ ሰ ርቶ አደሩ ህዝብ የትጥቅ ትግሉን ለመጀመር ወደሸንተረሩ ይገባል።ይ ኸ የትግላችን የመጨረሻ ደረጃ ግን፣ህይለስላሴ በቁመናው ሳለ መጀመ ር አለበት።ህይለስላሴ፣እኛን ሸጦ የሸመተውን ዝናና ክብር ይዞ ለዘልአ ለማዊ እረፍት መሄድ የለበትም።የሱ ዝና የፊውዳሊዝና የኤምፔሪያሊ ዝም ዝናና ክብር መሆኑን መርሳት የለብንም።ስለዚህ፣ማርክስ እንዳለው «ሰማያትን ለማናወፅ» እንነሳ!ከህዝቡ እንማር፣እናስተምረውም!ውሀ ውስጥ እንዳለ አሳ፣እኛም ህዝቡ ውስጥ እንግባ!የትግላችን አላማ ትክ ክለኛ ነውና እናሸንፋለን!

ጓድ፣በየሸንተረሩ የምንገናኝበት ቀንና ሰአት እንዳይርቅ ጠንክረን እንስራ!

---

(1) በጥቅም የተለያዩ መደቦች ከተፈጠሩ ጀምሮ
(2) ይኸና ወደፊትም በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የሚገጥሟችሁ አመተ ምህረቶች የተጠቀሱት እ.አ.አ. ነው።
(3) ኢንስቲቲዩሽኖች።አለቃ ኪዳነ ወልድና አውጉስት ዲልማን ን ተመልከት።
(4) Lipsky፣Ethiopia,its history,its people,its culture ገፅ 237 ተመልከት
(5) Lipsky፣ —"—  —"—  —"—  ገፅ 160 ተመልከት
(6) «የጥቂት ሰዎች ለገንዘብ መስገብገብና የአንዳንዶቹ በትውል ድና በማእርግ ተመክቶ ለስልጣን መሻማት ናቸው የኢትዮ ጵያን ህዝብ ግስጋሴ ያገዱት» ይላል የአስፋው ወሰን ንግግ ር።እንዴም ቢሆን፣የመሬት ጉዳይ አልተጠቀሰም።

## የ ታ ሀ ሳ ሱ ኩ ዴ ታ ለ ም ን ከ ሸ ፈ ?

ከፈቃደ ወርቅነህ

ታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ም. በኢትዮጵያ "እራሱን የቻለ" ኩ ዴታ
ተሞክሮ የመንግስት መገልበጥ ተግባር ተፈፀመ።አድማውን የመሩት
ከክብር ዘበኛ፣ከፀጥታ ክፍል፣ከፖሊስና ከሲቪል የተውጣጡ ጥቂት ሰዎ
ች ሲሆኑ፣እስከተወሰነ ጊዜ የመሳርያ ድጋፍ ያገኙት ከክብር ዘበኛ ትጥ
ቅ ነበር።

የኩ ዴታው መሪዎች አዲስ መንግስት አውጀው ለሶስት ቀናት ከ
ቆዩ በኋላ በጦር ሰራዊትና በአየር ሀይል ተደምስሰው ከዚህ በፊት በእ
ንደዚህ ያለ ሁናቴ ተደፍሮ የማያውቀው "ሰለሞናዊው" አገዛዝ ቀጠለ።
ህዝቡ ከመደናገርና ከገለልተኛነት አልፎ የያገባኛል ስሜት ለማሳየት ጊ
ዜ አላገኘም ነበር።

ስለ ኩ ዴታው ብዙ የተማታ ወሬ ይወራል።እስከሁን ድረስ በተ
ራማጅ አስተሳሰብ እውነቱን ገልጦ የሚያሳይ ትንተና አልተደረገበት
ም።ጉዳዩን አጣርቶ ትክክለኛ መልስ እንዲያገኝ ለማድረግ ሰፊ ጥናትና
ምርምር፣እንዲሁም ነፃ እጅ የማግኘትን እድል ይጠይቃል።የኢትዮጵ
ያን ዝብርቅርቅ የባላባቶች ፖለቲካዊ ታሪክ እያወቁ በኩ ዴታ ላይ ፍር
ድ ከማሳለፍ በፊት፣በእንደዚህ አይነት መንግስታዊ ለውጥ የሚገኘው
ን የኤኮኖሚና ሶሻል ነፃነት መመርመር ሳይሻል አይቀርም።

ኩ ዴታ (Coup D'etat) ከፈረንሳይኛ የተወሰደ ቃል ሆኖ የሚ
ያመለክተው በሃይል ተመርኩዞ ከመቀፅበት ከላይ በዱብዳ የሚመጣ
ን መንግስታዊ ለውጥ ነው።

ኩ ዴታ በነገስታት ቤተመንግስት ውስጥና በብሄራዊ ቡርጋዎ ፕ
ሬዚዴንቶች መኖርያ አካባቢም ጭምር ሲሰራበት ቆይቷል፤ይሰራበታል
ም።የኩ ዴታ አነሳስ ምንጩ ብዙውን ጊዜ በገዢ መደብ ውስጥ የሚ
ገኙ አባሎች ለስልጣን ሽሚያ ከሚያደርጉት ትግል የሚፈልቅ ነው።ብ
ዙውን ጊዜ ኩ-ዴታ የሚነሳው የህብረሰብን፣የሶሻልና የኤኮኖሚ አቋ
ም መሰረት ለመለወጥና ህዝባዊ ለማድረግ ሳይሆን የመሪዎችን መልክ
ና ስም ቀይሮ አገዛዙን በማራዘም የመደብ ይዞታን ለመጠበቅ እንደሆ



ነ አይጠረጠርም።ኩ ዴታ በሌላ ኩ ዴታ በቀላሉ ሊተካ ይችላል።በህዝ
ባዊ ትግል ተመርቶ አሮጌውን ስነስርአት በአዲስ በመለወጥ የሚገነባ
ውን የህዝብ አስተዳደር ኩ ዴታ ሊያናጋው አይችልም።ሬቮሉሽን ከዝ
ቅተኛ ደረጃ ቀስ ብሎ ተወልዶ ገስግሶ በማደግ የሚጠነክር ምንም አይ
ነት ሃይል የማያወዛውዘው የህዝብ ፍላጐት ሲሆን፣ኩ ዴታ ለጊዜው የ
ሚያስደነግጥ፣ከላይ ተነስቶ መንምኖ የሚወድም የጥቂቶች ምኞትና ጥ
ረት ነው።

ይሁን እንጂ አውቆም ሆነ ሳያውቅኩ ዴታ በህብረሰብ የሶሻልና ኤ
ኮኖሚ ኑሮ ውስጥ እግረ መንገዱን የሚያስቀረው መልካምና መጥፎ
ነገር አለው።

የታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ም. ኩ ዴታ መመርመር የሚገባው ከዚ
ህ ተነስቶ ነው።ኢትዮጵያ ብዙ ኩ ዴታዎች ከሚፈራረቅ ባቸው አገሮች
ለየት ያለ ታሪክ ስላላት ኩ ዴታውም በዚሁ መጠን ትንሽ ለየት ያሉ ጠ
ባዮች ይኖሩታል።ይህን ነጥብ ለማብራራት ያህል የሱዳንን እ.አ.አ. የ
1968 ዓ.ም. ኩ ዴታ ከታህሳስ አምስቱ ኩ ዴታ ጋር እናወዳድርና ልዩ
ነቱን እንመልከት።

ለሱዳን ኩ ዴታ አዲስ ነገር አይደለም።እንደዚሁም በርከት ያለ የ
ፖለቲካ ልምምድ አድርጋለች።ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ከኢትዮጵ
ያ የበለጠ የረጅም ጊዜ የትግል ልምምድ አላት።እ.አ.አ. በ1956 ዓ.ም
ነፃ ስትወጣ የቡርጋዎ ዴሞክራሲን ቀምሳለች።ትንሽ ቆይታ ከቡርጋዎ
ዴሞክራሲ ወደ "ሚሊቴሪ ዲክቴተርነት" ገባች።እ.አ.አ. በ1964 ህዝብ
የተካፈለበት ተቃውሞ ሰልፍ ተደርጎ ከወታደራዊ አገዛዝ እንደገና ወ
ደጥንቱ የቡርጋዎ ዴሞክራሲ ተመለሰች።እ.አ.አ. በ1968 ጥቂት የጦር
መኰንኖች በኩ ዴታ ለውጥ ማድረጋቸውን አስታውቀው፣ፀረኢምፔሪ
ያሊስትና ፀረፊውዳል መንግስት መሰረትን አሉ።ሱዳን፣ስም ብቻ የያዘ ቢ
ሆንም፣የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው፣ሰራተኛውንና ገበሬውን እመስላለሁ
የሚል ማህበር ነበራት።

ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ሁሉ ሁናቴ አልነበረም።የኢትዮጵያ ታሪክ
ረጅምና የተዘበራረቀ ለመሆኑ በሰፊው ቢወራም፣አንድ በእርግጥ የማያ
ከራክር ቁምነገር ይገኝበታል።ኢትዮጵያ በባርያ ንግድ፣በመሬት ይዞታና

በሃይማኖት ቁራኛነት ላይ የተመሰረተ ስርአቸ ጠብቃ እስከ ቅርቡ ድረ
ስ መቆየትዋ ነው።ከታሪኳ አብዛኛው የነገስታት፣የመሳፍንትና የቤተክህ
ነት ወይም የባላባታዊ አገዛዝ ነው።

ላይላዩን ሲያዩት ካሳ ከዝቅተኛ የህብረተሰብ ዘርፍ ተነስቶ ከፍተ
ኛውን መደብ በመዋጋት አንድ ታሪክ ለመጣል የሞከረ ይመስላል።ነገ
ር ግን እ.አ.አ. በ1855 አፄ ቴዎድሮስ ተብሎ ዘውድ በጫነ ጊዜ ተያይ
ዞ የመጣውን የበሰበሰ ስርአት ሲከተል የመደብ ምልክቱን እንደካደ አ
ይጠረጠርም።

እ.አ.አ. በ1896 የኢትዮጵያ ህዝብ የጣልያንን ዘመንዊ ወታደር
አድዋ ላይ ድል ሲመታ ለአገሪቱ አንድ ትልቅ የታሪክ ቅርስ ሰጥቷል።
ብዙ ሰዎች ይህን ህዝባዊ ድል ለሚኒሊክ ይሰጣሉ።ወጉ የተገላቢጦሽ የ
ሚሆነው ሚኒሊክ ኤርትራን በተሸነፈው የጠላት ግዛት ስር እንድትወ
ድቅ ሲያደርግ ነው።

ከዘውዲቱ መሞት በኋላ እ.አ.አ. በ1930 ሃይለስላሴ ዘውድ ጭኖ
የኢትዮጵያ ገዢ ሆነ።ፋሺሽት ኢጣሊያ ለሁለተኛ ጊዜ እ.አ.አ. በ1935
ኢትዮጵያን ስትወር ከህዝቡ ጋር ተሰልፎ እንደመዋጋት የዘረፈውን ዘ
ርፎ፣ቤተሰቡንና ቤቱን ጠቅልሎ ወደእንግሊዝ አገር ጠፋ።ጠቅላላ የአ
ለም ወታደራዊ ሃይል ሚዛን ተለውጦ ወደ ፀረፋሺሽቶች ከማድላቱና
የኢትዮጵያ አርበኞች ከደረጉት ከፍተኛ ተጋድሎ የተነሳ እ. አ. አ. በ
1941 ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ስታስመልስ፣የብዝበዛቸው መሳርያ አድርገ
ው ይጠቀሙበት የነበሩትን ኢምፔሪያሊስቶች ተከትሎ መጥቶ በህዝብ
ገንዘብ ገዝቶ ይፈነጥዝበት በነበረው "የፈርዌል" ቤተመንግስት ውስጥ
እንደገና ጥገኛ ባላባታዊ አገዛዙን ቀጠለ።

ታሪኩ ለታሪክ መርማሪዎች ይቆይ።እዚህ ሁሉ ዙረት ውስጥ የተ
ገባው በዚህ ረጅም የባላባታዊ ዘመን ብሄራዊ የፖለቲካ ንቃት ምን ያ
ህል ነበር? ብሎ ለመጠየቅ ነው።ነገር ላለመጉተት ብዙ አልነበረም።እ
አ.አ. 1867-8 የናፒር ጦር ዘመቻና የአድዋው ጦርነትም ተራዝሞ የ
ሚጓዝ ብሄራዊ የፖለቲካ ንቃት አላስቀሩም።ቢያስቀሩም የነበረውን አ
ገዛዝ ሃይልና የገዢዎችን ዝና ከማጋነን ይልቅ ህዝቡ ምርመራና ጥያቄ
እንዲያደርግ አልረዱም።



የኢትዮጵያ ዘመናዊ የፖለቲካ ቅርፅ መያዝ የጀመረው እ.አ.አ
በ1935 የፋሺሽት ወረራ ወዲህ ነው።በጦርነቱ ገዢው መደብ ተሸንፎ
አገሪቱ(መሀከለኛ ቦታዎችና ከተማዎች)፣ለአጭር ጊዜም ቢሆን፡ተወረ
ረች።የፋሺሽት ግፍ ህዝቡ በሰፊው ቀመሰው።ከአድዋው ድል የተገኘው
ብሄራዊ ኩራት ለጊዜው ተነካ።ቢሆንም ህዝቡ በየቦታው የፋሺሽትን
ሀይል በትጥቅ መቋቋሙን አልተወም።ስለዚህ ብሄራዊ የመንፈስ ንቃ
ት፣ባይዳብርም ቅሉ፡ስር መያዝ ጀመረ።ለምሳሌ፣በሃይለስላሴ ተመልሶ የ
ኢትዮጵያ ገዢ መሆን ለነፃነት የተዋጉ አርበኞች ተከፋፈሉ።አገሪቱን
ከድቶ ጠፍቶ የነበረ ሰው እንዴት ተመልሶ ይገዛታል በማለታቸውና በ
መሳርያ ጭምር በመቃወማቸው ጠላትን ያድኑ የነበሩ አገር ወዳድ አ
ርበኞች እንደነ ማሞ ሀይሉና በላይ ዘለቀ ያሉ ተሰቀሉ።ከዚያን ጊዜ ጀ
ምሮ ስንቱ አገር ወዳድና ለውጥ እፈልጋለሁ ባይ ህይወቱን አጥቷል።

የእርባታ ሀይሎች ከለመጉልመሳቸው የተነሳ(ዘመናዊ እርሻ ባለ
መስፋፋቱ፣ኢንዱስትሪዎች ባለማደጋቸው፣መሃይምነት በማጥለቅለቁና
የባህል እድገት እርምጃ ወደኋላ በመጐተቱ) የመደብ ህሊና በአገራ
ችን ለብዙ ጊዜ ቀዝቅዞ ቆይቷል።ከዚህም የተነሳ በበዝባዡ ገዢ መደብ
ና በተበዝባዡ ተገገር መደብ መከከል መሰረታዊ ቅራኔዎች ቢኖሩም ደ
ጋግመው በሀይል ሲጋጩ አልታዩም።በተጨማሪም እ.አ.አ. በ1917 በ
ሩሲያ የተደረገው መሰረታዊ ለውጥ ያስገኘው ህዝባዊ ድል የአለምን
የእርባታ ግንኙነት ሲያናውጥ ኢትዮጵያን ወሬው እንኳ አልገረፋትም።

ይሁንና ከእግዲህ ወዲህ ወደኋላ መመለስ አልተቻለም።ለልዩ ተ
ግባር ታስቦም ቢሆን በዝቅተኛ ደረጃ የተገኘው ትምህርት ለንቃት መ
ሳርያ ሆነ።ሃይለስላሴ ከጠፋበት አገር ተመልሶ አገዛዙን ከቀጠለ ጊዜ አ
ንስቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ ነው የማይባል ጭቆና፣ግፍና በደል ስለበዛ
በት በበለጠ ሮሮውን ማሰማት ጀመረ።የንጉሰ ነገስቱ መንግስት አረመ
ኔያዊ አገዛዝ የጥቂት ጨቋኝ በዝባዦችንና የአብዛኛውን ተጨቋኝ ህዝ
ብ የኑሮ ልዩነት እያጉላ ማሳየት ቀጠለ።አንዳንድ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎ
ችም መላወስ ጀመሩ።ከታህሳስ 5 ቀን 1953 ዓ.ም. ኩ ዴታ ትንሽ ቀደ
ም ብሎ በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት በመሬት አራሹና በገዢው ቤተሰብ የ
ጦር ሃይል መከከል የተደረገው የጠብ መንጃያ ውጊያ አንድ ቀዋሚ ማ

ስረጃ ነው።

ለሪቮሉሽናዊ ትግል የሚያስፈልጉት ሁኔታዎች እያሉ፣ሰራተኛው-
ና ገበሬው በመደብ ትግሉ የሚመራ ግንባር ቀደም ድርጅት ሳይፈጥር
ተበታትኖ በሚፈራገጥበት ወቅት የታህሳስ 5፣1953 ኩ ዴታ ታወጀ።ኩ
ዴታውን የማፅደቅ ጥያቄ እዚህ ውስጥ አይገባም።የሚያስፈልገው ለኩ
ዴታው አመጣጥ ምክንያት የሆኑትን አይነተኛ መዘዞች መመርመር፣መ
ሪዎቹ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ አቋም ውስጥ የነበራቸውን መደባዊ ቦታ
በደንብ ለመረዳት መሞከር፣በኩ ዴታው ምክንያት በህብረተሰቡ የታሪ
ክ ጉዞ ላይ የወደቁ ነጥቦች ቢኖሩ ጠባያቸውን ማጥናት፣በመጨረሻም ኩ
ዴታው የከሸፈበትን ምክንያትና ወደፊትም ኩዴታ ለኢትዮጵያ ህዝብ
የሶሻልና ኤኮኖሚ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት እንደማይችል አዲሱ
ትውልድ እንዲገነዘበው ማድረጉ ነው።

ለሶስት ቀናት ብቻ የቆዩት የታህሳስ 5፣1953 ኩ ዴታ መሪዎች ስ
ለአዲሱ መንግስት የስራ እቅድ አዋጅ ማሰማታቸው ይታወሳል።ትክክ
ለኛ ገፁን ለታዛቢ ለማቅረብ ያህል አንዳንዱን ነጥቦች ባጭሩ ከዚህ በ
ታች ማስፈሩ ይጠቅማል።

1. ኢትዮጵያ በቅርቡ ነፃ ከወጡ አፍሪቃ አገሮች እንኳ ወደኋላ መ
   ቅረቷን በማብሰር በአለም የነበራትን ጥንታዊ ቦታ ማስገኘት
2. ኢንተርናስዮናላዊ ግዴታዎችን ማክበርና ከወዳጅ አገሮች ጋር
   ያለውን ግንኙነት መቀጠል
3. የውጭ ካፒታል ለአገሪቱ ደህንነትና እድገት የሚረዳ ከሆነ(!!!)
   አለማስቸገር
4. ህዝቡ የኑሮ ደረጃውን እንዲያሻሽል አዳዲስ ፋብሪካዎችንና ኢ
   ንዱስትሪዎችን ማቋምና እንዲሰራ ማድረግ
5. እርሻ የአገሪቱ ኤኮኖሚ መሰረት ስለሆነ፣የአራሾች ምርት እን
   ዲሻሻል እርዳታ መስጠት
6. የኢትዮጵያ ነጋዴ ንግዱን አሻሽሎ ለአገሩ ኤኮኖሚ እድገት
   እንዲያበረክት እርዳታ ማድረግ
7. ብዙ ወጣት ኢትዮጵያኖች በየመንገዱ ስለሚዘረሩና ትምህርት
   ስለሚያስፈልጋቸው እንዲያገኙ ማድረግና ስራ ላጡት ስራ ማ



   ስገኘት
8. የኢትዮጵያ ትልቁ ችግር የቴክኒክ እውቀት ስለሆነ፣የትክኒክ ት
   ምህርት ቤቶች ከፍቶ ችግሩን መቋቋም

የኩ ዴታውን መምጣትና ሊከተል ይችል የነበረውን ፖለቲካዊ
ለውጥ በመገመት ብዙ የውጭ አገር ፀሀፊዎች አስተያየታቸውን ሰጥ
ተዋል።.

ክሪስቶፈር ክላፕሀም MODERN AFRICAN STUDIES በመባ
ል በሚታወቀው መፅሄት ውስጥ፣እ.አ.አ. መጋቢት 1968 ዓ.ም. ቁጥር
6 ላይ «የታህሳስ 1953 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኩ ዴታ» በሚል አርእስት
በፃፈው ድርሰት መግቢያ ላይ እንዲህ ይላል።

«.....ከሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ጋር ስትነፃፀር ኢትዮጵያ በ
ቅርቡ አስር አመታት ውስጥ ስልቹ የሆነ የመንግስት እርጋታ አድርጋ
ለች።ሃይለስላሴ ከብዙ ክፍለ ዘመናት በፊት እንደነበረ ተያይዞ የመጣው
ን ንጉሳዊ የፖለቲካ ስርአት ጠብቆ ይገዛል።ባለፉት 25 አመታት ስል
ጣኑን በሃይል ሊፃረር የቻለው በታህሳስ 1953 የተሞከረው ኩ ዴታ ብ
ቻ ነው።....»

የኩ ዴታውን ትርጉም በማለት አስተያየቱን ቀጥሎ «....እዚ
ህ የምንመረምረው ይህን ነጠላ፣አጭርና ከመቅፅበት መንግስቱን ለመ
ገልበጥ የተወሰደውን እርምጃ ነው።ምንድነው ጠቃሚነቱ? ምን አይነ
ት ጥያቄዎች መጠየቅ አለብን?.....

....ከሁሉ አስቀድሞ የንጉሳዊ አገዛዝ መሰረት የሆነውን የመ
ኳንንቱን፣የቤተክህነቱንና የጦር ሰራዊቱን ሀይል ያሩልሳል።አድራጎቱ
ም የነበረው መንግስት ምን መሆኑን ያስረዳናል።በሌላ በኩል ደግሞ በ
አገሪቱ ውስጥ በጦር ሃይሉና አዲስ አበባ በሚገኙ ምሁራኖች አካባቢ
ጥሎት የሄደው እያደገ የሚሄድ ፖለቲካዊ ንቃት አለ።....»

ግሪን ፊልድ ስለኢትዮጵያ በደረሰው መፅሀፍ ስለዚህ ኩ ዴታ ሲ
ያወጋ የሚከተለውን አስተያየት ይሰጣል።

«....በኢትዮጵያ ረጅም ታሪክ፣ሴራዎች፣እውከቶችና ፖለቲካ
ዊ ግድያዎች ነበሩ።ነገር ግን ሳይሳካ ባጭር የተቀጨው የ1953 ሪቮሉ
ሽን አንድ ከፍ ባለመንገድ ይለያል።አድመኞቹ የፈለጉት ብሄራዊ መ

ሪዎችን በሌላ ለመተካት ብቻ ሳይሆን የመንግስቱን አቋም ለመለወጥና ለማደስ(!!) ነበር።በታህሳስ 1953 ዓ.ም. የአፍሪቃ "የለውጥ ነፋስ" ከፍታ ያለውን የኢትዮጵያን ተራራ እንኳ ሊደርስ ቻለ። . . . »

ስለታህሳሱ ኩ ዴታ ከግረን ፊልድ ጋር የሚስማሙ ብዙዎች ናቸው።በቀላሉ ሁሉም ለማሳየት የፈለጉት የታህሳሱ ኩ ዴታ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ "የሬቮሉሽን ወይንም የመሰረታዊ ለውጥ" ሙከራ መሆኑን ነው።

የኩ ዴታው ተፈጥሮ ጠባይና የአዋጅ ፍሬነገር ተጨምቆ ሲመረመር ከፍብሎ ለምሳሌ ያህል ከተጠቀሱት አስተያየት ሰጪዎች፡በተለይ ግሪን ፊልድና መሰሎቹ የሚያቀርቡልንን አይደገፍም።ሬቮሉሽን ማለት እርጎውን ባላባታዊ ስርአት ነቅሎ በአዲስ የተለየ ስርአት መተካት ከሆነ፡እረ በየትኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ነው ብዙ ሬቮሉሽኖች ተፈፅመው የነበር? እንደዚህ ያለ የሀሳብ አቀራረብ የተመልካችን አስተያየት የሚያወናብድ፡"በኒዮ ኮሎኒያል" ጥቅም የተጋረደ የቡርዢዋ እንደራሴዎች ግምት ነው።

የስራ ፍሬው ሊመዘን እድል ያላገኘው የታህሳስ ኩ ዴታ ምንም ከዚህ በፊት ከሚታወቁት፡በገዢዎች ቤተመንግስት ውስጥ ከሚታዩት ተንኮሎችና ኩ ዴታዎች(ለምሳሌ ሃይለስላሴና ኢያሱ) በመጠኑ የሚለይ ቢመስልም፡ከህዝቡ ሬቮሉሽናዊ አለም ጋር ግንኙነት አይኖረውም።የህዝብ ሬቮሉሽን ትርጉም(concept) ከቡርዣዋ ሬቮሉሽን ትርጉም(concept) ፍፁም ይለያል።የብሄራዊ ቡርዣዋ ሬቮሉሽን ከባላባታዊ አገዛዝ ጋር ሲነፃፀር ተራማጅ ቢመስልም፡ቅርፁና ይዘቱ አንድ አይነት አይደለም።በአሁኑ የታሪክ ምእራፍ ብሄራዊ ቡርዣዋ(ያውም ካለ) መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም።የብሄራዊ ቡርዢዋ ሬቮሉሽን ጥገናንና አንዳንድ መሻሻልን ያስከትላል።ፍልስፍናው፡ርእዮተአለሙ፡ህጉ፡ወጉና፡ . . . . ወዘተ. በዚሁ መጠን ሊሻሽ ይችላል።ይህም መደረግ ያለበት የቢሄራዊ ቡርዣዋውን ይዘት ለማጠንከር ነው።የፓለቲካና የእርባታ ሃይል መቆጣጠር ስልጣን በስሩ ይወድቃል።የአገሪቱን ጥገኛነት ግን ሊያስቀር አይችልም።ስለዚህም፡የሀብት አከፋፈል ልዩነት፡ማለት ድህነትና ባለፀጋነት ጐንለጐን እንዲኖሩ ይገደዳሉ።እንዲያውም ጌታው የገቢው ምንጭ



እየዳበረ ሲሄድ፡አብዛኛው ድሀ እየቆረቆዘና እንደሚደረገው መሻሻል መጠን ብዝበዛው እየባሰበት ይሄዳል።ህዝባዊ ሬቮሉሺን የዚህ ተቃራኒ መሆኑ በጊዜ መታወቅ አለበት።

ያምሆን ይሁ፡በዛም አነሰ፡የታህሳሱ ኩ ዴታ እርግጥ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ታሪካዊ ጉዞ ላይ ፖለቲካዊ ንቃት ፈጥሯል።የሃይለስላሴን ፋሽሽታዊ አገዛዝ እያወቁ ኩ ዴታ አድራጊዎቹን መውቀስ አይገባም።ባላባታዊውን አገዛዝ በመሰላቸው ገልብጠው ለኢትዮጵያ ዘመናዊነት መስሎ የታያቸውን አውጀዋል።ተሳክቶላቸው ቢሆን ኑሮ ግባቸውን በበለጠ ልናውቅ ይረዳን ነበር።

ከኩ ዴታው መሪዎች አንዳንዶቹ የመሰረታዊ ለውጥ ምኞት እንደነበራቸው አይካድም።አገር ወዳድነታቸውም አይጠረጠርም።እዚህ ግን ለማሳየት የተፈለገው፡ኩ ዴታ በተፈጥሮው የሚነሳው በነበረው ስርአት ሀይል ላይ ተመርኩዞ ስለሆነ፡ከመሪዎቹ አንዳንዶቹ ፍላጐትም ቢኖራቸው መሰረታዊ ለውጥን ለማምጣት እንደማይችል ነው።

መሰረታዊ ለውጥ ያለውን ስርአት መሪዎች ጥቅም ይፃረራል።ያለው ሃይል የነዚህ ገዢዎች መሳርያ ሲሆን ዋና ጥረቱ ደግሞ ይህን ጥቅም መከላከልና መጠበቅ ነው።የጠቅላላው ሃይል ዋና ምኞት ያለውን ማቆየት ከሆነ፡አንዳንድ ቅን ሰዎች በመመኘታቸው ብቻ በዚህ ሃይል አማካኝነት እንዴት አድርጎ መሰረታዊ ለውጥ ሊመጣ ይችላል? የራሱን መቃብር በራሱ(መልካም ፈቃድ) የሚቆፍር አለን? ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት መሰረታዊ ለውጥ ሲሆን፡ይህም ሊመጣ የሚችለው ሰፊው ህዝብ በሚከፈልበት ፖለቲካዊና የመሳርያ ትግል ብቻ መሆኑ ለተራማጆች አይሰወርም።ምናልባት ኩ አድራጊዎቹ በጊዜያቸው ይህንን አልተረዱም ይሆናል።ሰው ከሞተ በኋላ እንደገና ወደዚህ አለም ለመመለስ ቢችል ኑሮ ከመሪዎቹ አንዳንዶቹ ዛሬ በሃሳቡ እንደሚስማሙና ከህዝቡ ጋር በመሰለፍ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ነፃነት ብልፅግናና ደስታ ለመዋጋት እንደማይቆጠቡ አይጠረጠርም።በፖለቲካ እምነታቸው ሳይሆን፡በቆራጥነታቸው ለወጠኑት ግብ እስከ መጨረሻው በጀግንነት መሞታቸው የሚደነቅ ነው።

የኩ ዴታው አንጐልና ቀያሽ ገርማሜ ንዋይ መሆኑ ከሚታመኑ

ምንጮች በተገኘው ዜና ሊታወቅ ተችሏል።ገርማሜ በህይወቱ ሳለ ር
ህሩህ፣እራሱን ጨቁና ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያኖች የሚቆረቆር ሰው ለ
መሆኑ በሃይለስላሴ የግፍ አስተዳደር ስር ሁኖ የፈፀማቸው ሰብአዊ ተግ
ባሮች ይመሰክራሉ።ገርማሜ ከኩዴታ መሪዎቹ ሁሉ በጠባይም ሆነ በ
ፍላጐት አይመሳሰልም።ምናልባትም በዚህ ምክንያት ይሆናል ወደመ
ጨረሻው ገደማ በእርሱና በሌሎቹ፣በተለይ በወንድሙ በመንግስቱ ንዋ
ይና በእሱ መካከል ብዙ ያለመግባባት ተፈጥሮ ነበር የሚባለው።ከቆፍ
ጣናነቱና ከጠንካራ ጠባዩ የተነሳ ተይዘው የነበሩትን ሚኒስትሮች ለመ
ረሸን ከወታደሮቹ ይልቅ እርሱ መሪነቱን እንደወሰደ ይነገራል።

ባጭሩ የኩ ዴታው ፖሊሲ የተመራው ባላባታዊ አገዛዝንና የበ
ላይ ደጋፊውን ኢምፔሪያሊዝምን ላለማስቀየም ነበር።በፕሮፓጋንዳቸው
ውስጥ ሃይለስላሴንም ሆነ የንጉሰ ነገስቱን ስርአት የሚወነጅል አንዳችም
ቃል አላሰሙም።የመንግስቱን አረመኔያዊ አገዛዝና ሌብነት አብራርተ
ው አላስረዱም።የኢትዮጵያ መሬት ተቀርሶ ለኢምፔሪያሊዝም፣በተለይ
ለአሜሪካን ኢምፔየያሊዝም፣የወታደር ሃይል ማስፈርያ እንዲሆን መሸ
ጡን ህዝባዊ መግለጫ አልሰጡበትም።ፖለቲካዊ ስልጣን ወደህዝቡ የ
ሚተላለፍበት ህጋዊ ፓርላሜንት ይቋቋም እንደሆነ አላሰሙም።አለበለ
ዚያም ሰራተኛውን፣ገበሬውንና ሌሎች ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስ
ት የሆኑ ሀይሎች እንደራሴዎች የሚካፈሉበት ጊዜያዊ የሆነ ብሄራዊ
ሪቮሉሽናዊ መንግስት እንዲቋቋም አላሰቡም።ሌላው ቀርቶ የብሄራዊ ቡ
ርዡዋ ሪቮሉሽን በተስፋ የሚያውጃቸውን፣እንደህግ መንግስት መለወጥ
የሰው ልጅ እኩልነትና መብት፣የንግግር፣የመፃፍ .... ነፃነቶች፣ምርጫዎ
ች ወደ ሲቪል አገዛዝ መመለስ የሚሉ በህዝብ ዘንድ ተወዳጅነት ሊኖ
ራቸው የሚችሉ ቃላቶችን እንኳ አላሰሙም።የስራ ፕሮግራማቸው ለዘ
ብ እንደማለቱ መጠን ግልፅ አልነበረም።ፕሮፖጋንዳቸው በደ ፈናው
«አሮጌው መንግስት እርምጃ አላደረም» ነው የሚለው።በዚህ መንፈስ
ሲታይ ኩ አድራጊዎቹ ፈጥረውት የነበረው መንግስት ምን መልክ እን
ደሚኖረው እኳን ገና የቆረጠ አይመስልም።

እረ ለመሆኑ ይህ ሁሉ ስህተት እንዴት ሊመጣ ቻለ? ብዙ ሰዎች
ኩ ዴታውን በመደገፍ፣ህዝቡ ደደብ ነው፤ዝም ብሎ ተኝቶ ነበር ይላሉ።



ክሱ ትክክል ይሆን? በፍፁም፣አይደለም።ያለማስተዋል የሚወረወር አ
ስተያየት ነው።ህዝቡ ደደብ አይደለም።በማያውቀውና ባልተረዳው ነገር
እንዴት ብሎ፣ለማንስ ብሎ ይንቀሳቀስ?

ከኩ ዴታው የምንቀስመው ዋና ትምህርት ይህ ነው።—የኩ ዴታ
ተፍጥሮ ጠባይም መታወቅ ያለበት እዚህ ላይ ይሆናል።— ድንገት ይ
መጣል፣ድንገት ይወድቃል፤ህዝቡ አይሳተፍበትም፤ሊሳተፍበትም አይች
ልም፤ከመጀመሪያው መች እንዲሳተፍበት ታቀደና! ኩ ዴታው ባ
ጭሩ ሊቀጭ ከቻለበት ዋና ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው።

---

## «አዲሱ መንግስት» በየሀገሩ ለሚገኙ ኤምባሲዎች ያስተላለፈው ቴሌግራም

«አዲሱ መንግስት» በዚያች አጭር እድሜው ውስጥ ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ፣በየአገሩ ለሚገኙ ኤምባሲዎች "የመንግስቱን ለውጥ" የሚያበስር ቴሌግራም መላክ ነበር።የቴሌግራሙ ይዘት በከፊል እንዲህ ይላል፡—

«...በልኡል አልጋ ወራሽ መርእድ አዝማች አስፋው ወሰን መሪነትና በመላው ህዝብና በጦር ሰራዊቱ ድጋፍ ሰላማዊ የስልጣን ለውጥ ተደርጓል።የለውጡ አላማ በመንግስቱ መስሪያ ቤቶች ውስጥ ተስፋፍቶ የሚገኘውን ብልሹነት ለማጥፋትና የአገሪቱን ጠቅላላ ደህንነት የሚጠብቁ ድርጅቶችን ለማቋቋም ነው።የአዲሱ መንግስት የውጭ ፖለቲካ ከማንኛውም አገር ጋር በእኩልነት ላይ በተመሰረተ የወዳጅነት ግንኙነት ይመራል።»

በአገራችን ብዙውን ጊዜ የአምባሳደርነት ሹመት የሚሰጠው ከአገዛዙ "ግድም" እንዲርቁ ለተፈለጉ ሰዎች ነው።ይህ ከብዙ አመታት ጀምሮ ለብዙዎች ግልፅ ሆኖዋል።ለተሹዋሚዎች ጭምር። የአዲሱን መንግስት ቴሌግራም ከተቀበሉት አምባሳደሮች አብዛኞቹ "በሹም ሽረቱ" አማካይነት ከአዲስ አበባ "ገለል" የተደረጉ የገዢው መደብ "ፍየሎች" ናቸው።

በቅርብ የሚያውቋቸው እንደሚያወሩት አንዳንዶቹ በአገሪቱ ወደኋላ መቅረት፣በአስተዳደሩ መበላሸት፣በፍትሁ መዛባት፣በሃይለሰላሴ ፈላጭ ቆራጭነት ከልክ በላይ በመብገን «ለውጥ» ፈላጊዎችና ተጠባባቂዎች ነበሩ።አልፈው አልፈውም በአገዛዙ ላይ የመረሩ ቃላትን ሳይሰነዝሩ አልቀሩም።

ታዲያ ይህ ቴሌግራም ሲደርሳቸው ምን እርምጃ(አቋም) ወሰዱ? የአብዛኞቹ አልታወቀም።የነፍሱን አቅጣጫ ለመጠበቅ ይሆን፣ወይም የተቃውሞ ድምፃቸውን (አንዳንዶች ተቃውሞአቸውን አሰምቷል ይባላል) ለማሰናዳት ከምላ ጐደል ሁሉም በማድባት ላይ እንዳሉ «የአዲሱ መንግስት» እድሜ ባጭሩ ተቀጨ።



ቴሌግራሙ እንደደረሰ ያለአንድ ውልውል በግልፅና በፍጥነት አዲሱን መንግስት ያወቁት በስዊድን የነበሩት አምባሳደር፣አቶ ተፈሪ ሻረው፣ብቻ ናቸው።የአዲሱ መንግስት መቆምና የተቀበሉትም መሆናቸውን በገሀድ በጋዜጣ ሸንጐ ላይ አሰሙ።"የምስራቹን" ለመስማት ከተሰበሰበው ህዝብ ጋር «ለነፃነት፣ለዴሞክራሲ ...» "ጥዋቸውን" ከነሱ በኋላ የሚከተለውን ተሌግራም "ለአዲሱ መንግስት" የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አስተላለፉ።

«...ቴሌግራማችሁ እንደደረሰኝ አረጋግጣለሁ፤በኢትዮጵያ ህዝብና በጦር ሰራዊቱ ድጋፍ፣በልኡል አልጋወራሽ አስፋው ወሰን መሪነት የተቋቋመውን መንግስት የምቀበለው በክብር ነው።

«መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ መብቶቻችንን ረግጠ ከያዘው የጭቆና ቀንበር መገላገላችንን በመስማቴ እደሰታለሁ።ይህንኑ ዜና በዴሞክራሲ ለሚተዳደሩት የእስካንዲናቪያ አገሮች አስተላልፌ አዲስ የተቋቋመውን እርግጠኛ ዴሞክራሲያዊ መንግስት እንዲያውቁ አሳስባቸዋለሁ።

«ይህ ጊዜው ያለፈበት የጥፋትና የስቃይ፣የውሸት ፕሮፓጋንዳ መሰረቱ የሆነ ፈላጭ ቆራጭ መንግስት ሰብአዊ መብቶችን እስከጠቀ ድረስ(!) ወደአገሬ እንደማልመለስ ካሁን በፊት ለአንዳንድ ሹማምንቶችና በአውሮፓ ለሚገኙ በርከት ያሉ ወጣቶች ነግሬ ነበር።

«አሰቃዩ የኢትዮጵያ መንግስት ህገ መንግስቱን እስከለወጠ ድረስ(!) በገዛ ፈቃዴ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎችንና ንብረቱን ትቼ የኢትዮጵያ ህዝብ የተጫነበትን ቀንበር ለመካፈል መርጬ ነበር።

«ስለዚህ አዲሱን መንግስት የማወቅና ከሱም ጋር የምተባበረው ከትልቅ ደስታ ጋር ነው።»(የማድነቅ ምልክቶቹና መስመሮቹ የመፅሄት አዘጋጅ በርዴ ናቸው።)

## የጋዜጣ ግልባጮች

ታህሳስ 5 ቀን 1953 በጨቋኙ የንጉሰ ነገስትመንግስት ላይ የተነሳውን ወታደራዊ ንቅናቄ ምክንያት በማድረግ ብዙ የውጭ አገር ጋዜጦችና መፅሄቶች ስለኩ ዴታው፡ስለመሪዎቹ፡ስለኢትዮጵያ ውስጣዊ ሁኔታ ሰፋፊ ሀተታዎችን አቅርበዋል።

አንዳንዶቹ የእለቱን አጭር ዜና በመስጠትና አንዳንድ በዘልማድ የሚሰነዘሩ—ኩ ዴታ በተነሳ ቁጥር—ባዶ ንግግሮች በማካፈል ሲወሰኑ ግማሾቹ ጉዳዩን ጠለቅ አድርጐ በመመልከት፡ምንም እንኳን ንቅናቄውን ያነሱትና ያከናወኑት ጥቂት ሰዎች ቢሆኑ መነሻው የብዙው አመት የህዝብ ጭቆና፡ችግርና የሰው ልጅ መብት መደምሰስ መሆናቸውን ግዙፍ የሆኑ ማስረጃዎችን እየሰጡ ለማስረዳት ሞክረዋል።

በዚያን ሰሞን ስለኩ ዴታው የቀረቡትን የጋዜጣ ሀተታዎች እንደገና መመልከት ሊረሱ የደረሱትን ዝርዝር ዜናዎች—ጥሎልን የሄደውን ዋና ቅርስና የተነሳሳበትን አቢይ ምክንያትማ እንዴት መርሳት እንችላለን!—ለማዘከር እንደሚረዳ በመገንዘብ ጉልተው ከታዩን ፅሁፎች አንዳንዶቹን(በሙሉ ሳይሆን በከፊል) ከዚህ በታች ለአንባቢዎቻችን እናቀርባለን።

የምናቀርበው ትክክለኛውን ትርጉም ብቻ ነው።አንዳንድ የሀቅ (facts) ስህተት ቢኖር የጋዜጠኛው እንጂ የኛ አለመሆኑን በቅድሚያ ለማስታወቅ እንወዳለን።

### "ኒውስዊክ"(NEWSWEEK)

ጃንዋሪ 2፡1961

"አንበሳውና ድርጊቱ"

ባለፈው ሳምንት አዲስ አበባ፡ዳግማዊ ምኒልክ ሃውልት አጠገብ፡የአንድ የኢትዮጵያ ኰሎኔል ሬሳ ተንጠልጥሎ በመድረቅ ላይ ይታይ ነበር።ሬሳው፡ልክ ከኩዴታው በፊት ሃይለስላሴ ካቢኔ ውስጥ የፀጥታ ሹም የነበረው፡የኰሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ ነው።በቅርቡ ተ



ነስቶ የከሸፈው፡ብዙ ደም ያፋሰሰው አመፅ መሪ በመባል በጥይት ከሞተ በኋላ አስከሬኑ ለማስጠንቀቂያ ያህል እንዲሰቀል ተደረገ። በዚህ አይነት፡ሶስት ቀን የቆየው አመፅ ተሰብሯል ማለት ነው።ንጉሰ ነገስቱ ተመልሷል፣ሚዳቆቹም ቤተ መንግስቱ መስክ ላይ ይቧርቃሉ።ይሁን እንጂ፡መሰረታዊ ጥያቄዎቹ መልሳቸውን አላገኙም። አመፁ ለምን ተነሳ? ፊውዳሉ ስርአት ላይ ምን አይነት ተፅንኦ ይኖረዋል?

### ላሪ ክሊንስ የተባለ የኒውስዊክ ጋዜጠኛ ካዲስ አበባ ያስተላለፈው ዜና

ንጉሱ አመፁን በማቃለል "ለግል ስልጣን ምኞት" ባላቸው ጥቂት መኰንኖች የተነሳሳ መሆኑን ገልፀዋል።ነገር ግን፡የአመፁ መሪዎች ብዙዎቹ የሃይለስላሴ ታማኝ አገልጋዮች ነበሩ።ንጉሱ ራሱ የኰሎኔል ወርቅነህን ተባባሪነት ሲሰማ የቄሳርን የመጨረሻ ቃል በሚያስታውስ አማርኛ፡«ወርቅነህም?ወርቅነህም?» አለ ይባላል።ከመሪዎቹ አንዱ ቢርጋዴር ጄኔራል መንግስቱ፡የክብር ዘበኛ አዛዥ ነበረ። አንዳንድ የአሜሪካን ዜጋዎች በግጭቱ ጊዜ በታው ላይ ተገኝተዋል።ከነርሱም አንዱ በኢትዮጵያ የአሜሪካን አምባሳደር የሆነው 53 አመት እድሜ ያለው፡አርቱር ሪቻርድስ፡በሁለቱ ወገኖች መካከል ይላላክ ነበር።የንጉሱ ደጋፊ ጦር ሰራዊት ቤተ መንግስቱን በወጋበት ጊዜ፡ሪቻርድስ እዛው ስለነበረ በመስኮት ዘሎ አመለጠ።

....ዛሬ አመፁ ተፈፅሞ ቢታይ፡መነሻ የሆኑት ምክንያቶች በፍፁም ሳይነኩ፡እንዳሉ ይገኛሉ።ሃይለስላሴ እ.አ.አ. በ1931 ዓ.ም. በቋቋመው ምክር ቤት ውስጥ መሉ የተቃውሞ(ቬቶ) ድምፅ አለው። የንጉሱ የግል ማእድኖች አሁንም በባሪያዎች እየተቆፈሩ የሚገኘው ወርቅ በጥሬው እየተጫነ ስዊስ አገር ወደ ሚገኘው የባንክ ካዝና ይገባል።ምናልባት ከሁሉ አሳሳቢ የሚሆነው፡አመፁ የአገሪቷን ፊውዳል አቋም እንዲለውጥ ከማፋጠን ይልቅ ያዘገየው እንደሆን ነው።በዚህ ሳምንት ውስጥ፡አመፁ በመንግስቱ ፖለቲካ ላይ ምን ለውጥ ሊያስከትል እንደሚችል በተጠየቀ ጊዜ፡የደሁዳው አንበሳ "አንዳችም" ብሎ መልሷል።

ዲሴምበር 26፡1960

ላሪ ኮሊንስ ዜናውን ሲደመድም፦

ምንም እንኳ አንዳንድ እርምጃዎች ቢታዩ፡በመላው አገር፡ህዝቡ እንዳጉረመረመ ነው።ንጉሱ ሙሉ የቆራጭ ፈላጭነት ስልጣን አለው።ምክር ቤቱ በሱ ፈቃድ ስር ነው፤ሰብአዊ መብቶች በፀጥታ ጠባቂዎች እጅ ሲሆኑ ደብዳቤዎች ይፈተሻሉ፤ስልክ ይቀዳል፤ወህኒ ቤቶች በጥርጣሬ ተይዘው በገቡ እስረኞች ተጣቧል።በሚልዮን ከሚቆጠረው ህዝብ አንድ አስረኛው ብቻ ነው የተማረው።በሽታ በያይነቱ በጣም የተስፋፋ ነው፤የመናገሻው ከተማ መንገዶች ሁሉ በለማኞችና በሽባዎች የተወረረ ነው።

በዚህ አንፃር ስንመለከተው፡ያለፈው ሳምንት አመፅ ለሃይለስላሴ አደጋ ከመሆኑም በላይ ማስጠንቀቂያ ነው።ንጉሱ ዙፋኑን ለማዳን መቻሉ በአልጋወራሹ እንደበት የተነበበው ፅሁፍ ያዘለውን እውነት በምንም አያስተባብለውም።

“ታ ይ ም” (TIME)

ዲሴምበር 26፡1960

. . . . አመፁ ሲጠነሰስ ከአመት በላይ ሆኖታል፤አመፀኞቹም ከኢትዮጵያ ምሁር ክፍል የተውጣጡ ናቸው።በግልፅም ሆነ በሽሽግ፡ከተሳተፉት መከከል የካቢኔ ሚኒስትሮች፡ታላላቅ አስተዳዳሪዎች፡የጦር ሀይል ኰሎኔሎችና ከውጭ አገር የተመለሱ ተማሪዎች ይገኙበታል።ሁሉም ሃይለስላሴ አስተዳደሩን በስልጣኔ ዘዴዎቹ ለማሻሻል ይመኩበት ከነበረው ክፍል የተውጣጡ ናቸው።በፊውዳሉ ስርአትና አቋም፡በተለይ የሚማረረው ይኸው ክፍል ነው።አመፀኞቹ ምንም አይነት የተጣራ የፖለቲክ ቀለም (ዝንባሌ) አልነበራቸውም።. . . . የእንቅስቃሴው ዘር በተማረው ሰው ዘንድ ፍሬ ይዟል፤ማደጉም አይቀርም።

የቀድሞውና የወደፊቱ ንጉስ

. . . . አገዛዙ፡ምንም እንኳ ሃይለስላሴ “መንግስታዊ ሶሺያሊዝም” ነው ቢል፡የፈላጭ ቆራጭነት ስልጣን በራሱ እጅ የሆነበት ንጉሳዊ



መንግስት ነው።አነስተኛ የመንግስት ስራ ለማግኘት ጠያቂው እንደተለመደው “ግንባር ማስመታት” አለበት።በየቀኑ ባለጉዳዮች ቤተ መንግስት ውስጥ ተሰልፈው ንጉሰ ነገስቱ አይኑን ይጥልባቸው ዘንድ በተስፋ ይጠባበቃሉ።እድለኛ ሆኖ ለመቅረብ ከቻለ፡ፊቱን መሬት ላይ ደቅኖ ጉዳዩን በማመልከት ንጉሱ የሚቸረውን ውሳኔ ይቀበላል።የንጉሱ ሃይል ሽርክ፡የቤተ ክህነት ድርጅት ነው።ይህ ድርጅት የኢትዮጵያን መሬት 40% ሲይዝ ጥቅሙ እንዳይነካበት ሲል የለውጥ እንቅፋት ነው።

የተማሩ ኢትዮጵያውያን፡ውጭ አገር ተምረው የተመለሱት፡400 ምሁሮች ጭምር፡ፊት ማስወጋትንና የቀረውን፡ጊዜው የተላለፈበት የፊውዳል ልምድና አቋም ይቃወማሉ።ንጉሱ ግን በ68 አመት እድሜው አገሩን ወደ ዴሞክራሲ ለመምራት አይቸኩልም።ስራውን ከፍ ከፍ ሊያደርጉለት የሚሞክሩት አወዳሾቹ የሚያስታውሱት፡በሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት አንጉል ልምዶች እንዲቀሩ መደረጋቸውን ነው።ለምሳሌ ያህል ባርነት መቅረቱን፡ሌባ ቀኝ እጁን ከመቆረጥ መዳኑን፡ጥሬ ስጋ በድግስ ላይ መበላቱ መቅረቱን ይጠቅሳሉ።

ጃንዋሪ 2፡1961

. . . . የተደረገው የአመፅ ሙከራ የተመራውና የተንሳሳው «በጥቂት ግለሰብ መኰንኖች ነው» ሲል ንጉሱ ለጋዜጠኞች አስታውቋል።ሃይለስላሴ ንግግሩን በመቀጠል አመፀኞቹ ደህንነትና ጭቆና ይቅር ብለው ሲነሱ፡«እራሳችን በትምህርት፡በጤናና በጠቅላላው በህብረተሰብ ረገድ ያቀድነውን የእድገት ፕሮግራም መደገፋቸው ነው» አለ።. . . . ስልጣኑን ተመልሶ መጨበጡን ለማስታወቅ ያህል፡በጥይት የተበሳሳውን የአንድ የአመፁ መሪ ሬሳ በአደባባይ እንዲሰቀል አዘዘ።

አመፁ (ሆን ብለው ንጉሱ ብራዚል በሚገኝበት ጊዜ ነው የጀመሩት።) ተደምስሷል፤ነገር ግን ብዙ ደም መፋሰስ አትርፏል።በትንሹ 325 ሰው ሞቷል።. . . ይህ አመፅና ወደፊት ሊመጣ የሚችለው የባሰ ሁከት፡የሃይለስላሴ የፊውዳል መንግስት እንዲለወጥ ያደ

ርገዋል ወይ?«በፍፁም» ሲል ራሱ ንጉሱ መልሷል።ነገር ግን ማ ርጀቱ፡መድከሙና በሀዘን መዋጡ ፊቱ ላይ ተፅፎ ይታይ ነበር።

"ኢቭኒንግ ስታንዳርድ" (የእንግሊዝ ጋዜጣ)

ዲሰምበር 15፡1960 (በርእሰ አንቀፁ ውስጥ)

...አገሪቷ በፖሊስ መንግስት ነው የምትተዳደረው ለማለት ይቻ ላል፤መጭው ዘመን ምን እንደሚያስከትል ለመገመት ያስቸግራል።

"ኤዲንበርግ ኢቭኒንግ ኒውስ" (እንግሊዝ)

ዲሴምበር 15፡1960

....አመፁን ያስነሱትን ምክንያቶች ለመገመት አያስቸግርም።ን ጉሡ ስልጣኑን ቀጥ በሌለው አይነት በጁ ይዟል።

"ኢስት አፍሪካን እስታንዳርድ" (ምስራቅ አፍሪቃ)

ዲሴምበር 15፡1960፡-ፀሀፊው ኬነት ሜደውዝ

...በመንግስት ትእዛዝ ስር ያሉት የሀገሪቷ ጋዜጦች የንጉሱን ን ግግር ሁሉ ከሰማይ የወረደ ቃል በማስመሰል ለህዝቡ ያቀርባሉ። በችግር የሚኖረው 90% የኢትዮጵያ ገበሬ ህዝብ በዚህ ሊደናገ ጥ ይችላል።የቀረው ግን አይታለልም።ምክንያቱም፡3,000 አመት ነፃነቷን ጠብቃለች የተባለችው አገር ከጎረቤት አፍሪቃ አገሮች ጋር ስትነፃፀር የቱን ያህል ወደኋላ እንደቀረች በግልፅ ይታያቸዋል።

ዲሴምበር 16፡1960

...የኩ ዴታው ግብ የንጉሱን ዙፋን ለመደምሰስ ሲሆን፡ለድሃው ህዝብ ደህንነት ምን ያህል ሊሰራ እንደተነሳ ጊዜ ብቻ ነው ሊያረ ጋግጥ የሚችለው።

"ኢስት አንግሊያን ደይሊ ታይምስ" (እንግሊዝ)

ዲሴምበር 17፡1960

...በአገሪቷ ውስጥ ስልጣን ለመያዝ በሚደረገው ትንንቅ የትኛ ውም ወገን ድልን ቢቀዳጅ፡በአለም የመጨረሻው የፊላጭ ቆራጭ ነት ስልጣን ያለው ንጉስ የወደፊት እድል የተለየ ይሆናል።...በ ኢትዮጵያ የሚታየው፡ጊዜው የተላለፈበት የፊውዳል ስርአት በ



አለም ውስጥ በሌላ ቦታ በዛሬው ጊዜ የሌለ አቋም ነው።...ህዝቡ ድምፁን አዲስ አበባ ድረስ የሚያሰማበት መንገድ የለውም፤የንጉ ሱ ድምፅ ግን፡አብዛኛውን ጊዜ በመትረየስ አፈሙዝ አማካይነት ነ ው የሚሰማው።ልዩ ልዩ አዋጆች በአማርኛ ሲታወጁ የያዘው ፍሬ ነገር የሚገባው አዋጁን ላወጡትና ለቀሩት አማርኛ ለሚገባቸው ብቻ ነው።ሌላውን አብዛኛውን ህዝብ ከጉዳይ የሚቆጥረው የለም አመፁ የተነሳሳው ይህን ሁሉ ለመለወጥ ነው።

"ሊቨርፑል ደይሊ ፖስት" (እንግሊዝ)

ዲሰምበር 17፡1960፡-ፀሀፊው ሮማን ኩክ

በመንቃንቅ ላይ ባለችው በአፍሪቃ ክፍል አለም ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከዛሬ ሁከት ሳይነሳ መቆየቱ የሚያስገርም ነው።ሁኔታ ው እንደዚህ ላለው ድርጊት ምቹ ከሆነ ብዙ ጊዜ አልፎታል።በዚ ህ ምክንያት የሆኑት ሁለት ነገሮች ናቸው።አንደኛ፡የሃይለስላሴ ከ ባድ ተፅንእ፤ሁለተኛ፡አገሪቷ በመገናኛ መስመሮች፡በውስጥም ሆነ በውጭ፡በጣም የተራራቀች መሆኗ።

"ዘ አብዘርቨር" (እንግሊዝ)

ዲሰምበር 18፡1960፡-ፀሀፊው ኮሊን ልጉም

....ሃይለስላሴ የአገሪቷን እድገት ከማስገኘት ይልቅ የራሱን የግ ል ስልጣን ማዳበር ነበር ጥረቱ።የግል አገዛዙን የሚቃወሙት ሃይ ሎች ቁጥራቸው ብዙ፡ምንጫቸው የተለያየ ነው።

በመሰረቱ ከሁሉ አደገኛ የሆነው ተቃውሞ የሚመጣው የሸዋው ን ክፍል የጭቆና አገዛዝ ከሚቃወመው እንደ ትግሬ፡ጎጃም፡ሰማ ሌ፡ጋላ፡ኤርትራ ያሉ ህዝቦች ነው።

ሁለተኛው የተቃውሞ ክፍል፡ወጣት ወደፊት ተራማጆችንና ወጣ ት የጦር መኰንኖችን ይይዛል።ወደፊት ተራማጆች ምሁሮች ሲሆ ኑ ብዙዎቹ ውጭ አገር የዩኒቨርሲቲ ትምርት ያገኙ ናቸው።ንጉሱ አስተዳደሩን እንዲመሩለት በነሱ ላይ ተስፋ ነበረው።ነገር ግን፡ከፍ ያለ ቦታና ደመወዝ እያገኙ ምንም አይነት ስልጣንና ሀላፊነት አ ይሰጣቸውም።የሃይለስላሴን ስልጣን ደግፎ የያዘው የቀድሞው ባ

ላባታዊ መዲብ አያስቀምሳቸውም።ወጣት የጦር መኰንኖች ደግሞ ምንም እንኳ በጦር ሰራዊትና በክብር ዘበኛ ቢከፋፈሉ በአስተያየት አንድነት አ ቸው።ይህ የመከፋፈል ድርጊት ጦር ሃይሎች እንዳያይሉ ሆን ብሎ የተሰራ ነው። ... መኰንኖቹ የተማሩና የሰለጠኑ ናቸው።ኰንጐና ኰሪያ አገልግሏል።ኩሩና በሀገራቸው በፖለቲካና በኢኰኖሚ ወደኋላ መቅረት የሚያፍሩ ናቸው።ስለዚህም ከወደፊቱ ተራማጆች ጋር ብዙ ጊዜ ይስማማሉ።

....ሶስተኛው የተቃውሞ ክፍል፣ከገገርው መደብ በግዞት የራቁ ሰዎችን ሲያጠቃልል የዛሬው ስርአት ሳይነካ አንዳንድ ጥገናዊ ለውጥን የሚሹ ይሆናሉ።ወጣት ምሁሮችና የጦር መኮንኖች ምንም እንኳ ሪቮሉሽናዊ መሆናችው ቢያጠራጥር አስተያየታቸው ከዚህኛው ክፍል አስተያየት ይበልጥ ወደፊት ተራማጅ ነው።

"ዘ ኢኰኖሚስት" (እንግሊ.ዝ)

ዲሴምበር 24፡1960

....አመፁ ባጭር በመቀጨቱ በውስጡ የነበረው የግራና የቀኝ ሃይል ሚዛን በትክክል ሳይጣራ ቀርቷል።አንድነታቸው የተመሰረተው የጊዜውን ስርአት ለማጥፋት በመፈለግ ላይ ብቻ ነበር።

"ዘ ታይምስ ዊክሊ ሪቪዩ" (እንግሊ.ዝ)

ዲሰምበር 22፡1960

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ለሪቮሉሽን ምቹ ነበረ። ... ከሁለተኛው አለም ጦርነት ወዲህ ንግድና አስተዳደር ላይ የተመሰረተ መካከለኛ መደብ በመፈጠር ላይ ሲሆን፡ይህ መደብ ጠቅላላ ህብረተሰቡ ውስጥ ሊዋሀድ አልቻለም።ብዙዎቹ ወጣት የመኳንንት ልጆች የዚህን መደብ አላማና አስተያየት ይደግፋሉ።ምክንያቱም ህብረተሰባዊ ለውጥ እንዲመጣና ኢትዮጵያ በአፍሪቃ የነፃነት ትግል ውስጥ ተገቢ ቦታዋን እንድትይዝ ይሻሉ።

"ኒው ስቴትስማን" -ዲሴምበር 24፡1960

አመፁ የተጠነሰሰበት ሁኔታ ግልፅ ነው።ኢትዮጵያ በኢኰኖሚ ረገድ በምታደርገው የተንቀረፈፈ እድገትና ባላት ከባድ የአስተዳደር ስርአት፣ወጣት ኢትዮጵያውያኖች ቅሬታቸው በጣም ከፍ ያለ ነው።ወጣት መኰንኖች በማእርግ እንዳያድጉ ከበላያቸው ያሉት የጦር አለቆች ቦታውን ይዘው ያግዷቸዋል።የውጭ አገር ትምህርት የቀመሱት ወጣት የመንግስት ሰራተኞች የአለቆቻቸው ብልሹ የስራ አመራር እንቅፋት ስለሚሆንባቸው ይበሳጫሉ።በወጣቶቹና እድሜአቸው በገፋ በጥንት ባለስልጣኖች መካከል ከፍ ያለ ጥላቻ አለ።

"ዘ ፋይናንሺያል ታይምስ" ፡-ዲሰምበር 15፡1960

ጣልያን ከወጣ ወዲህ ስልጣኑን የያዙት ከ500 አማራ ቤተሰቦች የተውጣጡት ባለርስት መኳንንት ሲሆኑ፡የሃይለስላሴ ዙፋን እንዲጠበቅ የነዚህ ራሶች ድጋፍ ያስፈልጋል።እነዚህ ጥቂት ባላባቶችና መሳፍንቶች ቀለሙ ቀላ ያለውን ደገኛ የአማራ ህዝብ በመወከል የገገርውን መደብ ፈጥረዋል።የግላቸው የተዋሀዶ ክርስትና ባህል ከ1,000 አመት በላይ የቆየ አላቸው፤ከአገሪቷም ህዝብ በብዛት አንድ ሶስተኛ ይሆናሉ።የቀረው ሁለት ሶሰተኛው በተለይ ከጥቁር አፍሪቃውያን ነገዶች የማይለይ ሲሆን በምስራቅ ኢትዮጵያ ደግሞ ለየት ያሉ የሶማሌ ህዝቦች ይገኙበታል።

ጣልያን ከወጣ ወዲህ ለሃገሪቱ እድገት ይህ ተሰራ ለማለት አያስደፍርም ።በዚህ የተነሳ ንጉሱ በጣም ይወቀሳል።ከሶቪየት ህብረት 36 ሚልዮን ፓውንድ በብድር ስም መቀበሉ ስለዚሁ ነው።ምንም እንኳ ይህ ብድር ለወደፊት የልማት እቅድ ቢያስከትል በኢኰኖሚ በኩል የመንግስቱ ደካማነት ግልፅ ሆኗል።በተለይም በጦር ሰራዊቱ ውስጥ በጣም ብዙ ቅሬታን ፈጥሯል።

የኢትዮጵያ ስታቲስቲኮች ልንተማመንባቸው አንችልም።ይሁን እንጂ፣አሉ የሚባሉትን ግምቶች እንኳ ብንወስድ ከአፍሪቃ ውስጥ በእድገታቸው ወደኋላ ከቀሩት አገሮች አንዷ መሆኗን እናያለን።በነፍስ ወከፍ ገቢ በአመት 15 ፓውንድ ሲሆን የህዝቧ ብዛት ደግሞ ከ15 እስከ 20 ሚልዮን ይገመታል።

"ስቬንስካ ዳግብላደት" (ስዊድን)

ዲሰምበር 16፥1960

ነፃነት ነገሰ፤የፊውዳል ጭቆና ተደመሰሰ

በስዊድን የኢትዮጵያ አምባሳደር የነበሩት አቶ ተፈሪ ሻረው አዲ
ሱን መንግስት በማወቅ ለጋዜጠኞች ያደረጉትን የሁለት ሰአት ን
ግግራቸውን «ነፃነትና ዴሞክራሲ ለዘልአለም ይኑሩ» በማለት ዘጉ።
በንግግራቸው ውስጥ የሃይለስላሴን መንግስት እውነተኛ መልክ ለ
ማጋለጥተችሏል።መንግስቱ ፊውዳል ስርአት ላይ በመመስረት የህ
ዝብን ባርነት ያስከትላል።የሀሳብ ነፃነት ኖሮ አያውቅም፤የሚፃፉት
ጋዜጦች ሁሉ ንጉሱን የሚያሞጉሱ ናቸው።አለም በሞላ ስለኢት
ዮጵያ ያለው አስተያየት ትክክለኛ አይደለም።በንጉሱ የሚነገሩት
የዴሞክራሲና የስልጣኔ ቃላቶች በዶ ፕሮፓጋንዳ ነው፤የእውነተኛ
ውን የባርነት ሁኔታ ለመሸፈን ነው።ዲስኩሮቹን ይፅፍ የነበረው
ስፔንሰር የሚባል አሜሪካዊ ሲሆን በአመት $100,000 ደሞዝ
ይሰጠው ነበር።ንጉሱ አገሩን በፖሊስ ሃይል በመጠቀም ነበር የሚ
ገዛው።ደስ ያላለውን ሁሉ ለማስገደል አይመለስም።80% የሚሆ
ነው የኢትዮጵያ ህዝብ በችጋር ሲንገላታ እሱ ይህ ነው የማይባል
ሀብት ወደአሜሪካን፥እንግሊዝና ስዊስ ባንኮች ያሸሽ ነበር።ከስዊ
ድን ያገኘውን እርዳታ የራሱን ሃይል ለማዳበሪያ ነው ያዋለው።
የግል ጭፍሮቹን ሚኒስትር በማድረግ የህዝቡን ደም ይመጣል።
ከፓርላማ አባሎች ውስጥ ተቃውሞ የሚያነሳ ሁሉ የደረሰበት ሳ
ይታወቅ ጠፍቶ ይቀራል።

"ኤክስፕሬሰን" (ስዊድን)

ማርች 6፥1961

....በጠቅላላው ከአህያ የዋለች ጊደር ፊስ ተምራ ትመጣለች የ
ሚባለውን በማስታወስ፡እኛ ስዊድኖች ከማን እንደምንውል ለይተ
ን ማወቅ አለብን።በራዲዮና በቴሌቪዥዮን ኢትዮጵያን ለመርዳት
ከፍ ያለ ፕሮፓጋንዳ ይደረጋል።ይህ በመሰረቱ ጥሩና ትክክል ነው።
ነገር ግን፥ኢትዮጵያ ውስጥ የነገሰው መንግስት የጭቆናና የሀይል



መንግስት መሆኑን መዘንጋት አይገባም።ንጉሱና የሚደግፉት ከፍ
ተኛ መደቦች ወሰን የሌለው ሀብት አጠራቅመዋል።ከዚህም ሀብ
ት ለህዝቡ የሚደርሰውና ችግሩንና ስቃዩን የሚያቃልልለት ቅን
ጣት እንኳ የለም።ከንጉሱ ሃብት ሲምንቱ እንኳ ስራ ላይ ቢውል
አገሩ ውስጥ የተስፋፋውን ቁምጥናን ለማሸነፍ በተቻለ ነበር።

"ላ ናዝዮኔ" (ጣልያን)

ዲሴምበር 22፥1960

የሰባቱ ቀን ፍርሃት በአዲስ አበባ

የአሜሪካን ቦታ

....የአሜሪካን የጦር አታሼ በኤምባሲው አማካይነት "ከስቴት
ዲፓርትሜንት" ጋር ግንኙነት ከደረገ በኋላ አሜሪካ የንጉሰጓደጋ
ፊዎች ለመርዳት ተነሳ።በኢትዮጵያ ውስጥ በጄኔራል ዴግራብ የ
ሚታዘዝ ያሜሪካን "ሚሊተሪ አሲስታንስ አድቫይዘሪ ግሩፕ" (ማ.
ግ.) አለ።ናዝሬት በሚባለውም ቦታ ታንክና ከባድ መሰሪያ በሱ አ
ሰልጣኝነት ስር አለ።እነዚህ ሰራዊቶች ወድያውኑ ወደቢሾፍቱ እ
ንዲንቀሳቀሱ ተደረገ።የጦር ሃይሉ የአመፀኞቹ ተቃዋሚ ሆነ።ያሜ
ሪካን ለንጉሱ ታማኞች ረዳት መሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ድብልቅ
ልቅ እንዳይፈጠርና ተቃዋሚ ርእዮተአለም እንዳይተናኝ ነው።የ
እንግሊዝ ኤምባሲም በዚሁ ጉዳይ ገብቶበታል።እንዲያውም በአ
ገሩ ውስጥ ኩዴታ መሆኑን በመጀመሪያ ለንጉሱ ያስታወቀው ይ
ኸው ኤምባሲ ነው።

ዲሴምበር 25፥1960

«በኢትዮጵያ በሃይለስላሴ ላይ መነሳት ተጀመረ እንጂ አላለቀም»

....ወደፊት ግራም ነፈሰ ቀኝ አንድ ነገር እውነት ነው።ይኸው
ም ሃይለስላሴ በባላባታዊ አገዛዙና "በንጉሱ ብሩህዊ አስተያየት"
ሊቀጥል አይችልም።

«ህዝቡ ባለኩ ዴታዎቹን እየተረዳቸው ሄደ»

አስከሬናቸው ተሰቅሎ የሚታየው የኩዴታው መሪዎች ህዝቡ በ
ሀዘን መልክ ይመለከታቸዋል።ይህ ሃዘኑ የመጣው ምናልባት የተ
ነሱበትን አላማ በመረዳቱ ይመስላል።

| ይዘት | ገጽ |
| --- | --- |
| 1. ርእሰ-አንቀጽ | 1 |
| 2. የ5 ታህሳስ 1953 የመንግስት ግልበጣ ሙከራ ዝርዝር ዜና | 18 |
| 3. የታህሳስ ጀግኖች | 34 |
| 4. የታህሳሱ እንቅስቃሴ "አናቶሚ" | 40 |
| 5. የታህሳሱ ኩ ዴታ ለምን ከሸፈ? | 58 |
| 6. "አዲሱ መንግስት" በየሃገሩ ለሚገኙ ኤምባሲዎች ያስተላለፈው ቴሌግራም | 68 |
| 7. የጋዜጣ ግልባጮች | 70 |